**ማውጫ** **ገጽ**

ምዕራፍ አንድ

እርባ ቅምር እና አሉታ ........ 2

፩.፩ መግቢያ ........ 2

፩.፪ እርባ ቅምር ........ 2

፩. ፫ አሉታ ........ 12

፩.፬ ንባበ ልሣነ ግእዝ ........ 20

፩.፬.፩ የሰላምታ አሰጣጥ/ተአምኆ በልሣነ ግእዝ ........ 20

፩.፬.፪, ስንብት ........ 24

ምዕራፍ ፪

ንዑስ አንቀጽ እርባታ እና አዕማድ ........ 26

፪.፩ ንዑስ አንቀጽ እርባታ ........ 26

፪.፪ አዕማድ ........ 31

፪.፫ ንባበ ልሳነ ግእዝ ........ 36

፪.፫.፩ ትውውቅ (ራስና ለሰዎች ማስተዋወቅ፤ ሌላ ሰውን ለሌላ ሰው ማስተዋወቅ) ........ 36

ምዕራፍ ፫

ክፍላተ ንግግር ........ 38

፫.፩ ስም ........ 38

፫.፪ ቅጽል ........ 42

፫,፫ አገባብ ........ 44

፫.፫.፩, ዐቢይ አገባብ ........ 44

፫.፫.፪ ንዑስ አገባብ ........ 46

፫.፫.፫ ደቂቅ አገባብ ........ 49

፫.፪ ንባበ ልሣነ ግእዝ ........ 54

፫.፪.፩ የስልክ ንግግር / ንባብ በምህላፈ ቃል ........ 54

# ምዕራፍ ፩

## እርባ ቅምር እና አሉታ

### ፩.፩ መግቢያ

በግእዝ ቋንቋ ውስጥ ከሚሰጡ የተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ሰፊውን ቦታ የሚይዘው የሰዋስው ክፍሉ ነው። ይህ የትምህርት ክፍል ሰዋስው ተብሎ በአንድ ቃል ይነበባል መሰላልና መሸጋገሪያ ተብሎ በሁለት ቃል ይፈታል። ሰዋስው ስለምን መሰላል ተባለ ቢሉ በመሰላል ከታች ወደ ላይ ይወጡበታል።ከላይም ወደ ታች ይወርዱበታል። በሰዋስውም በእግረ ሕሊና ሰማየ ሰማያት ወጥቶ ዕመቀ ዕመቃት ወርዶ በዓይነ ልቡና ምሥጢረ ሥላሴን ያዩበታል። መሸጋገሪያ ያለው ስለምን ነው ቢሉ በመሸጋገሪያ ከወዲህ ወዲያ፤ ከወዲያ ወዲህ ይመላለሱበታል።ይሸጋገሩበታል። በሰዋስውም በእግረ ልቡና እምጽማዌ ውስጠ ጥበብ፤እምኢያእምሮ ውስተ አእምሮ ይመላለሱበታል። ስለዚህ እርባ ቅምር ሰዋስው ተባለ ይላሉ።

የግእዝ ቋንቋ ሰዋስው በአጠቃላይ በአራት ታላቅ ክፍል ይከፈላል።

፩. እርባ ቅምር

፪. እርባ ግሥ

፫. ነጠላ ግሥ

፬. አገባብ

### ፩.፪ እርባ ቅምር

እርባ ቅምር ማለት የግሥን እርባታ በጠቅላላ ከነአዋጁ እና ከነሠራዊቱ የሚያስተምረን ክፍል ነው። ይህ ክፍል የግሥ አርእስት የሚሆኑትን ቀለማት ከሠራዊታቸው ጋር አመላቸውን የሚያሳይ፤ የሚጠብቅና የሚላላውን፤ በአንድ ቃል በብዙ የሚፈታውን፤ በራሱ ቋሚ ሲሆን ገቢርና ተገብሮ የመሰለውን፤ በሥርዓት የማይሄደውን ግሥ ሁሉ በየሥርዓቱ ከፍሎ አካሄዱንና ጠባዩን ሁሉ የሚያሳውቅ ነው። እርባ ቅምር በ ፳፰ ክፍል ይከፈላል። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ፩. መራኍት | ፲፩. መራኍያን | ፳፩. ስንዕው |
| ፪. አርእስት | ፲፪. ሳቢ ዘር | ፳፪. ሠጋርያን |
| ፫. ሠራዊት | ፲፫. ልማድ | ፳፫. ውላጤ ግእዝ |
| ፬. አዕማድ | ፲፬. ባዕድ ዘር | ፳፬. ምዕላድ |
| ፭. አሥራው | ፲፭. ኅርመት | ፳፭. አላኀላኀያን |
| ፮. ፀዋትው | ፲፮. ዝርዝር ቅጽል | ፳፮. ወኀጥያን |
| ፯. ዐቢይ አንቀፅ | ፲፯. ገዳፍያነ ዘመድ | ፳፯. ተመኵሳውያን |
| ፰. ንኡስ አንቀፅ | ፲፰. ወሳከያነ ዘመድ | ፳፰. ዝርው |
| ፱. ደቂቅ | ፲፱. ቱሱሐን | |
| ፲. ባዕድ ቅጽል | ፳. ተጻማሪ | |

በዚህ የትምህርት ክፍል ከላይ ከተጠቀሱት መካከል ዋና ዋና እና አስፈላጊ የሆኑትን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

**፩.፪.፩ ገዳፍያነ ዘመድ**

እነዚህ በእርባታ ጊዜ በፊት መነሻቸውን፤ በኋላ መድረሻቸውን እየተዉ የሚሄዱ ግሦች ናቸው። አካሄዳቸውም በ ፫ ወገን ነው።

<u>**መጀመሪያ አካሄድ**</u>

ይህ 'ተ' የሚዋጥበትን እርባታ ያሳያል። ይኸውም 'ተ' በሰድስት ፊደላት መነሻ ሲሆን ( ሰ፤ተ፤ዘ፤ደ፤ጠ፤ጸ ) በዐቢይ አንቀጽ ከሀላፊ በቀር በትንቢት፤በዘንድ፤በትእዛዝ አይገኝም። ፊደላቱ በግእዝ፣በራብዕ እና በሳድስ ይገባሉ።

**ምሳሌ፡-**

- ተሰብሐ: ይሴባሕ፡ይሰባሕ፡ይሰባሕ
- ተሣለቀ: ይሣለቅ፡ይሣለቅ፡ይሣለቅ
- ተትሕተ: ይቴሐት፡ይተሐት፡ይተሐት
- ተዘከረ: ይዜከር፡ ይዘከር፡ ይዘከር
- ተደመረ: ይዴመር፡ይደመር፡ይደመር
- ተጠየረ: ይጤየር፡ይጠየር፡ይጠየር
- ተፅዕነ: ይፄዐን፡ይፀዐን፡ይፀዐን

<u>**ሁለተኛ አካሄድ**</u>

'ተ' መነሻ 'ወ' መድረሻ ሆኖ ፬ ቀለማት በሆነ ግሥ በዐቢይ አንቀጽ ከሀላፊ በቀር በትንቢት፣ በዘንድና በትዕዛዝ መድረሻ ፊደሉ 'ወ' ይጠፋል። የመድረሻውን መሪ በሣብዕ ይጎርዳል።

**ምሳሌ፡-**

- ተሠገወ: ይሤጎ፡ይሠጎ፡ይሠጎ
- ተደለወ: ይዴሎ፡ይደሎ፡ይደሎ
- ተፈነወ: ይትፌኖ፡ይትፈኖ፡ይትፈኖ (ተፈነወ በሚለው የ 'ተ' ተከታይ 'ፈ' ከሰባቱ ፊደላት ውስጥ ስለሌለ አልጎረደም።)

<u>**ሦስተኛ አካሄድ**</u>

'ወ' አሁን ከተናገርናቸው ሌላ ደጊመ ቃል በሌለበት ቃል በካዕብ ይጎርዳል።

**ምሳሌ ፡-**

**በቀተለ ቤት**

- ተለወ: ይተሉ፤ይትሉ፤ይትሉ

**በገብረ ቤት**

- መሰወ: ይመሱ፤ይምሱ፤ይምሱ

**በቀደሰ ቤት**

- ለበወ: ይሌቡ፤ይለቡ፤ይለቡ

**በተንበለ ቤት**

- ሰንቀወ: ይሰነቁ፤ይሰንቁ፤ይሰንቁ

**በባረከ ቤት**

- ፃመወ: ይፃሙ፤ይፃሙ፤ይፃሙ

በክህለ ቤት ግን በትንቢት ብቻ ይጎርዳል። ይኸውም ምሕወ ብሎ ይምሑ፤ ይምሐው፤ ይምሐው የሚለውን ያሳያል።

**<u>አራተኛ አካሄድ</u>**

'ተ' መነሻ፤ 'የ' መድረሻ ሆኖ ፍጹም ግእዝ ፬ ቀለማት ከሆነ ግሥ እና ደጊመ ቃል ካለበት በቀር 'የ' መድረሻ ሲሆን በሣልስ ይጎርዳል።

በቀተለ ቤት በ 'ሀ' ፤በ 'አ' ሲነሳ በትንቢት፤ በዘንድና በትዕዛዝ ይጎርዳል። በቀረው በቀተለና በክህለ ቤት በትንቢት ብቻ ይጎርዳል። በዘንድ እና በትዕዛዝ ይገኛል።

**ምሳሌ፡-** ዐረየ: የዐሪ፤ይዕሪ፤ይዕሪ

ኀለየ:የኀሊ፤ይኅሊ፤የኀሊ

ጥዕየ: ይጥዒ፤ይጥዐይ፤ይጥዐይ

በገብረ፤ በቀደሰ፤ በተንበለ፤ በባረከ እና በዴገነ ቤት በትንቢት፤ በዘንድና በትዕዛዝ ይጎርዳል።

**ማሰረጃ፡-** መስየ: ይመሲ፤ይምሲ፤ይምሲ ( ገብረ )

ሐለየ: ይሔሊ፤የሐሊ፤የሐሊ ( ቀደሰ )

ጌገየ: ይጌጊ፤ይጌጊ፤ይጌጊ ( ዴገነ )

አመክነየ: ያመክኒ፤ያመክኒ፤ያመክኒ ( ተንበለ )

**<u>አምስተኛ አካሄድ</u>**

በቀተለ፤በገብረ፤በክህለ ቤት 'ወ' እና 'ው' መነሻ ሲሆኑ 'ወ' እና 'ው' መነሻ የነበሩት በትንቢት ይገኛሉ።በዘንድ እና በትእዛዝ ይታጣሉ።

**ማስረጃ፡-** ወረደ: ይወርድ፤ይረድ፤ይረድ

ወድቀ: ይወድቅ፤ይደቅ፤ይደቅ

ውኅዘ: ይውኅዝ፤የኅዝ፤የኅዝ

በቀደሰ እና በተንበለ ቤት 'ወ' መነሻ ሲሆን አይጎርድም።

**ምሳሌ፡-** ወደሰ: ይዌድስ፤ይወድስ፤ይወድስ

ወርዘወ: ይወረዙ፤ይወርዙ፤ይወርዙ

**<u>ስድስተኛ አካሄድ</u>**

በቀደሰ በገብረ ቤት 'ወ' መነሻ ሲሆን የሳቢ ዘራቸውን መነሻ ይጎርዳል።በ 'የ' ከጨረሱ ግን አይጎረዱም።

**ምሳሌ፡-** ወለደ: ልደት ወድቀ: ድቀት

ውዕየ: ውዕየት ወቀየ: ውቅየት

<u>**ሰባተኛ አካሄድ**</u>

ገዳፍያነ ዘመድ የተባሉት አራቱ ቀለማት (ቀ፣ከ፣ገ፣ነ) በግሥ መጨረሻ ላይ ሲገኙ የሚያመጡት ለውጥ ነው። ዝርዝራቸውን የግሥ ዝርዝር በመራሕያን በሚለው ክፍል ተመልከት።

<u>**ስምንተኛ አካሄድ**</u>

በከህለ ቤት 'የ' በመድረሻ ሲገኝ በ፮ መራሕያን (በአራቱ ሁለተኛ መደቦች እና በአንደኛ መደቦች) በሣልስ ይጎርዳል፤

ርእየ፤ርኢከ፤ርኢክሙ፤ርኢኪ፤ርኢክን፤ርኢኩ፤ርኢነ

**ምልማድ ፩**

**የሚከተሉትን ግሦች እስከ ትዕዛዝ አንቀጽ ድረስ አረባ፡፡**

ሀ. ተሣለቀ ሰ. ተድኀረ ኀ.ኖለወ

ለ. ተስዕረ ሸ. ተጠብለለ ነ. ርእየ

ሐ. ተዝኀረ ቀ. ተሠረወ ኘ.ወረደ

መ. ተፃረረ በ. ተቀነወ አ.ውኅጠ

ሠ. ተፅዕነ ተ. አመንተወ ከ. ወጽአ

ረ. ተወግዐ ቸ. ፃዕደወ ኸ. ተባረከ

**፩. ፪. ፪ ቱሱሐን/ተጻይ እርባታ**

እነዚህ በእርባታ ጊዜ የቀተለን ከቀደሰ፤ የቀደሰን ከቀተለ የሚያደበላልቁ፤ የሚለዋውጡ ግሦች ናቸው። አካሄዳቸውም በአምስት ወገን ነው።

<u>**መጀመሪያ አካሄድ**</u>

የቀተለን፤ የባረከን፤ የከህለን ተገብሮ የመሰሉ በእርባታ ጊዜ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የቀደሰን አካሄድ ይሄዳሉ።

**ምሳሌ፡-** ተኀየየ: ይትኄየይ፤ይትኀየይ፤ይትኀየይ

ተልዕለ: ይትሌዐል፤ይትለዐል፤ይትለዐል

ተዋነየ: ይትዌነይ፤ይትዋነይ፤ይትዋነይ (በካልአይ ይትዋነይ ም ይላል)

<u>**ሁለተኛ አካሄድ**</u>

"ወረወ፤ወጠነ፤ፀዐለ፤ገረመ"ን የመሰለ ግስ በኃላፊ የቀተለን፤ በትንቢት የቀደሰን ከዚያ በታች እንደገና የ ቀተለን አካሄድ ይሄዳል።

**ምሳሌ፡-** ወረወ: ይዌሩ፤ይውሩ፤ይውሩ

ወጠነ: ይዌጥን፤ይውጥን፤ይውጥን

ፀዐለ: ይፄዕል፤ይፅዐል፤ይፅዐል

ገረመ: ይጌርም፤ይግርም፤ይግርም( በዘንድና በትዕዛዝ ይግርም፤ይግርም ይላል)

<u>**ሦስተኛ አካሄድ**</u>

'ጠፈረ፤ፀፈረ' ን የመሰለ ግስ በኃላፊ የቀደሰን በትንቢት በዘንድና በትእዛዝ የቀተለን በአርእስት የቀደሰን አካሄድ ይሄዳሉ።

**ምሳሌ፡-** ጠፈረ: ይጠፍር፤ ይጥፍር፤ይጥፍር፤ጠፍሮ/ሮት

ፀፈረ: ይፀፍር፤ይፅፍር፤ይፅፍር፤ፀፍሮ/ሮት

**ማስታወሻ ፡-**

- ጸፈረ ጽፍርን ቆረጠ ሲል ይጼፍር ይላል

<u>**አራተኛ አካሄድ**</u>

'መሀረ ፤ወገረ' ን የመሰሉ ግሦች በኃላፊ ፍጹም የቀተለን ሲሆኑ በአንድ ቃል በሁለት ነገር እየተፈቱ በአንዱ ፍቺ የቀተለን በአንዱ ፍቺ የቀደሰን እርባታ የሚሄዱና በአዋጅ የማይጸኑ ናቸው።**ምሳሌ፡-**

**ሀ.** መሀረ (አስተማረ): ይሜህር፣ይምሀር፤ይምሀር፤ምሀሮ/ሮት

መሐረ (ራራ፤ይቅር አለ): ይምሕር ይምሐር፤ይምሐር፤ምሒር/ሮት

**ለ.** ወገረ (መታ): ይዌግር፤ይውገር ይገር፤ይውገር ይገር

ወገረ (ዕጣን አሳረገ): ይወግር፤ይውግር ይገር፤ይውግር ይገር

**ሐ.** ቀሠመ (አጣፈጠ): ይቄሥም፤ይቀሥም፤ይቀሥም

ቀሰመ (ቆረጠ): ይቀስም፤ ይቅስም፣ይቅስም

**ማስታወሻ፡-**

- ከላይ ካየነው በተጨማሪ በአንድ ወይም በሁለት ፊደላት ጠባይ ልውውጥ ምክንያት ሁለት ትርጉም ይዘው የተለያየ

  እርባታ ያላቸው ግሦችም አሉ።

**ምሳሌ፡- ሀ.** ረዐየ( ጠበቀ ): ይሬዒ፤ይርዐይ፣ይርዐይ

ርእየ (አየ): ይሬኢ፤ይርአይ፤ይርአይ

**ለ.** ቀረበ (ቆረበ): ይቄርብ፤ይቀርብ፤ይቀርብ

ቀርበ( ቀረበ): ይቀርብ፤ይቅረብ፤ይቅረብ

**ሐ.** ወሀከ (አነሳሳ): ይዌሀክ፣የሀክ፣የሀክ

ሆከ (አወከ): የሀውክ፤ይሁክ፣ይሁክ

**<u>አምስተኛ አካሄድ</u>**

በአንድ ቃል በሁለት እየተፈቱ በመጥበቅ የቀደሰን በመላላት የቀተለን የሚሆኑ ግሦች ናቸው።

**ምሳሌ፡- ሀ.** መከረ (ፈተነ)፡ ይሜክር፣ይመክር፤ይመክር

መከረ (ምክር መከረ)፡ ይመክር፤ይምክር፤ይምክር

**ለ.** መልሐ (አጣፈጠ)፡ ይሜልሕ፤ይመልሕ፤ይመልሕ

መልኀ (መዘዘ፤ነቀለ)፡ ይመልኅ፤ይምላኅ፤ይምላኅ

**ሐ.** ሰበከ (ጣዖትን ሠራ፤ቀረጸ)፡ ይሴብክ፤ይሰብክ

ሰበከ (አስተማረ)፡ ይሰብክ፣ይስብክ፤ይስብክ

**መ.** ጸብሐ (ገበረ፣ሙብዓ ሰጠ)፡ ይጼብሕ፤ይጸብሕ፤ይጸብሕ

ጸብሐ (ጠባ)፡ ይጸብሕ፤ይጽባሕ፤ይጽባሕ

**ምልማድ ፪**

***ሀ. የሚከተሉትን ግሦች ከነአማርኛ ትርጉማቸው እስከ አርእስት አንቀጽ ድረስ አርቡ።***

፩. ጸለለ (ሸፈነ፤ጋረደ) እና ጸለለ (ሠፈረ)

፪. መሰለ (በምሳሌ ተናገረ) እና መሰለ (መሰለ)

፫. ሐለየ (አሰበ )እና ኀለየ( ዘመረ ፤አመሰገነ)

፬. ፈጸመ (ጨረሰ) እና ፈጸመ (ለጎመ፤ዘጋ)

፭. ነስሐ (ተጸጸተ) እና ነስሐ (ሸተተ)

፮. ሰብሐ (አመሰገነ) እና ሰብሐ (ሰባ፤ ወፈረ)

፯. ሠረሐ (አቅናና) እና ሠረሐ (ሰራ፤ደከመ)

**ለ. የሚከተሉትን የግእዝ ዓ.ነገሮች ወደ አማርኛ ለውጡ**

፩. ንዑ ኀቤየ ኵልክሙ ስሩሓን ወክቡዳነ ፆር

፪. ወእመሰ ኢተመየጥክሙ ሰይፎ ይመልሕ

፫. ንዑ ደቂቅየ እምሀርክሙ ፈሪሃ እግዚአብሔር

፬. ረዐይ አባግዕየ

፭. ብፁዓን መሐርያን እስመ እሙንቱ ይትመሐሩ

፯. ርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ ኵሉ

፰. ሐዋርያት መሀሩ እለ አእመርዎ

፱. ዘሰብሐ ትጠብሑ ወትበልዑ ወባሕቱ ኢረዐይክሙ አባግዕየ

፲. ናሁ ደመና ብሩህ ጸለሎሙ

፲. ፈጸመ ዳንኤል አፈ አናብስት

፲፩. ይእተ አሚረ ይሜስሉ ምሳሌ ላዕሌክሙ

፲፪. ሐለየ አቡየ ከመ ይሑር ርኁቀ ፍኖተ

**ሐ. ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

፩. ቀደሰ ብሎ ይቄድስ ካለ ተሰብሐ ብሎ --------ይላል። ሀ. ይሴብሕ ለ. ይሰባሕ ሐ. ይሴባሕ መ. ይትሰባሕ

፪ .----- እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ። ሀ. ይባረክ ለ. ቡራኬ ሐ. ይትባረክ መ. ሀ እና ሐ

፫ .ዖደ ብሎ የዐውድ ካለ ተጽሕፈ ብሎ ---------ይላል። ሀ. ይትጸሐፍ ለ. ይጽሐፍ ሐ. ይጸሐፍ መ.ይጽሕፍ

፬ .አ አንስት ለምንት------- ሶበ ርኢክናሁ ለውእቱ ነዳይ። ሀ. ሰሐቅሙ ለ. ሰሐቅክን ሐ. ሰሐቃ መ. ሰሐቅን

፭. ትክክል ያልሆነው እርባታ የቱ ነው።

ሀ. ተጸወነ:ይጼወን፤ይጸወን፤ይጸወን ለ. ተልዕለ: ይትሌዐል፤ይትለዐል፤ይትለዐል

ሐ. መሐረ: ይሜሕር፤ይምሐር፤ይምሐር መ. ተሰቅለ: ይሰቀል፤ይሰቀል፤ይሰቀል

**፩. ፪. ፫ አላኅላኅያን**

አላኅላያን የተባሉ ፊደላት ፫ ናቸው፡፡እነዚህም “ሀ”፤”አ” እና “በ” ናቸው፡፡አላኅላኅያን የተባሉበት ምክንያትም በተቀመጡበት ቦታ ሆነው የተጠቀሰውን ግሥ አላልተው ስለሚያስነብቡ ነው፡፡

“ሀ” እና “አ” መነሻና መሀከል ሲሆኑ በሁሉ አይጠብቁም፡፡

“በ” ም በማንኛውም ግሥ ላይ ሲወድቅ አላልቶ ያስነብባል እንጅ አያስጠብቅም፡፡

**ማስታወሻ** “በ” ሁለት ፊድላት ኖሮት ፍፁም ግእዝ በሆነ ግሥ ላይ ይጠብቃል፡፡ ከዚህ በቀር በሁሉ ይላላል፡፡

**ምሳሌ**፡- ጠበ ---ይጠብቃል፤ ጠበበ---ይላላል

**፩. ፪. ፬ ውኅጥያን**

ውኅጥያን የተባሉ ፬ ቀለማት ናቸው። እነዚህም እየጠበቁ ቀለም ውጠው የሚያስቀሩ ቀለማት ቀ፤ገ፤ከ፤ነ ናቸው። እነዚህም በግእዛቸው፤ በራብዓቸው፤ በሣልሳቸው፤ በካዕባቸው፤ በሣድሳቸው፤ በሳብዓቸው አይቀርም በሁሉ ይገባሉ፡፡

**ማስታወሻ፡-** ከላይ ከተጠቀሰው ሌላ ቀለማትን አጥብቀው የሚያስቀሩ ቀለማት የሚከተሉት ናቸው፡፡

***ሀ.*** “ተ” በይእቲ ዝርዝር በኃላፊ አንቀጽ በራሱ ይጠብቃል፡፡

**ምሳሌያት ፡-** በግእዝ ፡ ረከበተኒ፤ ረከበተከ፤ ረከበተኪ፤ ረከበተነ

በራብዕ ፡ ረከበታ

በሳብዕ ፡ ረከበቶ፤ ረከበቶሙ፤ ረከበቶን

**ለ.**ፍፁም ግዕዝ ሁለት ቀለም የሆነ ግሥ መጨረሻው ይጠብቃል፡፡

**ምሳሌ** ፡ ሐመ፤ ጠበ፤ መረ

**ሐ.** የ "ተ" እና የ "ጠ" ግሦች የሩቂቱ ሴት ውስጠ ዘ መድረሻ ፊደሉ (ት ወይም ጥ) ይውጣል፡፡

**ምሳሌያት ፡** ምውት እንጅ ምውትት አይልም።

ፍልጥ እንጅ ፍልጥት አይልም።

**፩. ፪.፫. ተመኲሳይያን**

ተመኲሳውይያን የሚባሉት ግሦች አንድ ቃል ወይም ተመሳሳይ ተጨማሪ ቃል ይዘው

በትርጉም በተለያየ የሚፈቱ ግሦች ናቸው፡፡ አካሄዳቸው ፬ ወገን ነው፡፡

**፩.** በምስጢር የማይገናኙ እየራሳቸው የቆሙ ሲሆኑ አድራጊ፤ አስደራጊ፤ ተደራጊ ከመሰሉ ሌሎች ግሦች ጋር ሲመሳሰሉ የተለያየ ትርጉም አላቸው፡፡

**ምሳሌያት፡- ሀ.** ሴለየ (ለየ) → አድራጊ

ብእሲ ጠዋይ ይዘርዕ ሐከከ ወይሌሊ አዕርከተ።

አሌለየ (ማለደ) → አስደራጊ

አሌለያ ገይሰ ወሖራ ኀበ መቃብር።

**ለ.** ኀለየ (ዘፈነ፤ዘመረ) → አድራጊ

ምሕረተ ወፍትሐ አኀሊ ለከ።

አሕለየ (መማለጃ ሰጠ) → አስደራጊ

አሕለይከዮሙ ይምፅኡ ኀቤኪ።

**ሐ.** ሐመ (ታመመ) → አድራጊ

በእንቲያነ ሐመ።

ተሐመመ (ተመቀኘ) → ተደራጊ

ተሐምሞ ወተቃትሎ ስታይ ወስከረት ወዘአምሳሌሁ ለዝንቱ ዘይገብር።

ኢይሬኢ መንግሥተ እግዚአብሔር።

አስተሐመመ( አዘጋጀ፤ሰበሰበ ) → አደራራጊ

አስተሐመመ ዘውስተ ገዳም ሀመልማለ።

**፪.** በአንድ ቃል ሁለት ነገር እየተፈቱ በመጥበቅ የቀደሰን በመላላት የቀተለን ሚሆኑ ግሶች ናቸው። እነዚህንም ቱሱሐን በሚለው ክፍል ተመልክተናል።

፫. በአንድ ቃል ተነበው በብዙ ነገር የሚፈቱ ግሦች ናቸው።

**ምሳሌያት ፡-**

**ላኅልኀ** በ ፬ ይፈታል፡፡

ሀ. ላኅልኀ (ራሰ )፡ ይቡሰ ኀብስተ በማይ አላኅልኀ።

ለ. ላኅልኀ (ላላ)፡ ሶበ ይከውን አውታረ መሰንቆ ሉኅሉኀ ይጠፍዕ ቃናሁ እመኢተሰሐበ።

ሐ.ላኅልኀ  (ዘነጋ)፡ በእንተ ልኅላኄ ሕሊናሁ በአኮሰ በእንተ ድካመ ሥጋሁ።

መ. ላኅልኀ (ዛለ፤ታከተ)፡ እሉ አኃው ኮኑ ልኅሉኀነ።

**ቆመ** በ ፬  ይፈታል።

ሀ. ቆመ (ቆመ)፡  እቀውም ቅድሜከ ወአስተርኢ ለከ።

ለ. ቆመ (ጸና)፡  ወትቀውም እዴየ በኵነኔየ።

ሐ. ቆመ (ተተከለ)፡ ያቀውም ደብተራሁ።

መ.ቆመ (ተተካ)፡ ንጉሥ ሰሎሞን ቆመ በመንበረ አቡሁ።

**፬.** እነዚህ ተመኵሳውይያን ከአገባብ፤ከዘር፤ከነባር የሚገኙ በንባን አንድነት፤በነገር ልዩነት ያላቸው ቃላት ናቸው፡፡(አንዳንድ ጊዜም በንባብ ሊለያዩ ይችላሉ)።

**ሀ**. አእመራ  = አወቃት            የአምራ፤ያእምራ፤ያእምራ

= አወቁ              የአምራ፤ያእምራ፤ያእምራ

**ለ**.ከነባር እና ከአገባብ

እም =እናት (ነባር)              እምነ እናታችን(ነባር)

እም =ከ (አገባብ)               እምነ ከ (አገባብ)

**ምሳሌያት፡-** አልቦ አብ ወአልቦ እም(እናት ተብሎ)።

ወፅአ ትእዛዝ እምኀበ ቄሳር(አገባብ ሲሆን)።

እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ(እናታችን ሲሆን)።

እምነ ረሀብ ይኄይስ  ኲናት(ከ ሲሆን)።

**ሐ**. ከዘር እና ከነባር የሚወጡ በፊደል አንድ እየሆኑ በብዙ ነገር የሚፈቱ ቃሎች አሉ፡፡

ምሳሌ ፡- መና-------ምግብ፤እጅ መንሻ፤ገጸ በረከት ይሆናል።

ወአዝነመ ሎሙ መና ይብልዑ(ምግብ)።

ንሳእ መና ምስሌከ ወሑር ወተቀበሎ(እጅ መንሻ)።

ቀምሕ------አዝመራ፤ፍሬ፤ሙብል ይሆናል

ዐቃቢሁ ለቀምሕ ይሬኢ ፍሬሁ(አዝመራ)

ይበልዑ ዕፀወ ቀምሕ(ፍሬ)

ይቀምሕ አንበሳ ሐሠረ ከመላሕም(ምግብ)

**<u>ምልማድ ፫</u>**

**የሚከተሉትን የግእዝ ዐረፍተ ነገሮች ወደ አማርኛ ለውጡ፡፡ከዚያም ተመኵሳውይያኑን ለዩና በየትኛው አካሄድ እንደሚፈቱ ተናገሩ፡፡**

፩. ሀ. ማዕዜ ይከውን ነግህ

ለ.ወሖራ ወአንገሃ ጥቀ ሐዊረ ኀበ መቃብር

፪. ሀ. ወቤተት ኀበ እገሪሁ እስከ ይጸብሕ

ለ.ኢትጻብሖ ወእመቦ ዘኢተጻባሕከ ኢታውሥእ

፫. ሀ. መቅድሕተ እሳት ይክዕዉ ላዕሌሆሙ

ለ.ትከውን ምቅዳሐ ለኵሉ ነገሥተ ዓለም

፬. ሀ. ለምንት ትቴክዚ ወለምንት ተሀውከኒ እመኒ በእግዚአብሔር ከመእገኒ ሎቱ

ለ.ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐዩ

፭. ሀ. ኵሉ ትውልድ ይብሉ እምነ ጽዮን ሰላም ለኪ

ለ. ነግሠ ሞት እምነ አዳም እስከ ሙሴ

፮. ሀ. አርባሕከ ትምክሕተ በርእስከ ወበሰብዕከ ኀሳረ ወዝንጋኄ

ለ.ወበስቴከ መስተፍስሒ አርብሐኒ ተድላ

**፩. ፪.፮ ዝርው**

ዝርው የተባሉ ከአርዕስትና ከሠራዊት ስም የሌላቸው ቀለማት “ቈ” “ኰ” “ጐ” “ኈ” ን መነሻ መሀከል መድረሻ ያደረጉ ግሦች ናቸው፡፡ እነዚህም በየራሳቸው በየጠባያቸው ይረባሉ፡፡

**ምሳሌያት፡-** ሀ. ኈለቈ (ቆጠረ)፡ ይኌልቍ፤ይኈልቍ፤ይኈልቍ

ለ. ለሐኰ(ሠራ)፡ ይልሕኵ፤ ይልሐኵ፤ ይልሐኵ

ሐ.ጐየ(ሸሸ)፡ ይጐይይ፤ይጒይይ፤ይጒይይ(ይጒየይ )

**<u>ምልማድ ፬</u>**

**የሚከተሉትን ግሦች እስከ ትዕዛዝ አንቀፅ ድረስ አርቡ፡፡**

ሀ.ጐሕቈ ለ.ጐጕዐ ሐ. ጐንደየ መ.ጐድአ ሠ. ቈቀኆ

## ፩. ፫ አሉታ

በትምህርተ ልሳነ ግእዝ ውስጥ የሚገኙ ዐረፍተ ነገሮች፤ ንባባት ሁሉ በሁለት ዐበይት ክፍል ይከፈላሉ።

ሀ. በአወንታ(በጽድቅ) የሚነገሩ ዐ.ነገሮች

ለ. በአሉታ(በአፍሽ) የሚነገሩ ዐ.ነገሮች

**ሀ.በአወንታ(በጽድቅ) የሚነገሩ ዐ.ነገሮች**

ይህ ዐ.ነገር ስሙ እንደሚያመለክተው የሚነገረው በእሺታ፤ በእውነታ ወይም በሆነ ተብዬ አባባል ነው።

በዚህ አባባል ውስጥ የሚጠቀሱት ነባር አንቀጾች ውእቱ፤ቦ፤ሎ ን ያጠቃልላሉ፡፡(ዝርዝራቸውንም ያጠቃልላል)

ምሳሌያት ፡

- ቦ እለ ይብሉከ ዮሐንስሃ መጥምቅ።
- አነ ውእቱ ገብርኤል መልአክ ዘእቀውም በቅድመ እግዚአብሔር።
- ላቲ ዘመድ በዝንቱ ብሔር።

**ለ. በአሉታ(በአፍራሽ) የሚነገሩ ዐ.ነገሮች**

ይህ ዐ.ነገር በእንቢታ፤ በተቃራኒው ወይም በአልሆነም ተብዬ የሚነገር ዐ.ነገር ነው። በግእዝ ቋንቋ አሉታ በሁለት አይነት መልኩ ይመሰረታል።

፩. እርስ በርስ በማቃረን

፪. ባዕዳን ፊድላትን በመጠቀም

**<u>፩.የሰዋሰው የእርስ በርስ መቃረን</u>**

ይህ የአሉታ ዐይነት የሚፈጠረው አንዱ ሰዋሰው ለሌላው ምንም አይነት ባዕድ ፊደል ሳይጠቀም በተፈጥሮ ሲቃረነው ነው።

**ምሳሌያት፡-**

| **ጽድቅ** | **አሉታ** |
|---|---|
| ዐረገ | ወረደ |
| አብድ | ጠቢብ |
| ቀርበ | ርሕቀ |
| ሀየለ | ደከመ/ሐከየ |

**ምልማድ ፮**

**የሚከተሉትን ቃላት እርስ በርስ በማቃረን አዛምዱ**

| <u>**ሀ**</u> | <u>**ለ**</u> | |
|---|---|---|
| ፩.ከሰተ | ሀ.ጻድቅ | ረ.ምውት |
| ፪.ሐነጸ | ለ.ሰወረ | ሰ.ሥርዐ |
| ፫.ቡሩክ | ሐ.አብርሀ | ቀ.ሐከየ |
| ፬.ሕያው | መ.ነሰተ | በ.ኖለወ |
| ፭.ተግሀ | ሠ.ርጉም | |

**፪. በባዕዳን ፊደላት መቃረን**

ይህ የአሉታ ዐይነት የሚፈጠረው በተጠቀሰው ቃል ላይ ሌላ ባዕድ ፊደልን በመጨመር ነው፡፡በግእዝ ቋንቋ የታወቁት ቃላተ አሉታ የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. አኮ | ሐ. ሐሰ |
| ለ. አል | መ. ኢ |

## ሀ. አኮ

“አኮ” ን በአሉታነት የምንጠቀመው ውእቱ በነባር አንቀጽነቱ ጊዜ የነበረውን ትርጉም በአሉታነት ለመግለጽ ነው፡፡

ውእቱ በአስሩም መራሕያን በመሆንና በመኖር ግስ ስልት ይፈታል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ውእቱ | በመሆን ግሥ---- ነው፤ሆነ<br>በመኖር ግሥ-------- አለ፤ኖረ፤ነበር | ውእቱ |
| ውእቱ | በመሆን ግሥ----- ናቸው፤ሆኑ<br>በመኖር ግሥ----- አሉ፤ኖሩ፤ነበሩ | ውእቶሙ |
| ውእቱ | በመሆን ግሥ----- ናት፤ሆነች<br>በመኖር ግሥ----- አለች፤ኖረች፤ነበረች | ይእቲ |
| ውእቱ | በመሆን ግሥ---- ናቸው፤ሆኑ<br>በመኖር ግሥ---- አሉ፤ኖሩ፤ነበሩ | ውእቶን |

“አኮ” የ “ውእቱ” አሉታ ነው ስላልን

አኮ ውእቱ ________እሱ አይደለም፤እሱ አልሆነም፤የለም፤አልኖረም፤አልነበረም

አኮ ውእቶሙ _____አይደሉም፤አልሆኑም፤የሉም፤አልኖሩም፤አልነበሩም

አኮ ይእቲ ________አይደለችም፤አልሆነችም፤የለችም፤አልኖረችም፤አልነበረችም

**ምሳሌያት ፡-**

- አንተ ውእቱ ______ አኮ አንተ
- ትጉሀ ውእቱ ዮሐንስ_____ አኮ ትጉሕ ዮሐንስ
- አኮ በእንተ ጻድቃን ባሕቲቶሙ አላ ኃጥአንሂ ይስእል ሎሙ ከመ ይምሕሮሙ እዝአብሔር

**ማስታወሻ ፡-**

፩. አኮ ከግስ ወይም ከስም (መራሕያንንም ጨምሮ) በፊት ሊመጣ ይችላል። ከግስ በፊት ከመጣ ድርጊት አድራጊው አይታወቅም። ከስም በፊት ከሆነ ግን አድራጊውን ለይተን እናውቃለን።

**ምሳሌያት ፡-**

ሀ. አንተ ውእቱ ዘቀተልኮ ለዝንቱ አረዌ ምድር(አወንታ)

፩. አኮ አንተ ዘቀተልኮ ለዝንቱ አረዌ ምድር (አድራጊው የሚታወቅበት አሉታ)

፪. አኮ ዘቀተልኮ  አንተ  ለዝንቱ አረዌ ምድር (አድራጊው የማይታወቅበት አሉታ)

ለ. አንተ ውእቱ ዘተሐንጽ ቤትየ (አወንታ)

፩. አኮ አንተ  ዘተሐንጽ ቤትየ (አድራጊው የሚታወቅበት አሉታ)

፪.አኮ   ዘተሐንጽ አንተ ቤትየ (አድራጊው የማይታወቅበት አሉታ)

፪. በ አኮ ላይ ኑ እና ሁ ሲጨመሩ ወይም ትራስ ሆነው ሲነበቡ ጥያቄ ያስነሳሉ። አይደለምን፤ አልሆነምን፤ አልኖረምንም ተብለው ይፈታሉ።

**ምሳሌያት ፡-**

ሀ. አኮኑ ይቤ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ የኀልፍ ወቃልየሰ ኢየኀልፍ።

ለ. ኩናኔ ሥጋ ወነፍስ እግዚአብሔር አኮኑ።

**ምልማድ ፮**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አወንታ ዐ.ነገሮች ወደ አሉታ ለውጥ። በአሉታ ከተጠቀሱ ደግሞ ወደ አወንታ ለውጥና ትርጉማቸውን ተናገር።

፩. ንሕነ ውእቱ እለ ገበርነ ዘንተ ግብረ

፪.አንትን ውእቱ ትጉሃት

፫.በኀብስት ከመ ዘየሐዩ ሰብእ

፬.አኮ ሉ ዘይብለኒ እግዚኦ፤እግዚኦ ዘይበውእ መንግስተ ሰማያት

፭.አኮ በመስፈርት ዘይሁብ እግዚአብሔር መንፈሶ

፮.አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ከበብ ከመ ፀሐይ ወወርኅ አላ ምሉዕ ውእቱ

፯. አ ድንግል ተንበሊ ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን

## ለ. ሐሰ

ሐሰ “ሐሰወ” ዋሸ፤ ሀሰት ተናገረ ከሚለው ግሥ የተገኘ አሉታ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አይገባም፤ አይሆንም፤ አይደለም፤ አይድረስ፤ ውሸት፤ የለም ወዘተ ተብሎ ይፈታል።

“ሐሰ”ን በሁለት ዓይነት መልኩ በአሉታነት እንጠቀምበታለን።

፩. “ሐሰ”ን ከማንም ቃላት ጋር ሳናያይዝ ለብቻው እንጠቀምበታለን።

ሀ. ይዔምጽኑ ሰብእ ሶበ ያመጽእ እግዚአብሔር መቅሰፍተ ላዕለ ብእሲ።

ለ.ምንት እንከ ንብል ንገብርኑ ኃጢአተ ከመይፈደፍድ ጸጋሁ ለእግዚአብሔር።

፪. “ሐሰ”ን በአሥሩ መራሕያን በ”በ” እና “ለ” እየዘረዘርን እንጠቀምበታለን።

| በ | ለ |
|---|---|
| ሐሰ ቦቱ አይድረስበት፤አይሁንበት | ሐሰ ሎቱ አይሁንለት፤ሀሰት ያድርግለት |
| ሐሰ ቦሙ አይድረስባቸው፤አይሁንባቸው | ሐሰ ሎሙ አይሁንላቸው፤ሀሰት ያድርግላቸው |

**ምሳሌያት ፡-**

ሀ. ሐሰ ለከ እግዚኦ ይኩን ዝንቱ ላዕሌከ

ለ. ሐሰ ለከ እግዚኦ ታጥፍአነ በይነ ዝንቱ ብእሲ

**ምልማድ ፯**

**የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አማረኛ ለውጡ**

፩.አንተኑ ዘትገብር ዘንተ ግብረ

፪.ሰዐረናሁ እንከ ለሕገ ኦሪት በእንተ አሚን ሐሰ፡፡አኮ ዘንስዕር ሕገ ኦሪት አላ ንሥርዕ

፫.ወእመኒ ቦ እለ ኢየአምኑ ኢአሚነዚአሆሙኑ ይከልዕ ባእድ ከመኢይእመን በእግዚአብሔር ሐሰ

፬.ሐሰ ለኪ እኅትየ ከመትቅትሊ ለአኀውየ

## ሐ. አል

“አል” የ ቦ ዝርዝር አሉታ ነው፡፡

ቦ የመኖር ግሥ ሲሆን በአሥሩ መራሕያን እንደሚዘረዘር በቀዳማይ ዓመት ትምህርት ውስጥ ተምረናል። አል የ ቦ ዝርዝር አፍራሽ ነው ስላልን በአሥሩ መራሕያን ይዘረዝራል።

**ምሳሌ ፡-**

ቦ ውእቱ እሱ አለ፤ኖረ፤ነበር አልቦ ውእቱ እሱ የለም፤አልኖረም፤አልነበረም

ቦ ውእቶሙ እነርሱ አሉ፡ኖሩ፤ነበሩ አልቦ ውእቶሙ እነርሱ የሉም፡አልኖሩም፤አልነበሩም

**በአጠቃላይ በአወንታ ቦ ሲዘረዘር**

ቦቱ/ቦ  አለው፤አለበት፤ኖረው፤ኑሮታል፤ኑሮበታል፤ነበረበት፤በእርሱ

ባ/ባቲ  አላት፤አለባት፤ኖራት፤ኑታል፤ኑሮባታል፤ነበረባት፤በእር

ቦሙ  አላቸው፤አለባቸው፤ኖራቸው፤ኑሮቸዋል፤ኑሮባቸዋል፤ነበረባቸው፤በእነርሱ

ቦን  አላቸው፤አለባቸው፤ኖራቸው፤ኑሮቸዋል፤ኑሮባቸዋል፤ነበረባቸው፤በእነርሱ

**በአሉታ ደግሞ ሲዘረዘር**

አልቦቱ  የለውም፤የለበትም፤አልኖረውም፤አልኖረበትም፤አልነበረበትም

አልባቲ  የላትም፤የለባትም፤አልኖራትም፤አልኖረባትም፤አልነበረባትም

አልቦሙ  የላቸውም፤የለባቸውም፤አልኖረባቸውም፤አልነበረባቸውም

አልቦቶን  የላቸውም፤የለባቸውም፤አልኖረባቸውም፤አልነበረባቸውም

**ምሳሌያት ፡-**

፩. ብየ መከራ ______ አልብየ መከራ

፪.አልብየ ዘእበልዕ______ ብየ ዘእበልዕ

፫.ዘየአምን በወልድ ቦ ሕይወት ዘለዓለም______ ዘየአምን በወልድ አልቦቱ ሕይወት ዘለዓለም

**ማስታወሻ ፡-**

- ቦ እና ሎ በእርባታ ቢመሳሰሉም ከትርጉም አንፃር ግን ይለያያሉ፡፡
  **ምሳሌ ፡**
  ቦቱ ዕዳ    ዕዳ አለበት(ካለበት ላይ የሚቀነስ)
  ሎቱ ንዋይ    ገንዘብ አለለት(ካለበት ላይ የሚጨመር)
- የሚከተለውን የትርጉም ልዩነት አስተውሉ

ቦ____ አለ፤ኖረ፤ነበር

አሉ፤ኖሩ፤ነበሩ

አልቦ ______ የለም፤አልኖረም፤አልነበረም

የሉም፤አልኖሩም፤አልነበሩም

- የሚከተሉት ግን የተሳቢነት ትርጉም ያመጣሉ፡፡

ቦቱ =አለው፤ኖረው፤ነበረው

ቦሙ =አላቸው፤ኖራቸው፤ነበራቸው

**በአሉታ ደግሞ ሲዘረዘር**

አልቦቱ = የለውም፤አልኖረውም፤አልነበረውም፤አልነበረበትም

አልቦሙ = የላቸውም፤አልኖራቸውም፤አልነበረባቸውም፤አልኖረባቸውም

- ቦ ላይ አንክሮን የሚያመለክቱ ፊደላት ሁ እና ኑ ትራስ እየሆኑት ሲነገር የጥያቄ ቃል ሆኖ አለን፤ይሆንን ተብሎ ይፈታል

**ምሳሌ ፡-**

ቦኑ ሰብእ ዘአምጽአ ሎቱ ዘይበልዕ።

ወይቤሎ ናትናኤል ቦኑ ይትከሀል እምናዝሬት ከመይፃእ ብእሲ ኄር።

- አል የሚለው አፍራሽ ለ ቦ ዝርዝር በአፍራሽነት የሚያገለግለው በመደበኛ ትርጉማቸው ብቻ ነው፡፡

**ምሳሌ ፡-** አልባቲ ነውር= ትክክል

ሞተ አልብኪ= ስሕተት

**ምልማድ ፰**

**የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ ግእዝ መልሱ**

ሀ. ከእግዚአብሔር ሌላ አምላክ የለም

ለ.በደል አልነበረበትም

ሐ. የሚሰማ ጆሮ የላቸውም

መ.ከአምላካችን በቀር የሚረዳን የለም

ሠ.የተናገረው እውነት እንጂ ሀሰት አይደለም

## መ. ኢ

ኢ በግስ አንዳንዴም በስም መነሻ ላይ እየገባ በአሉታነት የሚነገር ነባር አንቀጽ ነው፡፡ ኢ በዐ.ነገር ውስጥ የተለያየ አካሄድ አለው፡፡በተለያዩ ቦታዎች የተለያየ ትርጉምን ይሰጣል፡፡

**የ «ኢ» ትርጉም በተለያየ አናቅጽ ውስጥ**

ሀ. በቀዳማይ አንቀጽ የ ኢ ትርጉም "አል" ነው

ምሳሌ ፡- ጸሐፈ ኢጸሐፈ(አልጻፈም)

ደከምነ ኢደከምነ(አልደከምንም)

ለ.በካልአይ አንቀጽ የ ኢ ትርጉም "አ" ነው

ምሳሌ ፡- ትነብብ ኢትነብብ(አትናገርም)

ትነብሩ ኢትነብሩ(አትቀመጡም)

ሐ.በዘንድ አንቀጽ የ ኢ ትርጉም “እንዳ፤ላ፤ሳ” ነው

ምሳሌ ፡- ይቀድስ ኢይቀድስ(እንዳያመሰግን፤ላያመሰግን፤ሳያመሰግን)

ትሢሚ ኢትሢሚ(እንዳትሾሚ፤ላትሾሚ፤ሳትሾሚ)

መ. በትእዛዝ አንቀጽ የ ኢ ትርጉም “አ” ነው

ምሳሌ፡- ሑር ኢትሑር(አትሂድ)

ትቀትሉ ኢትቀትሉ (አትግደሉ)

ሠ. በቦዝ አንቀጽ የ ኢ ትርጉም “ሳ” ነው፡፡

ምሳሌ ፡- ቀቲሎ ኢቀቲሎ(ሳይገድል)

ጽሒፎ ኢጽሒፎ(ሳይጽፍ)

ረ. በ ውስተ ዘ የ ኢ ትርጉም “ያል፤የማ” ነው

ገባሬ መንክራት ኢገባሬ መንክራት(ድንቅ ስራ ያልሰራ፤የማሰራ)

ጸሐፍያተ መጽሐፍ ኢጸሐፍያተ መጽሐፍ (መጽሐፍ ያልጻፉ፤የማይጽፉ)

ሰ. ከ ስም በፊት ሲገባ “የለም” የሚል ትርጉም አለው

አመምህር ወኢደቀመዝሙር (መምህርም ተማሪም የለም)

ኢአማኒ ወኢተአማኒ (አማኝም ታማኝም የለም)

**ማስታወሻ ፡-**

- “ኢ” የሚጨመረው በ አ ዘር የሚጀምር ግሥ ከሆነ በቀዳማይ፤በካልአይ፤በዘንድና በትእዛዝ አንቀጽ የ ኢ ዘር በግልጽ ሲቀመጥ አይታይም፡፡

**ምሳሌ፡-** አእመረ ኢያእመረ

ኣእምር ኢያእምር

አአምር ኢየአምር

እቀትል ኢይቀትል

- “ኢ” በትእዛዝ አንቀጽ ላይ የሚጨመር ከሆነ ምንጊዜም ከ “ኢ” ቀጥሎ አስራው ቀለም “ይ”፤”ት”፤ ወይም “ን” ይመጣሉ፡፡

ምሳሌ ፡- ቅትል ኢትቅትል

አእምር ኢታእምር

ቅትሉ ኢትቅትሉ

- የ “ውእቱ” እና “አነ” አፍራሽ ዝርዝር እርባታ የሚለያየው በቀዳማይ አንቀጽ ብቻ ነው፡፡የ “አንት” እና “ይእቲ” ዝርዝር እርባታ የሚለያየው በቀዳማይ አንቀጽ ብቻ ነው፡፡

**ምሳሌ ፡-**

ውእቱ እና { ቀተለ ኢቀተለ፤ ይቀትል ኢይቀትል፤ ይቅትል ኢይቅትል

አነ { ቀተልኩ ኢቀተልኩ፤ እቀትል ኢይቀትል፤ እቅትል ኢይቅትል

አንተ እና { ቀተልከ ኢቀተልከ፤ ትቀትል ኢትቀትል፤ ቅትል ኢትቅትል

ይእቲ { ቀተለት ኢቀተለት፤ ትቀትል ኢትቀትል፤ ትቅትል ኢትቅትል

**ምልማድ ፱**

**ሀ. ለሚከተሉት አወንታ አናቅጽ አሉታቸውን ፈልግ**

| | |
|---|---|
| ፩.መጻእኩ | ፮.ግበር |
| ፪.ንበውእ | ፯.ተሐውሩ |
| ፫.ይቄድስ | ፰.አእመሮ |
| ፬.አሐውጽ | ፱.ዝልፍዋ |
| ፭.ይስምዑ | ፲.አእመርዋ |

**ለ. ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

፩. አተሑሩ የሚለው አንቀጽ --------አንቀጽ ነው፡፡ ሀ.ትእዛዝ ለ.ዘንድ ሐ.ትንቢት መ.ሀ እና ለ

፪.ወደሰ ብሎ ወድስ ካለ ኢወሰድኩ ብሎ-------ይላል። ሀ.ኢይወድስ ለ.ኢወድስ ሐ.ኢይዌድስ መ.ሀ እና ለ

፫.ኢይነብብ ልሣንየ ሐሰተ፡፡የዐ.ነገሩ ባለቤት------ነው፡፡ ሀ.አነ ለ.አንት ሐ.ውእቱ መ.ሀ እና ለ

፬. ኢይመጽ -----------ኀበ ቤተ ትምህርት። ሀ.አነ ለ.አበበ ሐ.አስቴር መ.ሀ እና ለ

፭. ይቁማ ብሎ ቆማ ካለ ኢትቁም ብሎ-----------ይላል፡፡ ሀ.ቆምከ ለ.ኢቆምከ ሐ.ኢቆመት መ. ለ እና ሐ

፮. ትግሁ ወጸልዩ ከመ ---------ውስተ መንሱት፡፡ ሀ. ኢትበውኡ ለ.ኢትባኡ ሐ.ትበውኡ መ.ትባኡ

፯. ኢትመጽእኑ ---------------ኀበ ቤተ ትምህርት። ሀ. አስቴር ለ.አበበ ሐ.አንተ መ. ሀ እና ሐ

፰. ይቀትሉ ብሎ ቀተሉ ካለ ኢይቅትል ብሎ --------ይላል። ሀ.ኢቀተለ ለ.ይቀትል ሐ.ኢቀተልኩ መ.ሀ እና ሐ

፱. ቀተልከ ብሎ ኢትቀትል ካለ አምነ ብሎ -------ይላል፡፡ ሀ.ኢያምነ ለ.ኢይመን ሐ.ኢትእመን መ.ይእመን

፲. ”አታግባን” የሚለው በግእዝ ቃል ሲተካ፦ ሀ. አኮ አብአነ ለ.ኢታብአነ ሐ.ኢቦእከነ መ.ኢታበውአነ

## ፩.፬ ንባበ ልሣነ ግእዝ

**፩.፬.፩ የሰላምታ አሰጣጥ/ተአምኖ በልሣነ ግእዝ**

ሰዎች ከሰዎች ጋር ሲገናኙ ወይም ሲለያዩ ሰላምታ ይሰጣጣሉ ይሰነባበታሉ፡፡ በግእዝ ቋንቋም ሰላምታ መሰጣጣትም ሆነ መቀበል ይቻላል፡፡

በዚህ ክፍልም እንዴት ሰላምታ እንደምንሰጣጥ እንማራለን፡፡ የሰላምታ አሰጣጥ በግእዝ ቋንቋ ተአምኖ ይባላል፡፡

በግእዝ ቋንቋ ሰላምታ ለመሰጣጣት የምንጠቀንባቸው ቃላት ሦስት ሲሆኑ እነርሱም፡-ሰላም፣ በሓ እና እፎ ናቸው፡፡

## ሀ, ሰላም

ብዙ ጊዜ ሰላምታ ለመስጠት እና ለመቀበል የምንጠቀመው ቃል ‹‹ሰላም›› የሚለውን ነው፡፡ሰላም የሚለውን ቃል በሁለት ዓይነት መንገድ ለንጠቀምበት እንችላለን፡፡

፩, ብቻውን፡-ሰላም የሚለው ቃል ከሌሎች ቃላት ጋራ ሳይጫፈር ብቻውን ሰላምታ ለመስጠትም ሆነ ለመቀበል ያገለግላል፡፡

- ሰላም እብል ኪያከ መልአከ ርኅርኅ ልብ ለኩሉ  መልአከ ሩህሩሀ ልብ ለኩሉ አንተ ኢኮንክ ድሩከ____ ለሁሉ የምትራራ ጨካኝ ያይደለህ አንተን መልአኩብ ሰላም እልሀለሁ።
- ሰላም ለዝክረ ስምከ  ተጸውዖ ዘቀደመ በአፈ አምለከ አዳም እንበለ ይሰመይ ስመ ሩፋኤል-----ሩፋኤል ሆይ በአምላክ አንደበት የአዳምስም ከመሰየሙ በፊት አስቀድሞ ለተጠራ ስም አጠራረርህ ሰላም እላለሁ

፪, ከ«ለ» ዝርዝር ጋር ተጫፍሮ ፡- ሰላም በ«ለ» ዝርዝር አማካኝነት ሰላምታን ለመስጠትና ለመቀበል ያገለግላል።

ምሳሌ፡- ሰላም ለከ__ ሰላም ለአንተ ይሁን፤ ሰላም ለክሙ__ ሰላም ለእናንተ ይሁን፤

ሰላም ለኪ___ ሰላም ለአንቺ ይሁን፤ ሰላም ለክን ___ ሰላም ለእናንተ ይሁን

ከላይ ያሉትን ሀሳቦች ለመረዳት የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

፩, ጳውሎስና አስቴር የመንግሥት ሠራተኞች ናቸው። ሁለቱም ባለትዳሮች ናቸው። ነገር ግን ልጅ አልወለዱም። በአንድ ወቅት ታክሲ ውስጥ ይገናኛሉ።

ጳውሎስ፡- ሰላም ለኪ አስቴር።

አስቴር፡- ሰላም ለከ ጳውሎስ።

ጳውሎስ፡- እግዚአብሔር ይሰባሕ። ሰላም ይእቲ እኀትኪ።

አስቴር፡- አኮ ዳኅና ንዑስ ሕማም ሐመማ።

ጳውሎስ፡- አኀዝን ባህቱ ከመይኄይሳ እሴፎ።

፪, ዮሐንስና ዳንኤል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በአንድ ትምህርት ቤት ነበር። አሁን ደግሞ ሁለቱም በአንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም እየተማሩ የፀገኛሉ። በአንድ ወቅት ወደ ግቢ አየሄዱ እያለ መንገድ ላይ ተገናኙ።

ዮሐንስ፡- ሰላም ለከ ዳንኤል።

ዳንኤል፡- ሰላም ለከ ዮሐንስ።

ዮሐንስ፡- እፎ ውእቱ ትምህርት ወጽንዐተ ትምህርት።

ዳንኤል፡- ሠናይ። እግዚአብሔር ይሰባሕ። ለከሰ።

ዮሐንስ፡- ሊተሰ ኢኮነ ሊተ

ዳንኤል፡- እፎ ኢኮንከኑ ዳኅና። ወበዝ ሰሙነ ዕለታት ኢርኢኩከ ውስተ ቤተ መጽሐፍት።

ዮሐንስ፡- እወ ቤተ መጽሐፍት ኢአተውኩ በእንተ ሐመምኒ ንዑስ ሕማም።

ዳንኤል፡- ምንተከ ሐመከ።

ዮሐንስ፡- ጽፋተ ርእስ፣ ሕማመ ቁልቁሊት፣ ሕማመ ቃርሕ እኂዞኒ ቦ።

ዳንኤል፡- ናሁ እፎ አንተ፤ ኢሖርከኑ ኀበ ቤተ ጥዒና።

ዮሐንስ፡- ሐዊርየ ቦ። እንዘ እወስድ መድኀኒት ውእቱ ዘሀሎኩ።

ዳንኤል፡- ናሁ እፎ ኮንከ።

ዮሐንስ፡- ናሁሰ እግዚአብሔር ይሴባሕ ዳኅና አነ።

## ማስታወሻ፡-

- ሰላም በ«ለ» ሲዘረዘር ቀጥታ ትርጉሙ ሰላም ላንተ ይሁን ቢሆንም ከዚህ በተጨማሪ በሚመችን መልኩ ልንተረጉመው እንችላለን። ምሳሌ፡- ሰላም ለከ------ሰላም አደርህ፣ ሰላም አረፈድህ፣ ሰላም ዋልህ፣ ሰላም አመሸህ።

-----እንዴት አደርህ/አረፈድህ/ዋልህ/አመሸህ/ደኅና ነህ።

- ሰላም በ«ለ» ሲዘረዘር የሚረባው በአብዛኛው ለሁለተኛ መደቦች ብቻ ነው። ነገር ግን መልእክት ለመላክ ሲባል ሌሎችንም ልንልክ እንችላለን።

ምሳሌ፡- ሰላምየ አብጽሕ ሎሙ ----- ሰላምታየን ለእርሱ አድርሱልኝ/ሰላም በልልኝ።

- በግእዝ ቋንቋ አንድ ዓይነት ሰላምታ ሂደት አለ። ይህም ማለት በእድሜ ትልቅ ለሆኑ ለከበሩ ሰዎችም በእድሜ ላነሱ ሰዎችም የምናቀርበው ሰላምታ አንድ ዓይነት ነው።

ምሳሌ፡- ወአቡነሰ ቅዱስ ተክለሃይማኖት ቤተ ኩሎ ሌሊተ እንዘ ይትሐሰይ በመንፈስ ቅዱስ ዘኀደረ ላዕሌሁ

---- አባታችን ቅዱስ ተክለሃይማኖት ግን በእርሱ ላይ ባደረ በመንፈስ ቅዱስ ሲደሰት ሌሊቱን ሁሉ አደረ።

ወይቤልዎ ለቅዱስ አቡነ፡ አንተሰ ተክለሃይማኖት። አልብነ ሰብእ ዘይሰመይ በዝንቱ ስም።

---- ቅዱስ አባታችንን አሉት። ተክለሃይማኖት አንተ ነህ። በዚህ ስም የተጠራ ሰው የለንም።

- ነገር ግን በዕድሜ የሚበልጡንን ሰዎች ለማክበር የተለያዩ ቃለ አጋኖዎችን ልንጠቀም እንችላለን። በአብዛኛው ሌሎችን የምናከብረዎ ራሳችንን ዝቅ በማድረግ ነው።

ምሳሌ፡- አ አቡየ መጻእኩ ኀቤከ። ምንተ ተኀሥሥ።----- አባቴ ሆይ ወደ አንተ መጣሁ። ምን ትፈልጋለህ።

ነየ ገብርከ። ----- እነሆኝ ባሪያህ።

## ለ, እፎ

"እፎ" እንደ ሰላም በብዛት ሰላምታ ለመስጠትም ሆነ ለመቀበል እንጠቀምበታለን። ነገር ግን እፎን የምንጠቀመው ብቻውን አይደለም። ከሌሎች ቃላት ጋር በማጫፈር ነው። ከዚህም በተጨማሪ እንደ ሰላም ሰላምታው አጠቃለን መናገር ስለማንችል መጥቀስ የምንፈልገውን ለይተን እንጠቀምበታለን። እንደሚከተለው ከሌሎች ቃላት ጋር እናጫፍረዋለን።

እፎ ኀደርከ፤ እፎ ኀደርኪ፤ እፎ አንጋህከ፤ እፎ ወዐልከ፣ እፎ አምሰይከ፣ እፎ ከረምከ፣ እፎ ሐገይከ፣ እፎ ሀሎከ።

_እንዴት አደርህ፤ እንዴት አደርሽ፤ እንዴት አነጋህ፤ እንዴት ዋልህ፤ እንዴት አመሸህ፤ እንዴት ከረምህ፤ እንዴት ባጀህ፤ እንዴት አለህ።

ይህንን ግልፅ ለማድረግ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

፩, ኢሳይያስና ኪሩቤል ትናንትና ማታ አብረው ሲያጠኑ አምሽተው ከተለያዩ በኋላ ጥዋት ላይ ክፍል ውስጥ ተገናኙ።

ኪሩቤል፡- እፎ ኀደርከ እኁየ ኢሳይያስ

ኢሳይያስ፡- ዳኅና እግዚአብሔር ይሰባሕ። እፎ አንተ።

ኪሩቤል፡-ዳኅና። ትማለም ምሴት እንተ አፅናዕኖ ተእኅዘኑ ለከ።

ኢሳይያስ፡- ምንተ ኢይብል። በንዑሱ ነሚእየሁ ሀሎኩ። ለከሰ እፎ ውእቱ።

ኪሩቤል፡- ሊተሰ ከብደኒ። ምንተ በከመ ይኄይሰኒ እንዳኢ።

ኢሳይያስ፡- ኢትደንግፅ። ኩሎ ትምህርተ ነሚኦ በዋሕድ ዕለት ይከብድ። በበህቅ ትእኅዞ።

፪, ማርታና ኤልያስ የቅርብ ጓደኞሞች ናቸው። ጠዋት ተገናኝተው ከተጨዋወቱ በኋላ ተለያይተው አሁን ምሽት አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ተገናኙ።

ኤልያስ፡- እፎ አምሰይኪ ፍቅርትየ ማርታ።

ማርታ፡- ዳኅና። እፎ አምሰይከ ፍቅርየ ኤልያስ።

ኤልያስ፡- እግዚአብሔር ይሰባሕ። እምድኅረ ተለያልዮትነ።

ማርታ፡- እምድኅረ ሖርነ ኀበ ቤተክርስቲያን በእንተ ኩሉ ነገሮ ዘረከብክዎ በህየ በዐቢይ ውእቱ ዘተፈሣሕኩ። ለከሰ።

ኤልያስ፡- ሊተሰ በከመተአምረኒ ግብረ ዓለማዊ እንዘ እገብር ውእቱ ዘወዐልኩ ለምንተ ከማኪ ከመእኩን ኢትገብርኒ።

ማርታ፡- በእንተ ኮነ ቀሊል ድኅረዝንቱ ዕለት እጸውአከ ወንሐውር ኀቢረነ። ጌሠም በዓለ ማርያም ውእቱ። በእንተዝ ወጢነነ

ጌሠም ነሐውር ኀቢረነ።

ኤልያስ፡- በዐቢይ እትፌሣሕ። ጸውእኒ እንዘተሐውሪ።

ማርታ፡- በእንተዝ ሰኪበነ በጊዜ ጌሠም ሌሊተ እመንትራከብ ሠናይ ይመስለኒ።

ኤልያስ፡- በዐቢይ ሠናይ ሕሊና። ናሁ ዳኅና ኅድሪ።

ማርታ፡- አሆ ዳኅና ኅደር።

## ሐ, በሓ

«በሓ»ም እንደ ሰላምና እፎ ሰላምታ ለመስጠትና ለመቀበል የሚያገለግል ቃል ነው። አገባቡም የሚከተለውን ይመስላል።

ሀ, ብቻውን ምንም ቀለም ሳይጨመርበት፡-

- በሓ በልዋ ወተሳለምዋ ለቤተክርሰቲያን---- ቤተክርስቲያንን ተሳለሟት። ሰላምም በሏት።

- እምነ ብሓ ቅድስት ቤተክርስቲያን  ሥርጉት አረፋቲሃ---- ቅጥሮቿ ያማሩ/ያጌጡ የሆነች እናታችን የተቀደሰች ቤተክርስቲያን እንዴት አለሽ / ሰላምታ ይገባሻል።

ለ, በሁለተኛ መደብ ተዘርዝሮ፡-

በሓከ---- እንዴት አደርህ ፤ ሰላምታ ይገባሃል/ ይድረስህ ፤ እንዴት አለህ?

በሓክሙ---- እንዴት አደራችሁ፤ ሰላምታ ይድረሳችሁ፤ ሰላምታ ይገባችኋል፤ እንዴት አላችሁ?

በሓኪ----- እንዴት አደርሽ፤ ሰላምታ ይድረስሽ፤ ሰላምታ ይገባሻል፤ እንዴት አለሽ?

በሓክን---- እንዴት አደራችሁ፤ ሰላምታ ይድረሳችሁ፤ ሰላምታ ይገባችኋል፤ እንዴት አላችሁ?

ምሳሌዎች፡-

- ይዎድስዋ መላእክት ለማርያም በውስጠ ውሳጤ መንጦላዕት ወይብልዋ በሓኪ ማርያም ሀዳስዩ ጣዕዋ ----- መላእክት ማርያምን በመንጦላዕት/መጋረጃ/ ውስጥ ያመሰግኗታል። አዲስ ጣዕዋ ላንቺ ምስጋና ይገባሻልም ይሏታል።
- በሓከ አዳም ንጉሠ ሰማይ ወምድር ---- የሰማይና የምድር ንጉሥ አዳም ሆይ ሰላምታ ይገባሃል።

## ማስታወሻ፡-

- «በሓ»ን በሰላምታነት ስንጠቀምበት እፎ አይገባበትም። ”በሓከ አዳም ንጉሠ ሰማይ ወምድር” ይላል እንጅ “እፎ በሓከ አዳም ንጉሠ ሰማይ ወምድር” አይልም።

**ምልማድ ፲**

ሀ, ከዚህ በታች የተጓደሉ የሰላምታ አሰጣጥ ሂደቶች አሉ።የተጓደለውን በራሳችሁ አባባል አሟሉ።

- ሰላም ኀደርከ እኍየ።
- ________________።
- ሕማመከ ሰሚዕየ ቦ። ናሁሰ እፎ ሀሎከ።
- ________________።
- ኢሖርከኑ ኀበ ቤተጥዒና።
- ________________
- ናሁሰ እፎ ሀሎከ እምድኅረ ገበርከ ዘንተ ግብረ።
- ________________።
- ________________።
- ዳኅና
- ምንተ ከዊነከ ለነዋኀ ማዕል ኢረረከብኩከ።
- ________________።
- እፎ ይእቲ ጅማ። ነፋሳሰ። ሰብአሰ።
- ________________።
- ________________።
- እዎ።
- ________________።
- ________________።
- ________________።
- ________________።
- ሕይዎት መረረኒ እኍየ።
- ______________________።
- ዝንቱሰ ዜና ውእቱ። ናሁሰ ዓለም መራራ ኮነት ብየ። ደኪመከ ደኪመከ አድካመከ ኢትረከብ ባቲ።
- ______________________።

- እስኩ ንሬኢ።

ለ, የሚከተሉትን ሁኔታዎች በጥሞና ካገናዘባችሁ በኋላ በተጠየቃችሁት መሠረት ሰላምታ በግእዝ ቋንቋ አቅርቡ።

፩, ስምዖን ለረጅም ጊዜ ታሞ ሐኪም ቤት ተኝቷል። አሁንም ያለው አዚያው ነው። «ሰላም»ን በመጠቀም ሰላምታ አቅርቡለት።

፪, አሁን ሰዓቱ ከምሽቱ 12፡30 ነው። ቤተ መጽሐፍት ቁጭ ብላችኋል። ባለፈው ሴሚስተር አብራችሁት የተማራችሁትን ጓደኛችሁን ከጎናችሁ ቁጭ ብሎ አገኛችሁት። «እፎ»ን በመጠቀም ሰላምታ አቅርቡለት።

፫, ጴጥሮስ ወደአላችሁበት ከተማ ከመጣ ሁለት ቀናትን አሳልፏል። ልክ ሲመጣ ተዋወቃችሁት። ከዚያም በሁለተኛው ቀን ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄድ አገኛችሁት። «በሐ»ን በመጠቀም ሰላምታ አቅርቡለት።

፬, በቤተክርስቲያናችሁ የሚያገለግሉ አንድ መሪጌታ አገኛችሁ። ግእዝ ቋንቋን መናገር ይችላሉ። የግእዝ ጀማሪ ተማሪ እንደመሆናችሁ መጠን የግእዝን ቋንቋን በመጠቀም ሰላምታችሁን አቅርቡላቸው። «ሰላም»ን፣ «በሐ»ንና «እፎ»ን ተጠቀሙ።

፭, ቅዱሳት መጽሐፍትን አንብቡና የሰላምታ አሰጣጥ ሂደትን ፈልጉ። ከዚያም ያገኛችሁትን ለባለንጀሮቻችሁ አንብቡላቸው።

፮, በክረምት ወቅትና ክረምት ካለፈ በኋላ እንዲሁም በበጋና በጋ ካለፈ በኋላ ሰላምታችሁ ምን ሊመስል ይችላል? ለባለንጀሮቻችሁ ግለፁላቸው።

### ፩.፬.፪ ስንብት

በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት አንድ ሰው ከሌላው ባለንጀራው ጋር ሲለያይ መልካም ምኞቱን የሚገልፅበት የተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም ሂደት አለ። በብዛት ለስንብት የምንጠቀምባቸው ቃላትና ሐረጎች የሚከተሉት ናቸው።

ሰላም ኩን----- ሰላም ሁን ሰላም ኩኒ----- ሰላም ሁኚ ሰላም ኩኑ---- ሰላም ሁኑ ሰላም ኩና----- ሰላም ሁኑ

ሰላም ኀድር/ወዐል/አምሲ----- ሰላም እደር/ ዋል/ አምሽ ሰላም ኀድሩ/ወዐሉ/አምስዩ----- ሰላም እደሩ/ ዋሉ/ አምሹ

ሰላም ኀድሪ/ወዐሊ/አምስዪ------ ሰላም እደሪ/ ዋዪ/ አምሺ ሰላም ኀድራ/ወዐላ/አምስያ----- ሰላም እደሩ/ ዋሉ/ አምሹ

ዳኀና ኩን---- ደህና ሁን ዳኀና ኩኑ---- ደህና ሁኑ ዳኀና ኩኒ---- ደህና ሁኚ ዳኀና ኩና---- ደህና ሁኑ

ዳኀና ኀድር/ወዐል/አምሲ----- ደኅና እደር/ ዋል/አመሽ ዳኀና ኀድሩ/ወዐሉ/አምስዩ------ ደኅና እደሩ/ ዋሉ/አመሹ

ዳኀና ኀድሪ/ወዐሊ/አምስዪ------ ደኅና እደሪ/ ዋዪ/አመሺ ዳኀና ኀድራ/ወዐላ/አምስያ----- ደኅና እደሩ/ ዋሉ/አመሹ

እግዚአብሔር ይኩን ምስሌከ-- እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን

እግዚአብሔር ይኩን ምስሌክሙ--እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን

እግዚአብሔር ይኩን ምስሌኪ----- እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ይሁን

እግዚአብሔር ይኩን ምስሌክን----- እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን

ሠናይ ዕለት ይኩን ለከ---- መልካም ቀን ይሁንልህ ሠናይ ዕለት ይኩን ለክሙ---- መልካም ቀን ይሁንላችሁ

ሠናይ ዕለት ይኩን ለኪ---- መልካም ቀን ይሁንልሽ ሠናይ ዕለት ይኩን ለክን---- መልካም ቀን ይሁንላችሁ

በሰላም ያስተራክበነ------ በሰላም ያገናኘን

ከላይ የተዘረዘሩትን ቃላትና ሐረጋት ይበልጥ ለመረዳት የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

፩, ድሜጥሮስና ሲላስ የሚሠሩት አንድ መሥሪያ ቤት ነው። አሁን ሥራ ጨርሰው ወደየቤታቸውም ይሄዳሉ። ዕለቱ አርብ ከሰዓት ነው።

ድሜጥሮስ፡-እንከሰ ዘንተለያለይ ቦቱ ሰዓት መጽሐ። ለከዊኖቱ በዕለቱ ሠኑይ ለግብር ትመጽእኑ።

ሲላስ፡- እዎ ዘእመጽእ ይመስለኒ። ምንትኑ። አንተሰ ትመጽእኑ።

ድሜጥሮስ፡- እመጽ። ንትራከብ በዝየ። ሰላም ኩን።

ሲላስ፡-በል ኩን ዳኅና እንከሰ። ሠናየ ሰንበተ ይኩን ለከ።

ድሜጥሮስ፡- አሜን። ለኩልነ።

፪, ሄቨን የኮተቤ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ጸሐፊ ናት። አብርሃም ምዝገባ ሊመዘገብ ሲል የተወሰነ እርዳታ አድርጋለታለች። አሁን አብርሃም ምዘገባውን ጨርሶ ሊሄድ ነው።

አብርሃም፡- በእንተ ዘገበርኪ ሊተ ኩሎ ረድኤተ እዌድሰኪ።ናሁ በይነፈጸምኩ ግብርየ ይደልወኒ ከመአሐውር።

ሄቨን፡- አብርሃም ምንትኒ አኮ።

አብርሃም፡- አሆ ዳኅና ኩኒ።

ሄቨን፡- ዳኅና ኩን።

**ምልማድ ፲፩**

ሀ, የሚከተሉትን ንግግሮች በራሳችሁ አባባል ግለፁ።

፩, ጥላሁን እፎ ሀሎከ።

- ----------------።
- ----------------አይቴ ተሐውር።
- ----------------።
- ሠናየ ፀኒአ ለይኩን ለከ።
- -----------------።

፪,

- ሰላም ለኪ ሐና።
- ---------------።
- ሠናይ ሐና። ትከሊኑ እምዝ ትድኅኒ።
- -------------- ሐዊር ብየ።
- ---------------።
- ዳኅና ኩን።

ለ, ከዚህ በታች ያለውን ትዕዛዝ አስተውላችሁበራሳችሁ አባባል በግእዝ ቋንቋ ንግግር አቅርቡ።

እናንተ ስለአንድ ጉዳይ ከአንድ ሰው ጋር እያወራችሁ ቆያችሁ ትንሽ ከቆያችሁ በኋላ ንግግሩን ለማቋረጥ ፈለጋችሁ መሄድ ለምን እንደፈለጋችሁ ምክኒያታችሁን ለሚያናግራችሁ ሰው ግለፁለት። ከዚያም አስፈቅዳችሁ ሂዱ። በመጨረሻ ስለፈቀደላችሁ ሰውየውን አመስግኑትና ተለያዩ። ከላይ ያለውን ነገር የሚያካትት ንግግር በግእዝ ቋንቋ አቅርቡ።

# ምዕራፍ ፪

# ንዑስ አንቀጽ እርባታ እና አዕማድ

## ፪.፩ ንዑስ አንቀጽ እርባታ

አናቅጽ ዐበይት እና ንዑሳን(ደቂቅ) በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡

**ዐበይት አናቅጽ(ዐቢይ አንቀጽ)**

እነዚህ አናቅጽ የተሰጠውን ዐ.ነገር ማሰር የሚችሉ(የማሰር አቅማቸው ከፈተኛ የሆኑ) አናቅጽ ናቸው፡፡ እነዚህም

- ቀዳማይ
- ትንቢት
- ትዕዛዝ አናቅጽ ናቸው፡፡

**ንዑሳን(ደቂቅ አንቀጽ)አናቅጽ**

እነዚህ አናቅጽ የተሰጠውን ዐ.ነገር ማሰር የመይችሉ (የማሰር አቅማቸው በጣም ዝቅተኛ የሆኑ) አናቅጽ ናቸው፡፡ እነዚህም

- ዘንድ
- ዘር/አርእስት
- ሳልስ ውስጠ ዘ
- ሳድስ ውስጠ ዘ
- ቦዝ አንቀጽ ናቸው

ከላይ ከተገለፁት ንዑሳን አናቅጽ ውስጥ በ፲ሩ መራህያን ሊዘረዝሩ የሚችሉት ቦዝ አንቀጽ እና አርዕስት ናቸው፡፡

### ፪.፩.፩ የቦዝ አንቀጽ እርባታ

ቦዝ አንቀጽ ዐ.ነገርን የማሰር አቅሙ በጣም ዝቅተኛ የሆነ የተሰጠውን ግሥ አፍዝዞ እንዲህ አድርጎ እየተባለ ይፈታል፡፡

**የቀተለ ቦዝ አንቀጽ ንዑስ እርባታ**

| **መራሒ** | **ቦዝ አንቀጽ** | **ትርጉም** |
|---|---|---|
| ውእቱ | ቀቲሎ | ገድሎ |
| ውእቶሙ | ቀቲሎሙ | ገድለው |
| ይእቲ | ቀቲላ | ገድላ |
| ውእቶን | ቀቲሎን | ገድለው |
| አንተ | ቀቲለከ | ገድለክ |
| አንትሙ | ቀቲለክሙ | ገድላችው |
| አንቲ | ቀቲለኪ | ገድለሽ |
| አንትን | ቀቲለክን | ገድላችው |
| አነ | ቀቲልየ | ገድዬ |
| ንሕነ | ቀቲለነ | ገድለን |

**ማስታወሻ ፡-**

- በቦዝ አንቀጽ እርባታ ጊዜ በ ሤመ እና በ ቆመ ቤት የተደበቁት የ እና ወ ፊደላት ይወጣሉ፡፡

**ምሳሌ ፡-** ቆመ----- ቀዊሞ፤ቀዊሞሙ፤ቀዊማ፤ቀዊሞን፤ቀዊመከ፤ቀዊመክሙ፤ቀዊመኪ፤ቀዊመክን፤ቀዊምየ፤ቀዊመነ

ሤመ----- ሠዪሞ፤ሠዪሞሙ፤ሠዪማ፤ሠዪሞን፤ሠዪመከ፤ሠዪመክሙ፤ሠዪመኪ፤ሠዪመክን፤ሠዪምየ፤ሠዪመነ

- በሦስት ቀለማት መካከል ሀ ወይም አ ከገባ መነሻው ሳድስ ይሆናል፡፡

**ምሳሌ ፡-** መሐለ ----ምሒሎ፤ምሒሎሙ፤ምሒላ፤ምሒሎን፤ምሒለከ፤ምሒለክሙ፤ምሒለኪ፤ምሒለክን፤ምሒልየ፤ምሒለነ

ሰአለ-----ስኢሎ፤ስኢሎሙ፤ስኢላ፤ስኢሎን፤ስኢለከ፤ስኢለክሙ፤ስኢለኪ፤ስኢለክን፤ስኢልየ፤ስኢለነ

- በግሥ መድረሻ ላይ የ ካለ ቅድመ መድረሻውን ሳድስ ያደርጋል፡፡

ምሳሌ ፡- ጸለየ ጸልዮ ፤ ሠነየ ሠንዮ

- «ወ» በቦዝ አንቀጽ ላይ ተደርቦ ሲነገር በ -----ጊዜ ተብሎ ይፈታል፡፡

ምሳሌ፡ ቀቲሎ = ገድሎ፤ ወቀቲሎ = በገደለ ጊዜ

## ፪.፩.፩ የቦዝ አንቀጽ ዝርዝር እርባታ

፩. ውእቱ ተብዬ አሥሩን መራሕያን ሲያውቃቸው

| | |
|---|---|
| አእሚሮሁ(አውቆት) | አእሚሮክሙ(አውቋችሁ) |
| አእሚሮሆሙ(አውቋቸው) | አእሚሮኪ(አውቆሽ) |
| አእሚሮሃ(አውቋት) | አእሚሮክን(አውቋችሁ) |
| አእሚሮሆን(አውቋቸው) | አእሚሮኒ(አውቆኝ) |
| አእሚሮከ(አውቆህ) | አእሚሮነ(አውቆን) |

**፪. ውእቶሙ ተብዬዎች አሥሩንም መራሕያን ሲያውቋቸው**

| | |
|---|---|
| አእሚሮሙሁ(አውቀውት) | አእሚሮሙክሙ(አውቀዋችሁ) |
| አእሚሮሙሆሙ(አውቀዋቸው) | አእሚሮሙኪ(አውቀውሽ) |
| አእሚሮሙሃ(አውቀዋት) | አእሚሮሙክን(አውቀዋችሁ) |
| አእሚሮሙሆን(አውቀዋቸው) | አእሚሮሙኒ(አውቀውኝ) |
| አእሚሮሙከ(አውቀዉሀ) | አእሚሮሙነ(አውቀውን) |

- ከላይ ያለውን እርባታ በመመልከት ሌሎቹንም እንደዚሁ ማርባት ይቻላል።

**ምልማድ ፩**

**ሀ. የሚከተሉትን አንቀጾች በቦዝ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ እርባታ መሰረት አርቡ**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አእመረ | ሜጠ | በጽሐ | አወፈየ | ሞተ |
| ተመነየ | ሐለመ | አመክነየ | ወረዘወ | ጸውዐ |

**ለ.የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አማረኛ ለውጡ፡፡**

፩. ወመጺአ መምህሮሙ ተንሥኡ አርድእት

፪. ጎዲጎ ተሰዐ ወተሰዐተ ነገደ ወረደ ወልድ

፫. ወሰሚአ ሄሮድስ ንጉሥ ደንገጸ ወተሀውከ

፬. አይቴ ተሐውር ነሲአከ ለንዋይየ

፭ .ወበዊኦሙ ውስተ ቤት ረከብዎ ለሕፃን ምስለ ማርያም እሙ

**ሐ. የሚከተሉትን ወደ ግእዝ ለውጡ**

፩. በነጋ ጊዜ የካህናት አለቆች ተማከሩ

፪. ከሰማይ ወርዶ ፤ከእመቤታችን ተወልዶ፤በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ፤እንደ ሕፃናት በየጥቂቱ አድጎ፤በአይሁድ እጅ ተገርፎ፤በዕለተ አርብ ተሰቅሎ አዳምን ከሲኦል ባርነት ነፃ አወጣው፡፡

፫. በግልጽ ቆሞ ወንጌልን አስተማረ

፬. ምን እንዳደረገ አላውቅም ፡፡ነገር ግን እኛን ባየ ጊዜ ደነገጠ

፭. ሌባው የሴትየዋን ሞባይል ነጥቆ ሲሄድ በፖሊስ ተያዘ

**መ. የሚከተለውን ምሳሌ አድረጋችሁ የቀረውን ዐ.ነገር እናንተ ፃፉ፡፡**

፩.ብእሲ አእሚሮነ ለነ ሖረ ውስተ ብሔሩ(በውእቱ)

፪. አ ብእሲ አእሚረከነ ለነ ሖርከ ውስተ ብሔርከ(በአንተ)

**__፪.፩.፪ የአርእስት እርባታ__**

- አርእስት ወይም ንዑስ አንቀጽ ዐ.ነገርን ማሰር ከማይችሉ አናቅጽ ውስጥ ሲመደቡ በአሥሩ መራሕያን እንደሚከተለው ይረባሉ፡፡
  **ምሳሌ ፡-**
  የቀተለ አርእስት ንዑስ አንቀጽ እርባታ
  ቀተለ ቀቲል/ቀቲሎቱ

| **መራሒ** | **ትርጉም** |
|---|---|
| ቀቲልሁ/ቀቲሎቱ | መግደሉ |
| ቀቲልሆሙ/ቀቲሎቶሙ | መግደላቸው |

| | |
|---|---|
| ቀቲልሃ/ቀቲሎታ | መግደሏ |
| ቀቲልሆን/ቀቲሎቶን | መግደላቸው |
| ቀቲልከ/ቀቲሎትከ | መግደልህ |
| ቀቲልክሙ/ቀቲሎትክሙ | መግደላችሁ |
| ቀቲልኪ/ቀቲሎትኪ | መግደልሽ |
| ቀቲልክን/ቀቲሎትክን | መግደላችሁ |
| ቀቲልየ/ቀቲሎትየ | መግደሌ |
| ቀቲልነ/ቀቲሎትነ | መግደላችን |

## ማስታወሻ ፦

- ፩.ከላይ ያየነው እርባታ ተስቦ(በገቢርነት) እንደሚከተለው ይረባል፡፡

| **መራሒ** | **ትርጉም** |
|---|---|
| ቀቲልሁ/ቀቲሎቶ | መግደሉን |
| ቀቲልሆሙ/ቀቲሎቶሙ | መግደላቸውን |
| ቀቲልሃ/ቀቲሎታ | መግደላን |
| ቀቲልሆን/ቀቲሎቶን | መግደላቸውን |
| ቀቲልከ/ቀቲሎተከ | መግደልህን |
| ቀቲልክሙ/ቀቲሎተክሙ | መግደላችሁን |
| ቀቲልኪ/ቀቲሎተኪ | መግደልሽን |
| ቀቲልክን/ቀቲሎተክን | መግደላችሁን |
| ቀቲልየ/ቀቲሎተየ | መግደሌን |
| ቀቲልነ/ቀቲሎተነ | መግደላችንን |

፪. ካሉት ዘር አወጣጥ ውስጥ ደግሞ ሳቢ ዘር በ፲ ሩ መራሕያን ይዘረዝራል

**ምሳሌ ፡** **ሳቢ ዘር**

| | |
|---|---|
| ቀተለ | ቅትለት (አገዳደል) |
| ሰበከ | ስብከት |
| ወለደ | ልደት |
| ሜጠ | ሚጠት |
| ሖረ | ሑረት |

በ፲ ሩ መራሕያን ሲዘረዝር ደግሞ

ቅትለቱ (አገዳደሉ )  ቅትለትክሙ (አገዳደላችሁ)

ቅትለቶሙ (አገዳደላቸው)  ቅትለትኪ  (አገዳደልሽ)

ቅትለታ ( አገዳደሏ)  ቅትለትክን  (አገዳደላችሁ)

ቅትለቶን  (አገዳደላቸው)  ቅትለትየ  (አገዳደሌ)

ቅትለትከ (አገዳደልህ)  ቅትለትነ  (አገዳደላችን)

፫. ከላይ ያየነው የሳቢ ዘር እርባታ በገቢር ሲዘረዘር የሚከተለውን ይመስላል

ቅትለቶ(አገዳደሉ)  ቅትለተክሙ (አገዳደላችሁን)

ቅትለቶሙ (አገዳደላቸውን)  ቅትለተኪ  (አገዳደልሽን)

ቅትለታ ( አገዳደሏን)  ቅትለተክን  (አገዳደላችሁን)

ቅትለቶን  (አገዳደላቸውን)  ቅትለተየ  (አገዳደሌን)

ቅትለተከ (አገዳደልህን)  ቅትለተነ  (አገዳደላችንን)

፬. ይቤ ምድቡ ከንዑስ አንቀጽ ባይሆንም እርባታ ስናነሳ ግድ እሱን ማየት ስለሚገባን እንደሚከተለው እንመለከተዋለን፡፡

- ይቤ እስከ አሁን ካየናቸው ግሦች ሁሉ የተለየ ባሕርይ አለው፡፡እነዚህም
    - የሌሎቹ ግሦች መድረሻ ፊደላቸው ግእዝ ሲሆን የይቤ ግን ኃምስ ነው፡፡
    - ሌሎቹ ግሦች መድረሻቸው ግእዝ በመሆኑ ተነስተው ሲነበቡ ይቤ ግን ወዳቂ ነው፡፡

- ንዑስ እርባታውም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| **ውእቱ** | **ውእቶሙ** | **ይእቲ** | **ውእቶን** | **አንተ** |
|---|---|---|---|---|
| ይቤ(አለ) | ይቤሉ | ትቤ | ይቤላ | ትቤ |
| ይብል(ይላል) | ይብሉ | ትብል | ይብላ | ትብል |
| ይበል(ይል ዘንድ) | ይበሉ | ትበል | ይበላ | ትበል |
| ይበል(ይበል) | ይበሉ | ትበል | ይበላ | በል |

| **አንትሙ** | **አንቲ** | **አንትን** | **አነ** | **ንሕነ** |
|---|---|---|---|---|
| ትቤሉ | ትቤሊ | ትቤላ | እቤ | ንቤ |
| ትብሉ | ትብሊ | ትብላ | እብል | ንብል |
| ትበሉ | ትበሊ | ትበላ | እበል | ንበል |
| በሉ | በሊ | በላ | እበል | ንበል |

**ምልማድ ፪**

**ሀ. ለሚከተሉት ግሦች አርእስትና ሳቢ ዘር እርባታቸውን ፈልጉ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ወረደ | ፆደ | አተወ | በጽሐ | አእመረ |
| ዔለ | መሐረ | ወድቀ | ረዐየ | ጥዕየ |

**ለ. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ ግእዝ ለውጡ፡፡**

፩. ዳዊት ማዳን የእግዚአብሔር ነው አለ

፪. ስለዚህ ነገር ምን ትላለህ

፫. ሁላችንም የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ይገባሻል እንበል

፬. አቤቱ ይቅር በለን በሉ

፭. እኔ ግን አትሂዱ እላለው

፯. ሰሎሞን አቤልን አንበሳውን ገድለከው ስትሄድ ሴሊት በሕልሜ አየሁህ አለው
፰. ማወቁንስ አወቅሁ ስራ ከየት ይምጣ፡፡ለማንኛውም ጌታ እግዚአብሔር አንተ ታውቃለህ አልኩ በልቤ፡፡
፱. እንግዶች ሆይ እንግዲህ ስለ ግእዝ ቋንቋ ምን ትላላችሁ፡፡
፲. ሕይወታችሁ ምንድን ነው ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ፡፡ስለዚህ ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን በሉ፡፡
፲. ትልቅ ሰው ትልቅ መስሎ የሚታየን ለምንድን ነው ቁጭ ብለን ስለምንመለከተው ነውና ከተቀመጥንበት ወንበር እንነሳ፡፡

## ፪.፪ አዕማድ

### ፪.፪.፩ የአዕማድ ምንነት

በአጠቃላይ የግስ ጠባዮችን ገቢር እና ተገብሮ ብሎ በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡ነገር ግን እነዚህ ሁለቱ ብቻ ቃላትን አሳክተን የምንፈልገውን ሀሳብ ለመግለጽ በቂ አይደሉም፡፡ስለዚህ በተጨናሪ ሦስት ሌላ የግስ ጠባይ ጨምረን አምስት ልናደረጋቸው ይገባናል፡፡ እነዚህ አምስቱ የግስ ጠባዮች አዕማድ ይባላሉ፡፡ አዕማድ(አምስቱ ማዕረጋት) ለግስ እርባታ ሁሉ መነሻ እና መቋቋሚያ ወይም የግስን ዖታ፤የአንቀጽን እርባታ በየቤቱና በየሠራዊቱ ፀንቶ እንዲነገር የሚወስኑ እና ለይተው የሚመሩ ስለሆኑ አዕማድ ወይም አዕማደ ግሥ ተብለዋል፡፡
እነዚህ አምስቱ የግሥ ማዕረጋት የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩. አድራጊ ዐምድ (ገቢረ)
፪. ተደራጊ ዐምድ (ተገብሮ)
፫. አስደራጊ ዐምድ (ገቢር)
፬. ተደራራጊ ዐምድ (ተገብሮ)
፭. አደራራጊ ዐምድ (ገቢር)

**ምሳሌ ፦**

| | |
|---|---|
| ቀተለ(ገደለ) | አድራጊ ዐምድ |
| አቅተለ(አስገደለ) | አስደራጊ ዐምድ |
| ተቀትለ(ተገደለ) | ተደራጊ ዐምድ |
| ተቃተለ(ተገዳደለ) | ተደራራጊ ዐምድ |
| አስተቃተለ(አገዳደለ) | አደራራጊ ዐምድ |

- ግሦች በአምስቱ አዕማድ ሲረቡ ለእርባታቸው ህፀፅና ምልዐት አለው፡፡በምልዐት ሲረቡ አምስቱንም ደረጃ ይወጣሉ፡፡ በህፀፅ ሲረቡ ከአምስት ያነሰ ደረጃን ይወጣሉ፡፡

| ደረጃ | አድራጊ | አስደራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ | አደራራጊ |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ቀተለ | አቅተለ | ተቀተለ | ተቃተለ | አስተቃተለ |
| ፪ | ፈለሰ | አፍለሰ | | ተፋለሰ | አስተፋለሰ |
| ፫ | ሐነጸ | አሕነጸ | ተሐነጸ | | |
| ፬ | ዘነመ | አዝነመ | | | |
| ፭ | ኮነ | | | | |

- ከላይ ባየናቸው አዕማድ ላይ በመነሻ የምናገኛቸው ባዕዳን ፊደላት "ተ፤አ፤አስተ" ልማድ ይባላሉ፡፡
    - "ተ" የመደረግ፤የመደራረግ ልማድ ነው፡፡ነገር ግን ተወከፈ፤ተዘከረ ያለውን የሚመስል ግሥ የማድረግ ሲሆን ይገኛል፡፡ ተ በስድስት ፊደላት ከተነሳ በቀር በሌላ ግሥ ሁሉ በቀዳማይ፤በካልዐይ፤በሣልሣይ ይነገራል፡፡ ስድስት ፊደላት የተባሉት ተ፤ሰ፤ዘ፤ደ፤ጠ፤ፀ፤ጸ ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ ግሥ በቀዳማይ ብቻ ይነገርለታል፡፡

**ምሳሌ፡-**

ተሰብሐ ይሴባሕ፤ይሰባሕ፤ይሰባሕ
ተፀወነ ይፄወን፤ይፀወን፤ይፀወን

❖ “አ” የማስደረግ ልማድ ሲሆን የመደረግና የማድረግ ሆኖ ይገኛል

**ምሳሌ፡-**

አየድዐ ያየድዕ፤ያየድዕ፤ያየድዕ

❖ “አስተ” የማደራረግ ልማድ ሲሆን የመደረግ፤የማድረግ፤የማስደረግ ሆኖ ይገኛል፡፡

**ምሳሌ፡-**

አስተርአየ(አየ፤አሳየ) ፤ አስተብቍዐ(ማለደ)

### ሀ. አድራጊ ዐምድ

- ራሱን ችሎ በሀላፊ አንቀጽ የሚነገር የአዕማድ ሁሉ መሠረት ነው፡፡
  **ምሳሌ ፡-** ቀተለ፤ቀደሰ፤ተንበለ
- አድራጊ ዐምድ ግእዝን፤ራብዕን፤ኃምስን፤ሳብዕን ይስባል፡፡
  **ምሳሌ ፡-**
  ሰበኩ ሐዋርያት ወንጌለ
  ርእየ አንበሳ ውስተ ሐቅል
  ረከበ አርዌ ውስተ ገዳም
  ቀተለ ፀሮ በኲናት

### ለ. አስደራጊ ዐምድ

- በመነሻው ላይ ባዕድ ፊደል “አ” ን በመጨመር ከአድራጊ ግሥ ይመሰረታል
  **ምሳሌ፡-**
  ሐይወ አሕየወ
  ጸሐፈ አጽሐፈ
- አስደራጊ ዐምድ ሁለት ግእዝን ይስባል፡፡
  **ምሳሌ፡-** ያፈቅርዎ ሕዝብ ለባዕል ዘኢብልዐ ነዳየ ኅብስተ

### ሐ. አደራራጊ ዐምድ

- በመነሻው ላይ ባዕድ ፊደል “አስተ” ን በመጨመር ከአድራጊ ዐምድ ይመሰረታል፡፡
  **ምሳሌ**፡- ቀተለ አስተቃተለ
- አደራራጊ ዐምድ ምስለን አጫፍሮ ስምን ይስባል
  **ምሳሌ፡-** አስተቃተለ ሳሙኤል ሳኦልሃ ምስለ አጋግ

### መ. ተደራጊ ዐምድ

- በመነሻ ላይ “ተ” ን በመጨመር ከአድራጊ ዐምድ ይመሰረታል፡፡
  **ምሳሌ፡-** ተቀትለ፤ተቀደሰ
- ተደራጊ ዐምድ ተገብሮ ያደርጋል፡፡
  **ምሳሌ፡-** ተሐንጸ ቤት

### ሠ. ተደራራጊ ዐምድ

- በመነሻው ላይ ባዕድ ፊደል “ተ” ን በመጨመር፤ድኅረ መነሻውን ራብዕ በማድረግ ከአድራጊ ዐምድ ይመሰረታል፡፡
  **ምሳሌ፡-** ተቃተለ፤ተባረከ፤ተናገረ

- ተደራራጊ ዐምድ እርስ በእርሱ በሚደረግ ግብር እየገባ ይሠራል፡፡

**ምሳሌ፡-**

ተቃተለ ዳዊት ምስለ ጎልያድ

መላእክት ተናገሩ ምስለ ጎልያድ

## ፪.፪.፪. የአዕማድ ንዑስ አንቀጽ እረባታ

- ከላይ ያየናቸው አዕማድ በ፲ ሩ መራሕያን እስከ ትዕዛዝ ከቻለም እስከ ሳድስ ውስጠ ዘ ድረስ ይረባል፡፡እርባታውም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**በውእቱ ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተለ(ገደለ) | አቅተለ(አስገደለ) | አስተቃተለ(አገዳደለ) | ተቀትለ(ተገደለ) | ተቃተለ(ተገዳደለ) |
| ይቀትል(ይገድላል) | ያቀትል(ያስገድላል) | ያስተቃትል(ያገዳድላል) | ይትቀተል(ይገደላል) | ይትቃተል(ይገዳደላል) |
| ይቅትል<br>(ይገድል ዘንድ) | ያቅትል<br>(ያስገድል ዘንድ) | ያስተቃትል<br>(ያገዳድል ዘንድ) | ይትቀተል<br>(ይገደል ዘንድ) | ይትቃተል<br>(ይገዳደል ዘንድ) |
| ይቅትል(ይግደል) | ያቅትል(ያስገድል) | ያስተቃትል(ያገዳድል) | ይትቀተል(ይገደል) | ይትቃተል(ይገዳደል) |

**በውእቶሙ ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተሉ(ገደሉ) | አቅተሉ(አስገደሉ) | አስተቃተሉ(አገዳደሉ) | ተቀትሉ(ተገደሉ) | ተቃተሉ(ተገዳደሉ) |
| ይቀትሉ(ይገድላሉ) | ያቀትሉ(ያስገድላሉ) | ያስተቃትሉ(ያገዳድላሉ) | ይትቀተሉ(ይገደላሉ) | ይትቃተሉ(ይገዳደላሉ) |
| ይቅትሉ<br>(ይገድሉ ዘንድ) | ያቅትሉ<br>(ያስገድሉ ዘንድ) | ያስተቃትሉ<br>(ያገዳድሉ ዘንድ) | ይትቀተሉ<br>(ይገደሉ ዘንድ) | ይትቃተሉ<br>(ይገዳደሉ ዘንድ) |
| ይቅትሉ(ይግደሉ) | ያቅትሉ(ያስገድሉ) | ያስተቃትሉ(ያገዳድሉ) | ይትቀተሉ(ይገደሉ) | ይትቃተሉ(ይገዳደሉ) |

**በይእቲ ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተለት(ገደለች) | አቅተለት(አስገደለች) | አስተቃተለት(አገዳደለች) | ተቀትለት(ተገደለች) | ተቃተለት(ተገዳደለች) |
| ትቀትል(ትገድላለች) | ታቀትል(ታስገድላለች) | ታስተቃትል(ታገዳድላለች) | ትትቀተል<br>(ትገደላለች) | ትትቃተል<br>(ትገዳደላለች) |
| ትቅትል<br>(ትገድል ዘንድ) | ታቅትል<br>(ታስገድል ዘንድ) | ታስተቃትል<br>(ታገዳድል ዘንድ) | ትትቀተል<br>(ትገደል ዘንድ) | ትትቃተል<br>(ትገዳደል ዘንድ) |
| ትቅትል(ትግደል) | ታቅትል(ታስገድል) | ታስተቃትል(ታገዳድል) | ትትቀተል(ትገደል) | ትትቃተል(ትገዳደል) |

**በውእቶን ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተላ(ገደሉ) | አቅተላ(አስገደሉ) | አስተቃተላ(አገዳደሉ) | ተቀትላ(ተገደሉ) | ተቃተላ(ተገዳደሉ) |
| ይቀትላ<br>(ይገድላሉ) | ያቀትላ<br>(ያስገድላሉ) | ያስተቃትላ<br>(ያገዳድላሉ) | ይትቀተላ<br>(ይገደላሉ) | ይትቃተላ<br>(ይገዳደላሉ) |
| ይቅትላ<br>(ይገድሉ ዘንድ) | ያቅትላ<br>(ያስገድሉ ዘንድ) | ያስተቃትላ<br>(ያገዳድሉ ዘንድ) | ይትቀተላ<br>(ይገደሉ ዘንድ) | ይትቃተላ<br>(ይገዳደሉ ዘንድ) |
| ይቅትላ<br>(ይግደሉ) | ያቅትላ<br>(ያስገድሉ) | ያስተቃትላ<br>(ያገዳድሉ) | ይትቀተላ<br>(ይገደሉ) | ይትቃተላ<br>(ይገዳደሉ) |

**በአንተ ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተልከ(ገደልህ) | አቅተልከ(አስገደልህ) | አስተቃተልከ(አገዳደልህ) | ተቀተልከ(ተገደልህ) | ተቃተልከ(ተገዳደልህ) |
| ትቀትል (ትገድላለህ) | ታቀትል (ታስገድላለህ) | ታስተቃትል (ታገዳድላለህ) | ትትቀተል (ትገደላለህ) | ትትቃተል (ትገዳደላለህ) |
| ትቅትል (ትገድል ዘንድ) | ታቅትል (ታስገድል ዘንድ) | ታስተቃትል (ታገዳድል ዘንድ) | ትትቀተል (ትገደል ዘንድ) | ትትቃተል (ትገዳደል ዘንድ) |
| ቅትል(ግደል) | አቅትል(አስገድል) | አስተቃትል(አገዳድል) | ተቀተል(ተገደል) | ተቃተል(ተገዳደል) |

**በአንትሙ ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተልክሙ(ገደላችሁ ) | አቅተልክሙ(አስገደላችሁ ) | አስተቃተልክሙ(አገዳደላች ሁ) | ተቀተልክሙ (ተገደላችሁ) | ተቃተልክሙ (ተገዳደላችሁ) |
| ትቀትሉ (ትገድላላችሁ) | ታቀትሉ (ታስገድላላችሁ) | ታስተቃትሉ (ታገዳድላላችሁ) | ትትቀተሉ (ትገደላላችሁ) | ትትቃተሉ (ትገዳደላላችሁ) |
| ትቅትሉ (ትገድሉ ዘንድ) | ታቅትሉ (ታስገድሉ ዘንድ) | ታስተቃትሉ (ታገዳድሉ ዘንድ) | ትትቀተሉ (ትገደሉ ዘንድ) | ትትቃተሉ (ትገዳደሉ ዘንድ) |
| ቅትሉ(ግደሉ) | አቅትሉ(አስገድሉ) | አስተቃትሉ(አገዳድሉ) | ተቀተሉ(ተገደሉ) | ተቃተሉ(ተገዳደሉ) |

**በአንቲ ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተልኪ(ገደልሽ) | አቅተልኪ(አስገደልሽ) | አስተቃተልኪ(አገዳደልሽ) | ተቀተልኪ(ተገደልሽ) | ተቃተልኪ(ተገዳደልሽ) |
| ትቀትሊ (ትገድያለሽ) | ታቀትሊ (ታስገድያለሽ) | ታስተቃትሊ (ታገዳድያለሽ) | ትትቀተሊ (ትገደያለሽ) | ትትቃተሊ (ትገዳደያለሽ) |
| ትቅትሊ (ትገድዪ ዘንድ) | ታቅትሊ (ታስገድዪ ዘንድ) | ታስተቃትሊ (ታገዳድዪ ዘንድ) | ትትቀተሊ (ትገደዪ ዘንድ) | ትትቃተሊ (ትገዳደዪ ዘንድ) |
| ቅትሊ(ግደይ) | አቅትሊ(አስገድዪ) | አስተቃትሊ(አገዳድዪ) | ተቀተሊ(ተገደዪ) | ተቃተሊ(ተገዳደዪ) |

**በአንትን ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተልክን(ገደላችሁ) | አቅተልክን(አስገደላችሁ) | አስተቃተልክን (አገዳደላችሁ) | ተቀተልክን(ተገደላችሁ) | ተቃተልክን (ተገዳደላች) |
| ትቀትላ(ትገድላላችሁ) | ታቀትላ (ታስገድላላችሁ) | ታስተቃትላ (ታገዳድላላችሁ) | ትትቀተላ (ትገደላላችሁ) | ትትቃተላ (ትገዳደላላችሁ) |
| ትቅትላ (ትገድሉ ዘንድ) | ታቅትላ (ታስገድሉ ዘንድ) | ታስተቃትላ (ታገዳድሉ ዘንድ) | ትትቀተላ (ትገደሉ ዘንድ) | ትትቃተላ (ትገዳደሉ ዘንድ) |
| ቅትላ(ግደሉ) | አቅትላ(አስገድሉ) | አስተቃትላ(አገዳድሉ) | ተቀተላ(ተገደሉ) | ተቃተላ(ተገዳደሉ) |

**በአነ ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተልኩ(ገደልሁ) | አቅተልኩ(አስገደልሁ) | አስተቃተልኩ(አገዳደልሁ) | ተቀተልኩ(ተገደልሁ) | ተቃተልኩ(ተገዳደልሁ) |
| እቀትል(እገድላለሁ) | ኣቀትል(አስገድላለሁ) | ኣስተቃትል(አገዳድላለሁ) | እትቀተል(እገደላለሁ) | እትቃተል(እገዳደላለሁ) |
| እቅትል (እገድል ዘንድ) | ኣቅትል (አስገድል ዘንድ) | ኣስተቃትል (አገዳድል ዘንድ) | እትቀተል (እገደል ዘንድ) | እትቃተል (እገዳደል ዘንድ) |
| እቅትል(ልግደል) | ኣቅትል(ላስገድል) | ኣስተቃትል(ላገዳድል) | እትቀተል(ልገደል) | እትቃተል(ልገዳደል) |

**በንሕነ ባለቤትነት**

| አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተልነ(ገደልን) | አቅተልነ(አስገደልን) | አስተቃተልነ(አገዳደልን) | ተቀተልነ(ተገደልን) | ተቃተልነ(ተገዳደልን) |
| ንቀትል (እንገድላለን) | ናቀትል (እናስገድላለን) | ናስተቃትል (እናገዳድላለን) | ንትቀተል (እገደላለን) | ንትቃተል (እንገዳደላለን) |
| ንቅትል (እንገድል ዘንድ) | ናቅትል (እናስገድል ዘንድ) | ናስተቃትል (እናገዳድል ዘንድ) | ንትቀተል (እንገደል ዘንድ) | ንትቃተል (እንገዳደል ዘንድ) |
| ንቅትል(እንግደል) | ናቅትል(እናስገድል) | ናስተቃትል(እናገዳድል) | ንትቀተል(እንገደል) | ንትቃተል(እንገዳደል) |

**፪.፪. ፫ የቦዝ አንቀጽ አዕማድ እርባታ**

- ከላይ ያየነው አንቀጽ በአምስቱ ማዕረጋት እንደሚከተለው ይዘረዘራል፡፡

| ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አንተ |
|---|---|---|---|---|
| ቀቲሎ(ገድሎ) | ቀቲሎሙ(ገድለው) | ቀቲላ(ገድላ) | ቀቲሎን(ገድለው) | ቀቲለከ(ገድለህ) |
| አቅቲሎ(አስገድሎ) | አቅቲሎሙ(አስገድለው) | አቅቲላ(አስገድላ) | አቅቲሎን(አስገድለው) | አቅቲለከ(አስገድለህ) |
| ተቀቲሎ(ተገድሎ) | ተቀቲሎሙ(ተገድለው) | ተቀቲላ(ተገድላ) | ተቀቲሎን(ተገድለው) | ተቀቲለከ(ተገድለህ) |
| ተቃቲሎ(ተገዳድሎ) | ተቃቲሎሙ(ተገዳድለው) | ተቃቲላ(ተገዳድላ) | ተቃቲሎን(ተገዳድለው) | ተቃቲለከ(ተገዳድለህ) |
| አስተቃቲሎ (አገዳድሎ) | አስተቃቲሎሙ (አገዳድለው) | አስተቃቲላ (አገዳድላ) | አስተቃቲሎን (አገዳድለው) | አስተቃቲለከ (አገዳድለህ) |

| አንትሙ | አንቲ | አንትን | አነ | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|
| ቀቲለክሙ(ገድላችሁ) | ቀቲለኪ(ገድለሽ) | ቀቲለክን(ገድላችሁ) | ቀቲልየ(ገድዬ) | ቀቲለነ(ገድለን) |
| አቅቲለክሙ(አስገድላችሁ) | አቅቲለኪ(አስገድለሽ) | አቅቲለክን(አስገድላችሁ) | አቅቲልየ(አስገድዬ) | አቅቲለነ(አስገድለን) |
| ተቀቲለክሙ(ተገድላችሁ) | ተቀቲለኪ(ተገድለሽ) | ተቀቲለክን(ተገድላችሁ) | ተቀቲልየ(ተገድዬ) | ተቀቲለነ(ተገድለን) |
| ተቃቲለክሙ(ተገዳድለችሁ) | ተቃቲለኪ(ተገዳድለሽ) | ተቃቲለክን(ተገዳድላችሁ) | ተቃቲልየ(ተገዳድዬ) | ተቃቲለነ(ተገዳድለን) |
| አስተቃቲለክሙ (አገዳድላችሁ) | አስተቃቲለኪ (አገዳድለሽ) | አስተቃቲለክን (አገዳድላችሁ) | አስተቃቲልየ (አገዳድዬ) | አስተቃቲለነ (አገዳድለን) |

**ምልማድ ፫**

***ሀ. የሚከተሉትን አንቀጽ አምዳቸውን እየለየህ ገቢር ወይም ተገብሮ መሆናቸውን ግለጽ፡፡***

፩. ተብህለ ፪. አስተናበበ ፫ .ተባረከ ፬. አስምዐ ፭. ተረጐመ

***ለ. ለሚከተሉት ቃላት አዕማዳቸውን (አምስቱን ማዕረጋት) ጻፍላቸው፡፡***

፩. ተረፈ

፪. አመረ

## ፪.፫ ንባበ ልሳነ ግእዝ

**፪.፫.፩ ትውውቅ (ራስና ለሰዎች ማስተዋወቅ፤ ሌላ ሰውን ለሌላ ሰው ማስተዋወቅ)**

አንድ ሰው ከማውቀው ሰው ጋር ሲገናኝ ራሱን በግእዝ እንዴት ሊስተዋውቅ እንደሚችል፤ እንዲሁም ባልንጀራውን ለሌላ ሰው በግእዝ እንዴት ሊስተዋውቅ እንደሚችል እንመለከታለን፡፡

አንድ ሰው ራሱን ለሌሎች ለማስተዋወቅ በብዛት የሚጠቀምባቸው ዐ/ነገራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አንሰ እሰመይ አቤል
- አንሰ እትበሀል አቤል
- አነ አቤል ውእቱ
- ስምየ አቤል ውእቱ

አንድ ሰው ባልንጀራውን ለሌሎች ሲያስተዋወቅ በብዛት የሚጠቀምባቸው ዐ/ነገራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አንተ ብእሲ አእምሮ ለዝንቱ ብእሲ
- አስቴር ዑቂዮ ለዝንቱ ብእሲ
- ዝንቱ ብእሲ ይሰመይ አቤል
- ዝንቱ ብእሲ ይትበሀል ዳዊት

ይህንንም ለመረዳት እንድንችል የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት

1, ሰሎሞን የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነው። ከሁለት የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ጋር መንገድ ላይ ተገናኙ።

ሰለሞን፡- እፎ ወዐልክሙ አኃውየ።

ሁለቱ ተማሪዎች፡-ዳኅና እግዚአብሔር ይሴባሕ። እፎ ወዐልከ እኁነ።

ሰለሞን፡-ኀበ አይቴ ውእቱ ዘተሐውሩ አኃውየ።

ሁለቱ ተማሪዎች፡- ኀበ ከኒሳ ንሕነ።

ሰለሞን፡-ትፈቅዱኑ ሊተ እሑር ምስሌክሙ።

ሁለቱ ተማሪዎች፡- ለይኩን / ሠናይ ንትፌሳሕ።

ሰለሞን፡-ንትኣመር በበይናቲነ፡፡አንሰ እሰመይ ሰሎሞን፤ ዘካልኣይ ዓመት መርድአ ጥዒና አነ፤ ክፍለ ቀድሶትየ ክፍለ ትምህርት ውእቱ።

ሶፎንያስ፡-አንሰ እሰመይ ሶፎንያስ ዘዋሕድ ዓመት መርድአ ሐተታ አነ፡፡ ክፍለ ቀድሶት አልብየ በእንተ ወጣኒ አነ።

ሔኖክ፡- እሰመይ ሔኖክ አነኒ ከመ ሶፎንያስ ዘዋሕድ ዓመት መርድአ ሐተታ አነ፡፡ ክፍለ ቀድሶት አልብየ በእንተ ዘኮንኩ ወጣኒ።

ሰለሞን፡-ድኅረዝ አመ ትሬእዩኒ ጸውዑኒ በስምየ ወአምኑኒ፡፡ ምንትመ ኢያጽዕቀክሙ ንግሩኒ ዘተኀሥሡ።

ሁለቱ ተማሪዎች፡- እሆ እኁነ ንሴብሐከ።

ሰለሞን፡- ሰላም ኩኑ።

2, ሰዐቱ የምሳ ሰዐት ነው፤ ሰብለ በዛብህን ለቀድሞ ባልንጀራዋ ሶስና እያስተዋወቀች ነው፡፡

ሰብለ፡-ሶስና ተአምሪዮኑ ለፍቁርየ በዛብህ፡፡

ሶስና፡-ኢየአምሮ፡፡

ሰብለ፡-እሆ ናሁ አስተኣምረኪ ምስሌሁ፡፡ በዛብህ ይትበሐል፡፡

ሶስና፡- አሆ በዛብህ አንሰ እሰመይ ሶስና ፡፡

በዛብህ፡-አሆ ሶስና

ሰብለ፡- ሶስና ዘቀዳሚ ቢጽየ ይእቲ፡፡ ምስሌየ ዘተምህረት ቢጽየ ይእቲ፡፡ ናሁ በመዝገበ ንዋይ በዘኀለፎ ዓመት ተባሪካ ውስተ ጅማ ግብር እኂዛ ሀለዎት፡፡

በዛብህ፡- ኀቡረኑ ዘትገብሩ

ሰብለ፡-አኮ ኀቡረ ዘንገብር ፡፡ ጊዜ ምሳሕ ግብተ ተራከብነ፡፡

ሶስና፡-ሰብለ ለምንት እስከ ናሁ ኢስተኣመርክኒ ምስሌሁ፡፡

ሰብለ፡-ናሁኬ አስተኣመርኩክሙ።

**ምልማድ ፬**

1 በሚከተሉት ሁኔታዎች ተመስርታችሁ ንግግር አዘጋጁ፡፡

ሀ. ሰላማዊት የምትባል ልጅን አጠገብህ ላለው ሰው አስተዋውቅ፡፡ሰላማዊት ጂማ ዩኒቨርሲቲ ተመርቃ አዲስ አበባ ውስጥ የምትሰራ  የግእዝ ተማሪ ናት፡፡

ለ. ለረጅም ጊዜ ተለይቶአችሁ የቆየው በርናባስ አሁን ከአሜሪካን አገር መጥቶአል፡፡ በርናባስ የሰፈራችሁ ልጅ ነው፡፡ በርናባስን አብረዋችሁ ለሚማሩ ወንድሞቻችሁ/እኅቶቻችሁ አስተዋውቁ፡፡

ሐ. ኤልሳቤጥ የክፍልህ ተማሪ ናት፡፡ ነገር ግን ሰላም ተባብላችሁ አታውቁም፡፡አሁን ከኤልሳቤጥ ጋር ተገናኛችሁ ፡፡ ከኤልሳቤጥ ጋር ተዋወቁ/ስለ ትምህርት ተነጋገሩ፡፡

4. እርሱ የማያውቅህ አንተ ግን የምታውቀው የግእዝ ተማሪ መንገድ ላይ አገኘህ፡፡ ከእርሱ ጋር ተዋወቅ ስለ ግእዝ ትምህርት አሰጣጥ ተወያዩ፡፡

# ምዕራፍ ፫

## ክፍላተ ንግግር

ሰው ሀሳቡን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ የሚለጽባቸው ቃላት ክፍላተ ንግግር ይባላሉ። የማንኛውም ቋንቋ ሥልቱ ተመርምሮ እንደ ቋንቋው ሥልትና ብልፅግና የንግግር ክፍሉ ይወሰናል። ክፍላተ ንግግሮች በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ቁጥራቸው የለያየ ነው። በዚህም መሠረት በግእዝ ቋንቋ አሥራ አንድ የንግግር ክፍሎች አሉ። አነዚህም ከዚህ በታች በንፅፅር በሦስት ቋንቋዎች ቀርበዋል።

| ግእዝ | አማርኛ | እንግሊዘኛ |
|---|---|---|
| ስም | ስም | Noun |
| መስተአምር | ማሳወቂያ | Article |
| ቅጽል | የስም ገላጪ | Adjective |
| ተውላጠ ስም | የስም ምትክ | Pronoun |
| ግሥ | ግሥ | Verb |
| ተውሳከ ግሥ | አነቀጽ አጎላማሽ | Adverb |
| ደቂቅ አገባብ | መስተዋድድ | Preposition |
| ንዑስ አገባብ | መስተዋድድ | Conjunction |
| ዐቢይ አገባብ | መስተዋድድ | << << |
| ኣዳማቂ | አዳማቂ | << << |
| ቃለ አጋኖ | ቃለ አጋኖ | Exclamation |

**ማስታዎሻ፡-**

- ♣ ክፍላተ ንግግርና የቃል ክፍል አንድ ዓይነት ትርጉም የላቸውም።የቃል ክፍሎች ሀሳብን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ከመግለጻቸው በተጨማሪ ራሳቸውን ችለው ይቆማሉ።መዚህም መሠረት መስተአምር፣ አዳማቂና ቃለ አጋኖ ከቃል ክፍል አይመደቡም።ነገር ግን የንግግር ክፍሎች ናቸው።

### ፫.፩ ስም

#### ፫.፩.፩ የስም ምንነት

ስም ማንኛውም ህላዌ ወይም ኑዋሪ ፍጥረት ሰውም ሆነ እንስሳ፣ አምላክም ሆነ መልአክ፣ ባሕርይ ወይም አካል ያለውም የሌለውም ሁሉ የሚጠራበት ቃል ነው።

ምሳሌ፡- ሰብእ፣ እንስሳ፣ ጳውሎስ፣ ሕይዎት፣ ባሕር፣ ወዘተ…

ስሞች ሁሉ በሁለት ዋናዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። እነዚህም፡-

ሀ, ውልድ ስም/ዘር/

ለ, ነባር ስም ናቸው።

***ሀ, ውልድ ስም***፡- ይህ ስም ከግሥ የተገኘ ወይም የተወለደ ስም ማለት ነው።በዚህ ስም ውስጥ የሚጠቀሱት ዘር አወጣጦች የሚከተሉት ናቸው።

- ዘመድ ዘር
- ባዕድ ዘር
- ዘር
- ምዕላድ ናቸው።

ማስታዎሻ፡- ዘር የምንለው ባዕድ ዘር፣ ዘመድ ዘር፣ሳቢ ዘር፣ ጥሬ ዘርና ሌሎችንም የግሥ ዘሮች ነው።

ምሳሌ፡- ቀተለ፥ ቀትል-አገዳደል-ዘመድ ዘር

፥ ምቅታል፣እቅታል፣ ትቅታል፣ ምስትቅታል፣ እስትቅታል- መግደያ ቦታ- ባዕድ ዘር

# የቀተለ ቤት ሁሉ እንደዚህ ይሆናል።የተለየ አመልካላቸው ውጪ

ቀደሰ፥ ቁድስ- ዘመድ ዘር

፥ መቅደስ፣ ምቅዳስ፣ እቅዳስ፣ ትቅዳስ፣ እስትቅዳስ፣ምስትቅዳስ- የመቀደሻ ቦታ፣ ማስቀደሻ፣ መቃደሻ፣ ማቀዳደሻ፣ መስቀዳደሻ- ባዕድ ዘር

፥ ቅድሳት- ምስጋና- ምዕላድ

፥ ቅዳሴ- ጥሬ ዘር

**ለ, ነባር ስም**፡- ይህ የስም ዓይነት ከግሥ የማይገኝና ለግሥ እርባታ ዘር የማይሆንቃል ማለት ነው።

ምሳሌ፡- ማይ፣ እሳት፣ ምኩራብ ፣ ወዘተ…

**ማስታዎሻ**፡-

ሀ, አንድ ቃል የንግግር ክፍሉ ስም ነው ስንል የሚከተሉትን ሊያሟላ ይገባል።

- በዐ/ነገር ውስጥ ባለቤት ሊሆን የሚችል ቃል ነው።
- በዐ/ነገር ውስጥ ተሳቢ ሊሆን የሚችል ቃል ነው።
- ምዕላዶችን ጨምሮ ወይም ሳይጨምር ሊባዛ ይችላል።
- አመልካች ወይም ጠቋሚ መስተአምሮችን ሊወስድ ይችላል።
- መጠንን፣ ግብርንና ዓይነትን የሚገልጹ ገላጮችን የሚወስድ ቃል ነው።

ለ, ከዘር አወጣጥ ውስጥ ሳቢ ዘር፤ ከግሥ እርባታ ውስጥ ንዑስ አንቀጽ ድርጊት ተቀባዩን ስለሚሰቡ ንዑሳን አናቅጽ ተብለው የግሥ ማዕረግ ቢኖራቸውም ስሞች ናቸው።

ምሳሌ፡- ቀተለ- ቅትልት- መግደል፣ መገደል- ሳቢ ዘር

ነበበ- ነቢብ- መናገር - ንዑስ አንቀጽ

በዐ/ነገር ውስጥ ፥ ቅትለተ ሰብእ ፈድፈደ- ሰውን መግደል በዛ / ተበራከተ/

ነቢበ ጽድቅ ያፈደፍድ ሞገሰ- እውነትን መናገር ተወዳጅነትን ያበዛል።

# ለአጠናን ይመቸን ዘንድ ከላይ የተጠቀሱትን የስም ክፍሎች በአራት ክፍል ከፍለን ማየት እንችላለን። እነዚህም አራቱ ክፍላት የሚከተሉት ናቸው።

፩, ስመ ኩሉ /የወል ስም/--- collective noun

፪, ስመ ተጸውዖ / የመጠሪያ ስም --- proper noun

፫, ስመ እነግሊጋ / የጥቅል ስም/ ----common noun

፬, ስመ ረቂቅ / የነገር ወይም የግብር ስም/ --- abstract noun

**፩, ስመ ኩሉ**፡- ይህ የስም ዓይነት በአማረፀኛ የወል፣ ጋራ ወይም የሁሉማለት ሲሆን የሰዎች ወይም የነገሮች ስብስብ በአንድነት የሚገለጽበት፤ ለቤት አገልግሎት ለሚውሉ ሰው ለሠራቸው ቁሳቁሶች የሚሰጥ ስያሜ ነው።

ምሳሌ፡- ብእሲ፣ ብእሲት፣ ላሕም፣ ሦር፣ መንበር፣ ዐራት፣ ጵርሆ፣ ወዘተ…

**፪, ስመ ተጸውዖ**፡- ይህ የስም ዓይነት ማንኛውም ፍጥረት ከነፈጣሪው በተለይ ለግሉ ስም ወጥቶለት የሚጠራበት ስም ነው።

ምሳሌ፡- ጴጥሮስ፣ ኢትዮጵያ፣ ጎንደር፣ ግዮን፣ ኢየሩሳሌም፣ ወዘተ…

**ማስታወሻ**፡-

- ♣ በተጸውዖ ስም ላይ ተደርበው የሚነገሩ የአክብሮት፣ የማዕረግ፣ የተዛምዶና የተቀብዖ ስሞች አሉ።

ምሳሌ፡- ጋሽ፣ እምዬ፣ እሜቴ፣ ደጅ አዝማች፣ ራስ፣ ግራ አዝማች፣ መቶ አለቃ፣ ረቢ፣ ጳጳስ፣ ዲያቆን፣ ወዘተ…

**፫, ስመ እንግሊጋ**፡- ይህ የስም ዓይነት የጥቅል ስም ውስጠ ብዛት ያለው አንድ ስብስብ የሚጠራበት ነው። ይህም ማለት ብዙ የወል ስሞችን በውስጡ ይይዛል ማለት ነው።

ምሳሌ፡- ሕዝብ፣ መርዔት፣ ፍጥረት፣ ሰብእ፣ ወዘተ…

**፬, ስመ ረቂቅ**፡- ስመ ረቂቅ በዓይን የማይታዩ በእጅ የማይዳሰሱ፤ በዓይን ታይተው በእጅ የማይዳሰሱ፤ በጆሮ ተሰምተው በዓይን የማይታዩ፤ ዓይነትን፣ ግብርንና ሁኔታን የሚያመለክቱ፤ ጉልህ ሆነው የማይጨበጡ፤ በአእምሮ ብቻ የሚታሰቡ ረቂቅ ነገሮች የሚጠሩበት ስም ነው።

ምሳሌ፡- ሕይወት፣ ሞት፣ ድንቁርና፣ ቅዳሴ፣ ወዘተ…

**፫.፩.፪ የስም ሙያ**

ማንኛውም ቃል በዐ/ነገር ውስጥ የሚገኝበት ሁኔታ ሙያ ይባላል። ስለዚህ ስም በዐ/ነገር ውስጥ ተገኝቶ የሚሰጠው አገልግሎት የስም ሙያ ይባላል ማለት ነው። ስም እንደ አገባቡ አራት ዋናዋና ሙያዎች አሉት።

| | |
|---|---|
| ፩, ባለቤት | ፪, ተሳቢ |
| ፫, የሰሚ ባለቤት | ፬, ዘርፍ |

**፩, ባለቤት**፡- ስመ በዐ/ነገር ውስጥ ሲያገለግል እንደ ባለቤት ያገለግላል። ባለቤት ማለት ደግሞ አንቀጽ ከነጓዙ የሚነገርለት፣ ድርጊት አድራጊና ፈጻሚ ማለት ነው።

ምሳሌ፡- ሰብእ መጽአ

ተሐንጸ ቤት ዲበኰኵሕ

**፪, የሰሚ ባለቤት**፡- አንድ ስም የሰሚ ባለቤት ሆኖ አገለገለ ማለት ሁልጊዜ ዐ/ነገሩ የሚነገረው ለሁለተኛ ሰው ነው ማለት ነው። ይኸው ሰው ወይም ሰሚው ለተጠቀሰው ዐ/ነገር ባለቤት ነው። በዐረፍተ ነገር ውስጥ «አ» የሚለውን ድምጽ ይዞም ሳይዝም ሊነገር ይችላል።

ምሳሌ፡- አ አዳም መሬት አንተ

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ

አ አምላክ ደምከ ውኅዘ

**ማስታወሻ**፡-

- ሰሚ የሚለውን ቃል በአራት ከፍሎ ማየት ይቻላል።እነዚህም እንደሚከተለው ይገለጻሉ።
  - የባለቤት ሰሚ፡- አ አምላክ ደምከ ውኅዘ
  - የአገባብ ሰሚ፡- አማኑኤል ለዕውር ቅኔ ቅኔከ አስተብፅእዎ
  - የዘርፍ ሰሚ፡- አ አምላክ ደመ ገቦከ ውኅዘ
  - የተሳቢ ሰሚ፡- አ አምላክ ቤተከ ሐነፁ

**፫, ተሳቢ**፡- ተሳቢ ማለት ድርጊት የሚፈጸምበት ተዐረፍተ ነገር ክፍል ነው። ተሳቢ ርቱዕ ተሳቢና ኢ-ርቱዕ ተሳቢ ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

ሀ, ርቱዕ ተሳቢ፡- ገቢር አናግሮ ለገቢር ግሥ የሚስብ ተሳቢ ማለት ሲሆን ሲስብም የፊደላትን ቅርጽ በመቀያየር ነው።

| መድረሻ | ለውጥ | ምሳሌ |
|---|---|---|
| ግእዝ | ግእዝ | |
| ካዕብ | ሳብዕ | ቤቱ--- ቤቶ፣ እሙ--- እሞ፣ ወዘተ… |
| ሣልስ | ኃምስ | ብእሲ--- ብእሴ፣ ገባሪ--- ገባሬ፣ ከይሲ--- ከይሴ፣ ወዘተ… |
| ራብዕ | ራብዕ | መና--- መና፣ ደመና--- ደመና፣ ደብተራ---- ደብተራ፣ መንበራ-- መንበራ፣ወዘተ… |
| ኃምስ | ኃምስ | ቅዳሴ--- ቅዳሴ፣ ውዳሴ--- ውዳሴ፣ መናሔ--- መናሔ፣ ወዘተ… |
| ሳድስ | ግእዝ | መሬት--- መሬተ፣ ህብስት--- ህብስተ፣ አመት--- አመተ፣ ወዘተ… |
| ሳብዕ | ሳብዕ | ከበሮ--- ከበሮ፣ መሰንቆ--- መሰንቆ፣ ወዘተ… |

ለ, ኢ-ርቱዕ ተሳቢ፡- ይህ የተሳቢ ዓይነት ቃሉን ሳይለዋውጥ በደቂቅ አገባብ (መስተዋድድ) ይመሠረታል። ግሡም ገቢርም ተገብሮም ሊሆን ይችላል።

ምሳሌ፡- ወልድ መጽአ ውስተ ዓለም

ተፈነወ ወልድ በአብ

ተፈጥረ ዓለም በአምላክ

**ማስታወሻ**፡-

- ርቱዕ ተሳቢ በምንሠራበት ጊዜ መድረሻ ፊደላቸው በ«ሁ» የሚጨርሱ ስሞች ተሳቢያቸው ራሱ ነው።

  ምሳሌ፡- ቅዳሴሁ- ቅዳሴሁ፣ ሥጋሁ-- ሥጋሁ
- የተጸውዖ ስምን ስንስብ «ሃ» የሚለውን ፊደል እንጨምርበታለን። አንዳንዴም «ለ»ን ከፊት እንጨምርበታለን።

  ምሳሌ፡- ጴጥሮስ-- ጴጥሮስሃ፡ ለጴጥሮስ

  ዳዊት-- ዳዊትሃ፡ ለዳዊት
- ለሀገራት ፍፁም ሳድስ ሦስት ፊደል ከሆነ መድረሻቸውን ወደ ግእዝ በመቀየር ተሳቢያቸውን እንመሠርታለን።

  ምሳሌ፡- ግብፅ-- ግብፀ፣ ምስር-- ምስረ፣ ቅምር-- ቅምረ፣ ወዘተ…
- ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ሌሎች ሐገ ወጦች አሉ። ከነዚህ ሕገ ወጦች ውስጥ የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

| ቃል | የስም ዝርዝር | የተሳቢ ዝርዝር |
|---|---|---|
| አብ | አቡሁ፣አቡሆሙ፣አቡሃ፣አቡሆን፣አቡከ፣አቡክሙ፣ አቡካ፣አቡክን፣አቡየ፣አቡነ | አቡሁ፣አቡሆሙ፣አቡሃ፣አቡሆን፣አባከ፣አባክሙ፣አባኪ፣ አባክን፣አባየ፣አባነ |
| ሐም | ሐሙሁ፣ሐሙሆሙ፣ሐሙሃ፣ሐሙሆን፣ሐሙከ፣ ሐሙክሙ፣ሐሙኪ፣ሐሙክን፣ሐሙየ፣ሐሙነ | ሐሙሁ፣ሐሙሆሙ፣ሐሙሃ፣ሐሙሆን፣ሐማከ፣ሐማክሙ፣ ሐማኪ፣ሐማክን፣ሐማየ፣ሐማነ |
| አፍ | አፉሁ፣አፉሆሙ፣አፉሃ፣አፉሆን፣አፉከ፣አፉክሙ፣ አፉክን፣አፉኪ፣አፉየ፣አፉነ | አፉሁ፣አፉሆሙ፣አፉሃ፣አፉሆን፣አፉከ፣አፉክሙ፣አፉክን፣ አፉኪ፣አፉየ፣አፉነ |
| እኅ | እኁሁ፣እኁሆሙ፣እኁሃ፣እኁሆን፣እኁከ፣እኁክሙ ፣እኁክን፣እኁኪ፣እኁየ፣እኁነ | እኁሁ፣እኁሆሙ፣እኁሃ፣እኁሆን፣እኁከ፣እኁክሙ፣እኁክን፣ እኁኪ፣እኁየ፣እኁነ |
| እድ | እዴሁ፣እዴሆሙ፣እዴሃ፣እዴሆን፣እዴከ፣እዴክሙ ፣እዴክን፣እዴኪ፣እዴየ፣እዴነ | እዴሁ፣እዴሆሙ፣እዴሃ፣እዴሆን፣እዴከ፣እዴክሙ፣እዴክን፣ እዴኪ፣እዴየ፣እዴነ |

**፬, ዘርፍ**

ሁለት ስሞች በአንድነት ተጣምረው አንደኛው ባለገንዘብ ሁለተኛው ገንዘብ ሆነው ሊመሠረቱ ይችላሉ። ገንዘቡ ባለቤት ሲባል ባለገንዘቡ ዘርፍ ይባላል።

ምሳሌ:- ቤተ አቡየ → ቤት--- ባለቤት፥ አብ--- ዘርፍ፥ የ--- ዝርዝር ይባላሉ።

ዘርፍ በሦስት መንገድ ሊመሠረት ይችላል። እነዚህም መንገዶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ, በማናበብ

ለ, በ«ለ»

ሐ, በ«ዘ፣እንተ፣ እለ»

ሀ, በማናበብ ሲመሠረት:- ዘርፍ ከባለቤት ጋር ሊጣመር የሚችለው ገቢር የመሆን ችሎታ ባላቸው ስሞች ነው። ይህም ማለት ዘርፍ ከባለቤት ጋር የሚያያዘው በግእዝ፣ በራብዕ፣ በኃምስና በሳብዕ ፊደል ብቻ ነው።

ምሳሌ:- ፍኖተ ሠላም፣ ደብተራ ኦሪት፣ ብእሴ እግዚአብሔር፣ ከበሮ ማኅሌት፣ ወዘተ…

**ማስታወሻ:-**

- ♣ በማናበብ የተመሠረቱ ስሞች ዘርፍ ደፊ ሊሆኑ ይችላሉ። ዘርፍ ደፊ ማለት ዘርፉንና ባለቤቱን ቦታቸውን ቀያይሮ መጻፍ ማለት ነው።

  ምሳሌ:- ፍኖተ ሠላም ---- ሠላመ ፍኖት፥ ሊሆን አይችልም።

ለ, በ«ለ» ሲመሠረት:- ማንኛውም ዘርፍ በ«ለ» ሲመሠረት ስሙ ወይም ባለቤቱ ተዘርዝሮ መቀመጥ አለበት። እነዚህ ስሞች ዘርፍ ደፊ ሊሆኑ ይችላሉ። ዘርፍ ከሁለት ቃላት በላይ ከተያያዘ የዘርፍ ዘርፍ ይባላል።

ምሳሌ:-

| በ«ለ» የተመሠረተ ዘርፍ | የዘርፍ ዘርፍ | ዘርፍ ደፊ |
|---|---|---|
| ቤቱ ለዮሐንስ | ቅጽረቤቱ ለዮሐንስ | ለዮሐንስ ቅጽረ ቤቱ |
| ምክሮሙ ለጠቢባን | ዜና ምክሮሙ ለጠቢባን | ለጠቢባን ዜና ምክሮሙ |
| መዝሙሩ ለዳዊት | መሰንቆ መዝሙሩ ለዳዊት | ለዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ |
| ክብሩ ለሰሎሞን | መንበረ ክብሩ ለሰሎሞን | ለሰሎሞን መንበረ ክብሩ |

ሐ, በ«ዘ፣ እንተ፣ እለ» ሲመሠረት:-እነዚህ ቀለማት ያልተዘረዘሩ ስሞችን ያያይዛሉ። በአጠቃቀማቸው ዙሪያ ሁለት አመለካከት አለ።

የመጀመሪያው አመለካከት ዘ → ለአንድና ለብዙ እለ → ለብዙ ብቻ እንተ → ለነጠላ ብቻ

ምሳሌ:-አማልክት ዘአህዛብ መላእክት እለ ሰማያት ባሕታዊ እንተ ገዳም

ወለት ዘንግሥት ዕቊባት እለ ሰሎሞን ቤት እንተ እኅትየ

አዋልድ እለ አልቦን ኍልቈ

የሁለተኛው አመለካከት ዘ → ለወንድ እለ → ለሴትም ለወንድም እንተ → ለሴት ብቻ

ምሳሌ:-ኬፋ ዘተብህለ ጴጥሮስ ህዝብ እለ ሀለው ምስሌሁ ድንግል እንተ ተፍኅረት

ብዙ ጊዜ በመጻሕፍት የተለመደው እና የምንጠቀምበት የመጀመሪያውን አካሄድ ነው።

**ማስታወሻ:-**

- ♣ በ«ዘ፣ ዝንተ፣ እለ»የተጣመሩ ስሞች ዘርፍ ደፊ ሊሆኑ ይችላሉ።

ምሳሌ:- መዝሙር ዘዳዊት= ዘዳዊት መዝሙር

- ብእሲት እንተ ሎጥ =እንተ ሎጥ ብእሲት

♣ ዘርፍ እና ባለቤት የያዙ ጥምር ስምችባለቤትም ተሳቢም ሊሆኑ ይችላሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ:- ተሐንጸ <u>ቤተ እግዚአብሔር</u>። | ባለቤት | ሰሎሞን ሐነጸ <u>ቤተ እግዚአብሔር</u>። | ተሳቢ |
| ተሐንጸ <u>ቤቱ ለእግዚአብሔር</u>። | | ሰሎሞን ሐነጸ <u>ቤቱ ለእግዚአብሔር</u>። | |
| ተሐንጸ <u>ቤት ዘእግዚአብሔር</u>። | | ሰሎሞን ሐነጸ <u>ቤት ዘእግዚአብሔር</u>። | |

♣ ሰያፍ ዘርፍ አይዝም።

♣ ወገን ቅጽል ዘርፍ አይዝም። ምሳሌ:-ዳዊት መጸብሐዌ ወልድ። -------አይባልም።

♣ «ለ» ተሳቢ ትሆናለች። ምሳሌ:-ሰብሑ ለስመ እግዚአብሔር።

♣ «ዘ» ተሳቢ ትሆናለች። ምሳሌ:-እግዚአብሔር ይጌስጽ ዘያፈቅሮ።

♣ የሰው ስም፣ የመላእክት ስም፣ የሀገር ስም ዘርፍ ይሆናል እንጅ ዘርፍ አይዝም።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማስረጃ:-ክንፈ ሚካኤል | ይላል እንጅ | ሚካኤለ ክንፍ | አይባልም። |
| ዐፅመ ጊዮርጊስ | | ጊዮርጊሰ ዐፅም | |
| ሰብአ ሰዶም | | ሰዶመ ሰብእ | |
| ንጉሠ ባቢሎን | | ባቢሎነ ንጉሥ | |
| እግረ ተክለ አብ | | ተክለ አበ እግር | |
| ውሉደ ያዕቆብ | | ያዕቆበ ውሉድ | |
| ወርቀ ኢትዮጵያ | | ኢትዮጵያ ወርቅ | |

## ፫.፪ ቅጽል

ቅጽል ተቀጸለ ወይም ተቀዳጀ ከሚለው ግሥ የወጣ ዘመድ ዘር ነው፡፡ ቅጽል ከስም ጋር ተናቦ ወይም ተያይዞ የስምን ዓይነትና መጠን፣ ሁኔታንና ግብርን ይገልጻል፡፡ ቅጽል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡እነርሱም:-

ሀ, ውስጠ ዘ ለ, ግልጸ ዘ (አዛማጅ) ቅጽል ናቸው፡፡

ሀ, ውስጠ ዘ ቅጽል:-ዘ የሚባለል ፊደል በግልጽ የማይታይበት ነገር ግን ወደ አማርኛ ሲተረጎም ‹የ‹ የሚባል ፊደል የሚያመጣ የቅጽል ዓይነት ነው፡፡

ለ, ግልጸ ዘ ቅጽል:- እነዚህ የአንቀጽን ማሰሪያነት አስቀርተው የሚቀጸሉ ቀለማት ማለትም (ዘ፣ እለ፣ እንተ)ን በውስጣቸው ይዘው የሚቀጸሉ ቅጽሎች ናቸው፡፡ አንዳንድ ሊቃውንት መሥገርተ ግሥ ብለው ይጠሩአቸዋል፡፡እነዚህ ቀለማት በቅጽልነታቸው አዛማጅ(ግልጸ ዘ) ቅጽል ሲባሉ የአንቀፅን ማሰሪያነት በማስቀረታቸው ዐቢይ አገባብ ይባላሉ፡፡

ምሳሌ:- ጳውሎስ ዘተፀውዐ ወተፈልተ ለትምህርተ ወንጌል ---- የተጠራ ጳውሎስ ወንጌልን ለማስተማር ተለየ

ዐማዊ ንጉሥ ዘኢይሌቡ ይገብር እኩ ---- የማያስተውል ዐመፀኛ ንጉሥ ክፉ ሥራን ይሠራል

ሰብእ እለተኀርዩ እምከርሰ እሞሙ ---- ከእናታቸው ማህፀን የተመረጡ ሰዎች አሉ

ከላይ የተገለጸው ውስጠ ዘ ቅጽል በሰባት ክፍል ይከፈላል፡፡ እነዚህም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡

1, ወገን ቅፅል 2, የግብር ቅፅል 3, የዓይነት ቅፅል 4, አመልካች (ደቂቅ) ቅፅል

5, መጠይቅ (ንዑስ) ቅፅል 6, አገናዛቢ ቅፅል 7, አኀዝ ቅፅል

**<u>፫.፪.፩ ወገን ቅፅል</u>**

በሰውም ሆነ በሀገር ላይ ወድቆ ወገንነትን፣ ኅሳነትንወይም አባትነትን የሚያሳየው የቅፅል ዓይነት ወገን ቅፅል ይባላል፡፡ ወገን ቅፅል መድረሻውን ራብዕ አድርጎ በተባዕታይ ነጠላ ‹ዊ‹ ብዙ ‹ዊያን‹ በአንስታይ ነጠላ ‹ዊት‹ ብዙ ‹ውያት‹ የሚሉትን ቀለሞች ጨምሮ ይገኛል፡፡

| ምሳሌ:- | **ስም** | **ነጠላ ወገን ቅፅል** | **ብዙ ወገን ቅፅል** |
|---|---|---|---|
| | ኢትዮጵያ | ኢትዮጵያዊ/ዊት | ኢትዮጵያዊያን/ውያት |
| | እስራኤል | እስራኤላዊ/ዊት | እስራኤላዊያን/ውያት |
| | ሰማይ | ሰማያዊ/ዊት | ሰማያዊያን/ውያት |
| | ምድር | ምድራዊ/ዊት | ምድራዊያን/ውያት |

**፫.፪.፪ የግብር ቅጽል**

ማንኛውም ፍጥረት የሚሠራውንና የሠራውን፣ ሙያውንና ግብሩን የሚያሳይን ክፍል የግብር ቅጽል ይባላል። የግብር ቅጽል የሚባሉት ሣልስ ቅጽል፣ሳድስ ቅጽልና መስም ውስጠዘና መድበል ናቸው።

ምሳሌ፡- ሣልስ ቅጽል--- መሀሪ፣ ቀታሊ፣ ሠዓሊ፣ ወዘተ.

ሳድስ ቅጽል--- ምሁር፣ ቅቱል፣ ሥዑል፣ ወዘተ.

መስም ውስጠዘ--- መምህር፣ መኰንን፣ መስፍን፣ ወዘተ.

መድበል--- ቀተልት፣ ጠበብት፣ ነገሥት፣ ወዘተ.

**፫.፪.፫ የዓይነት ቅጽል**

የአንድን ነገር፣ ሰው፣ እንስሳ፣ ወይም ዕቃ ቁመት፣ ቀለም፣ ዓይነት እንዲሁም አኳኋን የሚነግረን ቅጽል የዓይነት ቅጽል ይባላል።

ምሳሌ፡- ቀይሕ፣ ሐጺር፣ ሐዲስ፣ ጸሊም፣ ወዘተ.

**፫.፪.፬ አመልካች (ደቂቅ) ቅጽል**

እነዚህ ቅጽሎች ከጓደኞቹ ለይተን “ይህ” ወይም ”ያ” እያልን ነገርን፣ እንስሳንና ሰውን የምናሳይበት የቅጽል ዓይነት ነው። እነዚህንም ቅርብና ሩቅ ብለን ልንከፍላቸው እንችላለን።

| ቅርብ | አማርኛ ትርጉም | ሩቅ | አማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|---|
| ዝ/ዝንቱ | ይህ | ዝክቱ/ዝስኩ/ዝኩ | ያ |
| ዛ/ዛቲ | ይህች | እንትኩ/እንታክቱ | ያቺ |
| እሉ/እሎንቱ | እኚህ(ተ) | እልኩ/እልክቱ | እነዚያ/እነኚያ(ተ) |
| እላ/እሎን/እላንቱ | እኚህ(አ) | እልኰን/እልክቶን | እነዚያ/እነኚያ(አ) |

ምሳሌ፡- ዝ መጽሐፍ ዚአየ ውእቱ

ዝንቱ ብእሲ ቀተለ ዝኰ ከይሴ

እሉ እደው ይኔጽሩ እልክተ አንስተ

**ማስታወሻ፡-**

- ከላይ ያየናቸውን አመልካች ቅጽሎች ስንስባቸው የሚከተለውን ይመስላሉ።

| አመልካች ቅጽል | ተሳቢ | አመልካች ቅጽል | ተሳቢ |
|---|---|---|---|
| ዝ/ዝንቱ | ዘንተ | ዝክቱ/ዝኩ | ዝክተ |
| ዛ/ዛቲ | ዛተ | እንትኩ/እንታክቱ | እንታክተ |
| እሉ/እሎንቱ | እሎንተ | እልኩ/እልክቱ | እልክተ |
| እላ/እሎን/እላንቱ | እላንተ | ዝስኩ | ዝስኰ |

- ከላይ ያየናቸው አመልካች ቅጽሎችና መራሕያን አመልካች ቅጽል ሲሆኑ የሚኖራቸው አገልግሎት ተመሳሳይ ነው።

**፫.፪.፭ መጠይቅ (ንዑስ) ቅጽል**

የነገርንም ሆነ የሰውን ዓይነትና አኳኋን ጠይቀን የምንረዳበት የቅጽል ዓይነት መጠይቅ (ንዑስ) ቅጽል ይባላል። እነዚህንም ነጠላና ብዙ ብለን እንከፍላቸዋለን።

| ነጠላ | ብዙ | ነጠላ | ብዙ |
|---|---|---|---|
| መኑ፣ አይ | እለመኑ፣ አያት | ምንት | ምንታት |
| ስፍን | እስፍንቱ | ወዘተ… | |

ምሳሌ፡- አይ ዕፅ ይኄይስ እምዕፀው

አያት አዝማዲከ እምእሉ ሰብእ

**፫.፪.፮ አገናዛቢ ቅጽል**

ለስም ዝርዝር የሚረዱ ባእዳን ቀለማት አገናዛቢ ቅጽል ይባላሉ። ችነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

| ነጠላ | ብዙ |
|---|---|
| የ | ነ |
| ከ | ክሙ |
| ኪ | ክን |
| ካዕብ/ሁ/ | ሆሙ |
| ራብዕ/ሃ/ | ን/ሆን |

**፫.፪.፯ አኃዝ ቅጽል**

የሰዎችን ወይም የነገሮችን ማነስና መብዛት፣ ስንትነትና ስንተኛነትን ዘርዝሮ የሚያሳይ ቅጽል አኃዝ ቅጽል ይባላል።

ምሳሌ፡- አሀዱ፣ ክልዔቱ፣ብዙኅ፣ ሑዳጥ፣ ንስቲት

አሐዱ ብእሲ ይወርድ ኀበ ኢየሩሳሌም

ሑዳጥ ዓሣ አጽገበ ብዙኃነ

**ምልማድ ፩**

ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ

፩, የግብር ቅጽል የቱ ነው?

ሀ, እሎንቱ ለ, ያሬዳዊ ሐ, ቀቲሎት መ, ዐቀብት

፪, የደቂቅ ቅጽል አገልግሎት፡-

ሀ, ለማመልከት ለ, ለመጠየቅ ሐ, መጠንን መግለጽ መ, ሁሉም

፫, ቁመት በ_____________ ቅጽል ይመደባል።

ሀ, አመልካች ለ, ዓይንት ሐ, አኀዝ መ, መጠይቅ

፬, ከስም በፊት ሲገቡ አንቀጽ በኋላ ሲገቡ ቅጽል የሚሆኑ __________ ቅጽሎች ናቸው።

ሀ, አመልካች ለ, አገናዛቢ ሐ, አዛማጅ መ, መልስ የለም

፭, "ትጉህ ውእቱ ዮሐንስ" በሚለው ዐ/ነገር ውስጥ ቅጽሉ፡-

ሀ, ውእቱ ለ, ትጉህ ሐ, ዮሐንስ መ, መልስ የለም

## ፫,፫ አገባብ

በሰዋስው መነሻ፣ መካከልና መድረሻ ላይ እየገባ ሰዋስውን ነጅ ወይም በሰዋስው ተነጅ ሆኖ የሚነገር ብትን ነባር ሰዋስው አገባብ ይባላል። አገባብ ማለት የሰዋስው አሰባሰብ የሰዋስው አሰካክ ማለት ነው። በአጠቃላይ አገባብ ማለት ሰዋስውን ሰብሳቢ፣ ማሳኪያና ማያያዣ ማለት ነው። አገባብ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። አነዚህም፡-

ሀ, ዐቢይ አገባብ
ለ, ንዑስ አገባብ
ሐ, ደቂቅ አገባብ
ናቸው።

**፫.፫.፩, ዐቢይ አገባብ**

በሰዋስው ላይ (በአንቀጽና በስም) ላይ እየገባ ወይም እየወደቀ የሚነገር ብትን ነባር ሰዋስው ዐቢይ አገባብ ይባላል። ዐቢይ ማለት ታላቅ፣ ጽኑ፣ ብርቱ፣ ወዘተ ማለት ነው። በነባርና በዘማች አንቀጽ በኃላፊና በትንቢት እየገባ ወይም እየወደቀ ማሰሪያነትን የሚያስለቅቅ ዐቢይ አገባብ ይባላል። ዐቢይ የተባለበት ምክንያት በሰዋስው (በስምና በአንቀጽ) ላይ እየወደቀ የአንቀጽ ማሰሪያነትን ስለሚያስቀር ነው። አገባብ የተባለበት ምክንያት ደግሞ በሰዋስው (በስምና በአንቀጽ) ላይ እየወደቀ ሰዋስውን ስለሚያሳካ፣ ዐ/ነገርን ስነሚያስማማ ነው።

ብዙ ዓይነት የዐቢይ አገባብ ዓይነቶች አሉ። ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

1, ገላጭ (አስረጅ) ፡- እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ

2, ማንፀሪያ፡- ከመ፣ አምሳለ፣ እስከ፣ ወዘተ…

3, አፍራሽ (አሉታ) ፡- አላ፣ ዳዕሙ፣ ባሕቱ፣ እንበለ፣ አዲ፣ ወዘተ…

ምሳሌ፡- ብዙኃን ይትፌስሑ በልደቱ እስመ/አምጣነ/አኮኑ ዐቢየ ይከውን

ቀነዮ ሞት ለአዳም እስመ/አምጣነ/አኮኑ አበሰ አዳም

አንጎርጎሩ አይሁድ በእንተ ዘሐይወ ዕውር

እስመ/አምጣነ/አኮኑ ኢአቀበ ትዕዛዞ ለእግዚአብሔር ተወከፈ አዳም በድልዎት ፍትሐ ሞት በሥጋ ወነፍስ እምእግዚኡ

አሌ ለክሙ አ ሕዝበ ክርስቲያን እስመ/አምጣነ/አኮኑ ተሠልጡ ላዕሌክሙ ተንባላት

ዮም ንወድሳ ለማርያም በእንተ ዘተወልደ እምኔሃ እግዚአብሔር ቃል

ኀበ ሀሎ ገደላ ይትጋብኡ አንስርት

አይሁድ ሰቀሉ አምላከ <u>ከመ</u> ሰቀለ ሙሴ አርዌ ብርት

ኢናጥብዕ ልበነ <u>ዳዕሙ</u> ንዘከሮሙ ለነዳያን

ዐቢይ አገባብ በጣም ብዙ ክፍሎች ሲኖሩት ለዚህ ትምህርት ይሆነን ዘንድ እንደምሳሌ በጣም ትንሾችን እናያለን፡፡እነዚህንም ከዚህ በታች በየከፍላቸው እናያቸዋለን፡፡

**፩, «ና» የሚሆኑ አገባቦች**

«ና» የሚሆኑ አገባቦች አምስት ናቸው፡፡ እነዚህም እስመ፣ አምጣነ፣ አኮኑ እና ሰ ናቸው፡፡ ወ አገባብን ሁሉ ሲጫን እስመን፣ አምጣነንና አኮኑን አይጫናቸውም፡፡ አነዚህ እስመ፣ አምጣነና አኮኑ ከአገባብ ሁሉ በፊት በመጀመሪያ ይነገራሉ፤ አነርሱን የሚቀድማቸው የለም፡፡

«እስመ» «ና» ሲሆን፡- ኢትቴክዙ እስመ ቀርበ ዘመነ መንግሥቱ ለቴዎድሮስ--- የቴዎድሮስ የመንግሥቱ ዘመን ቀርቧልና አትተክዙ፡፡

ንስተይ ወይነ አስመ ወይን ያስተፌሥሕ ልበ ሰብእ--- ወይን እንጠጣ ወይን የሰው ልብን ያስደስታልና፡፡

እስመ ልዑል እግዚአብሔር ይሴባሕ በኀበ ልዑላን--- እግዚአብሔር ታላቅ ነውና በታላላቆች ዘንድ ይመሰገናል፡፡

«አምጣነ» እና «አኮኑ»ም ከማሁ ይሠራሉ፡፡

«ሰ» «ና» ሲሆን፡- የኀደገን፣ የተርፈን፣ የጸንሐን፣ የበዝኀንና የተረስአን ትእዛዝ ይዞ ይገባል፡፡ በኮነና በረሰየ ትእዛዝ ዝንጋዔን፣ ዛውዐን፣ ስሐቅን፣ ስላቅን፣ ተውኔትን፣ ሕብልን ሕላዌንና ተምኔትን ይዞ ይገባል፡፡ «ሰ» «ና» ሆኖ በሚያገለግልበት ዐረፍተነገር ሁለት ማሠሪያዎች ይኖሩታል፡፡የመጀመሪያ ማሠሪያው አልቦ፣ ኢ፣ አኮ ናቸው፡፡ በሁለተኛው ማሠሪያ ተሳቢ ወ፣ ሂ፣ ኒ፣ ኒ፣ ጥቀ ስንኳ ሲሆኑ ይገባሉ፡፡ ሲገባም እንደሚከተለው ነው፡፡

- ኢፈጸሙ አይሁድ ሕገ ወንጌል ይትረሳዕሰ/ይዘንጋዕሰ/ይጽናሕሰ/ይትኀደግሰ/ይትርፍሰ ዝንቱ ሕገ ኦሪትሂ/ሕገ ኦሪት ጥቀ/ሕገ ኦሪት ኒ/ ወሕገ ኦሪት ኢፈጸሙ--- አይሁድ ሕገ ወንጌልን አልፈጸሙም፤ ይህስ ይቅርና/ይህስ ይቆይና ተኦሪት ሕግን ስንኳ አልፈጸሙም፡፡

| ፪, «ስለ» የሚሆኑ አገባቦች | ምሳሌ | አማርኛ ፍቺ |
|---|---|---|
| በእንተ<br>በይነ<br>እንበይነ<br>ህየንተ<br>ተውላጠ<br>ፍዳ<br>በቀለ<br>በዘ | አንጎርጎሩ አይሁድ በእንተ ዘሐይወ አይሁድ<br>ነሰሐ ሳሙኤል በይነ ዘአንገሦ ለሳኦል<br>በከየት ራሔል እንበይነ ዘተቀትሉ ደቂቃ<br>ፈደይዎ አይሁድ እኪተ ለእግዚእነ ህየንተ ዘገብረ ሠናየ<br>ተገፍዐ ዳዊት በእደ ወልዱ ተውላጠ ዘገፍዖ ለኢርዮ<br>ነድየ ነዌ እምብዕለ ነፍስፍዳ ዘብዕለ በብዕለ ሥጋ<br>ብፁዕ ዘይትቤቀለኪ በቀለ ተበቀልክነ<br>ነሥኡ ሰማዕት አክሊለ ፅድቅ በዘተጋደሉ ብዙኃ | አይሁድ ዕውር ስለዳነ አጉረመረሙ፡፡<br>ሳሙኤል ሳኦልን ስላነገሠ ተጸጸተ፡፡<br>ራሔል ስለተገደሉ ልጆቿ አለቀሰች፡፡<br>አይሁድ ጌታችንን በጎ ስላደረገ ክፉን ከፈሉት፡፡<br>ዳዊት ኦርዮን ስለገፋ በልጁ እጅ ተገፋ፡፡<br>ነዌ በሥጋ ብልፅግና ስለበለፀገ ከነፍስ ብልፅግና ደኸየ፡፡<br>ስለተበቀልሽን የሚበቀልሽ ንኡድ ክቡር ነው፡፡<br>ሰማዕት ብዙን ስለተጋደሉ የጽድቅ አክሊልን ተቀበሉ፡፡ |
| ፫, «ዘንድ» የሚሆኑ አገባቦች | | |
| ኀበ<br>መንገለ<br>ወ/ው/እደ | ኀበ ሀሎ ገደላ ይትጋብኡ አንስርት<br>አስተጋብኡ አይሁድ ሕሙማነ መነገለ ሀሎ ክርስቶስ<br>ተጋብኡ ሕዝብ ብዙኃንወእደገብሩ ሐዋርያት ተአምረ | ግዳይ ባለበት ዘንድ አሞሮች ይበዛሉ፡፡<br>አይሁድ ክርስቶስ ባለበት ዘንድ በሽተኞችን ሰበሰቡ፡፡<br>ሐዋርያት ተአምርን ባደረጉበት ዘንድ ብዙ ሕዝብ ተሰበሰቡ፡፡ |

ከላይ የተጠቀሱትን እንደ ምሳሌ ካየን ሌሎችን ደግሞ ከተለያዩ የግእዝ መጽሐፎች መመልከት ይቻላል፡፡

**፫.፫.፪ ንዑስ አገባብ**

ከስም ወይም ከአንቀጽ በፊት ወይም በኋላ ገብቶ ሁለት ቃላትን የሚያጫፍር ሰዋስውን የሚያሳካ /የሚያያይዝ/ ዐ.ነገርን የሚያስማማ ንዑስ አገባብ ይባላል።

- ንዑስ የተባለበት ምክንያት  ከአንቀጽ ላይ ወድቆ የአንቀጽን ማሰሪያነት ስለማያስቀር ነው።
- አገባብ የተባለበት ምክንያት የሰዋስው(አንቀጽ እና ስም) ማሳኪያ(ማያያዣ) የዐ.ነገር ማስማሚያ ስለሚሆን ነው።

ምሳሌ፡-ምንት፣ መኑ፣ አይ፣ እፎ፣ ማዕዜ፣ አይቴ፣ ስፍን፣ በሀ

- ምንት ትገብር
- አይ ይሰምእ ቃለከ
- አይቴ ቀበርክምዎ ለአላዛር
- ኀበ መኑ ተፈነወ መልአክ ኀበ ኤልሳቤጥኑ ወሚመ ኢተፈነወ ኀበ ሰሎሜ እንበለ ዘተፈነ ኀበ ማርያም
- በሀ በልዋ አንትሙ ለቤተክርስቲያን

ንዑስ አገባብ  ከሚባሉት ውስጥ

- መጠይቅ ንዑስ አገባብ፡- ምንተ ትገብር ፤ አንተኑ ተዐቢ እምያእቆብ
- አንቀጽ አጎላማሽ ፡-እፎ ተአምኑ ቃልየ
- ተሳቢ፡- እስፍንተ ቀተለ ሐራዊ ፤ አይቴ ፆደ ዮሐንስ፤ መነ የኀሥሡ አይሁድ
- ቅጽል፡-

  የባለቤት ቅጽል፡-ምንት ግብር ይበቍዖ ለሰብእ ፤ አይቴ ሀገር ትከውን ምዕራፈ

  የተሳቢ ቅጽል፡- ምንተ ግብረ ንግበር ንሕነ ፤ አይቴ ሀገረ ወረሰ አብረሀም

- የሰዋስው ዘርፍ፡- ብእሴ ምንት ያስቀርር እግዚአብሔር፤ ምክረ አይ ሰምአ አዳም፤ ምጽዐተ መኑ ይፈርህ አርዌ

# ንዑስ አገባብ ከምንላቸው ውስጥ የሚከተሉትን መጥቀስ እንችላለን።

**፩, አይ፤ምንት፤አያት፤ምንታት፤አ፤ሚ፤መኑ**

እነዚህ ንዑስ አገባባት ምን፤ ምንድን ተብለው ይተረጎማሉ፡፡ የበዙት ደግሞ(አያት፤ምንታት) ምኖች ፤ ምንድኖች ተብለው ይፈታሉ፡፡ ከተጸውዖ ስም በቀር በብትን ሁሉ ይገባሉ፡፡

ምሳሌ፡-

- አይ ምግባር ውእቱ ምግባሩ ለአብርሃም ስርቅኑ ወሶበ አኮሁ ትዕግልት ባሕቱ ኂሩት፡፡
- ምንቱ ለዳዊት ሰሎሞን እኑሁኑ ወሚመ ወዐሊሁ አላ ወልዱ፡፡
- አየ መብልዐ በልዐ ዮሐንስ እክልኑ ወሚመ ሥጋ አላ ቈጽለ፡፡
- አያተ እመሳፍንት ወእምነቢያት ለመሥዋዕት ዘኀረየ እግዚአብሔር ነቢያተሁ ወእመ አኮሁ ነገሥተ ዳእሙ ካህናተ።

በ ‹አይ› እና ‹መኑ› ላይ እለ ሲገባ ያበዛዋል፡፡

- እለመኑ ፈነወ ሙሴ ውስተ ሴሎ እለ አልአዛርኑ ወሶበ አኮኑ እለ አብድዩ ዳዕሙ እለ ካሌብ፡፡
- አ ዕፁብ ግብሩ ለእግዚአብሔር እስመ ኢኀሠሠ ረዳኢ እንዘ ይገብር ኲሎ፡፡
- ሚ ተዐጋሢ ጊዮርጊስ እስመ ኢያምረረ ውዕየ እሳት ውብልሐ ሰይፍ፡፡

**፪ አይ፤ አይቴ፤ ማእዜ**

‹አይ› ‹አይቴ› የት ወዴት ይሆናሉ፡፡ ‹አይ› እና ‹ማእዜ› ደግሞ መቼ፤ መቼ ተብለው ይፈታሉ፡፡

- እም አይቴ ሀገር ኀበ ግብጽ ሖረ አብርሐም እምከላውዴዎንሁ ወሚመ እምካራን አላ እምከነዓን፡፡
- ኤሊያስ እምአይቴ ሖረ፡፡
- እም አይ ሀገር ኀበ ገነት ሖረ ኤሊያስ እመ ኢሖረ እም ናዝሬት ወሚመ እም ገሊላ ዳዕሙ እምነ ሰማርያ፡፡

- አይ ዕለት ተሰቅለ ክርስቶስ ዕለተ ረቡዕኑ ወሚመ ዕለተ ዓርብ፡፡
- ማእዜ ተሰብከት አሪት እምጊዜ አብርሐምኑ ወእመ አኮኑ እምጊዜ ሳሙኤል ባሕቱ እም አመ ሙሴ፡፡
- አዳምሰ ድኅነ ሶበ ተሰቅለ አምላኩ ማእዜ ድኅነ ይሁዳ፡፡

**፫, ስፍን፤ እስፍንቱ**

‹ስፍን› ስንት ‹እስፍንቱ› ስንቶች ይሆናሉ፡፡

- ስፍን ኅብስት መብልዑ ለመነኮስ ኃባውዝሁ ክልዔቱ ወሚመሁ ኃምስቱ ኃባውዝ አላ ስድስቱ ኅብስተ፡፡
- ስፍነ ሕፃነ ወለደት ሳራ እመ ኢወለደት ክልዔተ ወሚመ ኢወለደት ኃምስተ አላ ስድስተ ሕፃናተ፡፡
- እስፍንተ ሕፃናተ ወለደት ርብቃ ኃምስተሁ ሕፃናተ ወእመ አኮሁ ኃምስተ ዳእሙ ክልዔተ ሕፃናተ፡፡

**፬, እፎ፤ በእፎ፤ ለምንት**

‹እፎ› እንዴት፣ ምንኛ ፤ምነው ይሆናል፡፡ በእፎ፤ ለምንት ለምን፤ ለምንድን ይሆናሉ፡፡

- እፎ ሠናይ ሀገረ መላእክት እስመ ኢሀለዉ ቦቱ ገፋዕያነ ነዳይ፡፡
- ለምንት ኀደጉ መነኮሳት ሀገሮሙ እም ኢረከቡ ሀገረ ሠናይተ፡፡
- እፎ የኀድጉ ጻድቃን ቤቶሙ እም ኀደጉ ቤቶሙ አልቦሙ ተስፋ፡፡
- ቦኑ በእፎ ወረደ ዳዊት ውስተ ኢሎፍሊ እመሰ ፀብዐ ሳኦል ይፈርሕ፡፡

**፭, ሁ፤ኑ**

እነዚህ ንዑስ አገባቦች ቃላተ ጥያቄ ናቸው፡፡ ትርጉማቸውም ‹ን፤ት› ይሆናሉ፡፡

- እፎ አኀዝዎ ለወልድ አይሁድ ወእፎ አሠርዎ ይትአኀዝኑ እሳት ወይትአሠርኑ እግዚእ፡፡
- በይነ ምንት ትዝህርቱ ለባዕል ላዕለ ነዳይ፤ ወበይነ ምንት ተዋርዶቱ ለነዳይ በባዕል ኢየነዲሁ ዘብዕለ ወኢይብዕልሁ ዘነድየ፡፡

**፮, ቦኑ**

‹በውኑ› ተብሎ ይፈታል፡፡ መነሻዎቹ እፎ፤ በእፎ፤ ለምንት ናቸው፡፡ በአንቀጽ በቀዳመደይ በካልዓይ ይገባል፡፡

- በእፎ ያፈቅር ሰብእ ዓለመ ቦኑ ይመስሎ ዘኢየኀልፍ፡፡

**፯, አ**

‹አ› በንዑስ አገባብነቱ የሚከተሉት አገልግሎቶች አሉት፡፡

1, ቃለ አክብሮ 4, ቃለ አኅስሮ 7, ምን
2, ቃለ ተጋንዮ 5, ሆይ 8, ይብላኝለት
3, ቃለ ተሣልቆ 6, ወዮ 9, ስመ አምላክ ይሆናል፡፡

ምሳሌ፡-

- አ ማርያም እፎ አግመርኪ አምላከ እንዘ ንዕስት አንቲ። -------ቃለ አክብሮ
- አ ማርያም መላእክት የዐብዩኪ ወሱራፌል ይሴብሑኪ።-------ቃለ ተጋንዮ
- አ ሰብእ ምንት ትትዔበይ እንዘ መሬት አንተ። --------ቃለ አኅስሮ
- አ ይሁዳ በቋዕከኑ እም ትሠይጦ ለእግዚእከ። --------ቃለ ተሣልቆ
- አ አኃውየ ኢታፍቅሩ ወርቀ እስመ ወርቅ ኀላፊ ውእቱ። -------ሆይ
- አ ፈጠረ ዓለመ። -------ስመ አምላክ
- አ ይሁዳ ዘሤጦ ለእግዚኡ። --------ይብላኝለት
- አ ዕሙቅ ብዕለ ጥበቡ ለእግዚአብሔር። --------ምን
- አ እም ዝንቱ ሞት ዘሥሉጥ ላዕለ እጓለእምሕያው። ------- ወዮ

**፰, አሌ፤ወይ፤ሰይ**

እነዚህ ደግሞ ‹ወዮ› ተብለው ይፈታሉ፡፡ እንተ፤ እለ፤ ዘ፤ እስመ/አምጣነ/አኮኑ፤ ይከተሏቸዋል፡፡ በ‹ለ› ዝርዝር ይገባሉ፡፡

- አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን እስመ ትበልዑ አብያተ መበለታት፡፡
- ወይ/አሌ ሊተ ሕገ ወትእዛዘ በእንተ ኢዐቀብኩ ወድኅረኒ በእንተ ኢነሳሕኩ፡፡
- ሰይ ሊተ ዘርኅቀ ማኀደርየ፡፡

**፱, አው፤ዮጊ፤ሚመ፤እመ፤አኮ፤ሶበአኮ**

እነዚህም ‹ወዮ› ይሆናሉ፡፡ መነሻዎቻቸው እፎ፤ በእፎ ለምንት ናቸው፡፡ እነዚህንም ባሕቱ ‹ነገር ግን› ሲሆን ይከተላቸዋል፡፡

- እፎ መተረ አዳም በለሰ ባሕቱ አይ እመ ኢያእመረ ከመይተልዎ መርገም፡፡
- ዳዊት በእፎ ቀተለ  ነፍሰ ባሕቱ/ዮጊ እንዘ/እመ ይስሕት ትእዛዘ እግዚኡ፡፡
- እፎ ያፈቅር ሰብእ ተድላ ዓለም ባሕቱ/አው ሶበ ኢያእመረ ከመ ይማስን ፍጡነ፡፡
- ምንት ሲሳዩ ለዮሐንስ አዉ ቆጽል፡፡
- መኑ አቡሁ ለያዕቆብ ሚመ ይስሐቅ፡፡
- ምንት ልብሱ ለዮሐንስ ዮጊ ሰቀ ጸጉር፡፡

**፲, እስኩ፤ ዮጊ**

እነዚህ ደግሞ ‹እስኪ› ይሆናሉ፡፡መነሻዎቻቸው እፎ፤ በእፎ ለምንት ናቸው፡፡ እነዚህንም ባሕቱ ‹ነገር ግን› ሲሆን ይከተላቸዋል፡፡

- እፎ ያፈቅር ሰብእ ንዋየ ባሕቱ እመ/ሶበ ኢያእመረ እስኩ ከመ ይማስን፡፡
- ንስጥሮስ እፎ ኀደገ አምላኮ  እስኩ ይጠይቅ ይሁዳሃ ከመ ረከበ በቁዔተ አመ የኀድግ አምላኮ፡፡
- ዮጊ ኢትስግድ ሊተ እስመ አነሂ ገብር ከማከ፡፡

**፲፩, ከመ፤ጽመ**

ከመ እና ጽመ ‹ዝም ብሎ› ተብለው ይተረጎማሉ፡፡ ‹ከመ› ‹መቸም፤ መች፤ ድንቅ፤ ብቻ ›ይሆናል፡፡

- እፎ መተረ አዳም በለሰ ባሕቱ አይ እመ ኢያእመረ ከመይተልዎ መርገም፡፡
- ለምንት ኀደጉ ኀጥአን አምላኮሙ ባሕቱ ከመ ኢያእመሩ ትእዛዘ አሪት፡፡
- ከመኒ ኢያዕረፉ እሥራኤል እምፀብእ ከመ እመ ነግሠ ሰሎሞን፡፡
- አዳም ከመ ነበረ ውስተ ገነት እምቅድመ ትጻእ ሔዋን እምገቦሁ፡፡

**፲፪, እስመ፤ኳ**

እስመ ኳ ‹ምንኛ› ይሆናሉ፡፡በቀዳማይ በካልዓይ ይገባሉ፡፡ኳ በቀዳማይ ፤ በካልዓይ ፤ በሣልሳይ ይገባል፡፡
ጴጥሮስ እመ ይቤልዎ ተሰቀልሁ አምላክከ እስመ/ኳ ተሰቅለ፡፡

**፲፫, እንቋዕ፤ጥቀ**

‹ስንኳን› ተብለው ይፈታሉ፡፡ እንቋዕ በቀዳማይ፤ በካልዓይ ጥቀ በሣልሳይ አንቀጽ ይገባሉ፡፡

- እንቋዕ ሞተ ሰሎሞን እንበለ ይርአይ ሙስናሃ ለሀገሩ፡፡
- ይቤሎ ለዘይቤሎ ይሙትኑ እኁከ ጥቀ ይሙት ሕማምኒ ኢይርከቦ፡፡
- እፎ አማሰኖሙ ለአይሁድ እግዚአብሔር ባሕቱ እንቋዕ አማሰኖሙ እስመ ሰቀልዎ እንበለ ፍትሕ፡፡

**፲፬, እንከ፤እምዮም/እምይእዜ**

‹እነሆ› ‹እንግዲያው› ‹እንኪያው› ተብለው ይፈታሉ፡፡

**፲፰, አ፤ኬ፤ሶ**

እነዚህ ቃለ አጋኖ ቃለ መልእክት ይሆናሉ፡፡ ‹አ፤ኬ› ቃለ አጋኖ ሲሆኑ በቀዳማይ በካልዓይ ይገባሉ፡፡ቃለ መልእክት ሲሆኑ ከ‹ሶ› ጋር በሣልሳይ ይገባሉ፡፡

- ንስጥሮስ እፎ ኀደገ አምላኮ ጸልአኬ ነፍሶ፡፡
- አ እግዚአ አድኅንሶ አ እግዚአ ሠርሕሶ፡፡
- በእፎ ክሕደ ይሁዳ ሃይማኖቶ እምከመሰ ክሕደ ሃይማኖቶ ፈተወአ ኀጉለ ነፍሱ፡፡

**፲፱, ሰ**

‹ስ፤ ሳ፤ ማ› ይሆናል፡፡ ሳ ሲሆን በቀዳማይ ፤ በካልዓይ ሲገባ መነሻው እፎ ፤ በእፎ ፤ለምንት ናቸው፡፡

- እፎ ኀደገ ንስጥሮስ አምላኮ ይወርድሰ ሲያለ በይነ ኀደገ አምላኮ፡፡

‹ሰ፤ስ፤ማ› ሲሆን በተያቂና በመላሽ ቃል በይቤ ይነገራል፡፡ በጠያቂው አንቀጽ ሁ፤ ኑ በጽድቅ ባሉታ ይገባሉ፡፡

- ይቤሎ ሰብእ እመ ይቤሎ ሰብእ በልዐሁ ዮሐንስ ቆጽለ እንከሰ እመ ኢበልዐ ቆጽለ ምንተ በልዐ፡፡
- ይብሎ ሰብእ ለእንተ ይብሎ ይትቤዘዎኑ አምላክ ለአዳም እምከመሰ ኢተቤዘዎ አምላክ መኑ እምተቤዘዎ፡፡

**፫.፫.፫ ደቂቅ አገባብ**

ከስም ላይ ወድቆ ሰዋስውን የሚያሳካ /የሚያያይዝ/ ዐ.ነገርን የሚያስማማ ደቂቅ አገባብ ይባላል።

- ደቂቅ የተባለበት ምክንያት ከአንቀጽ ላይ ስለማይወድቅ ነው።
- አገባብ የተባለበት ምክንያት በስም ላይ እየወደቀ ሰዋስውን ስለሚያሳካ(ስለሚያያይዝ) የዐ.ነገር ማስማሚያ ስለሚሆን ነው።

ምሳሌ፡-ላዕለ፣ መልዕልተ፣ ታሕተ፣ መትሕተ፣ ዲበ፣ ውስተ፣ መንገለ፣ ኀበ፣ ማእከለ

- ላዕለ/መልዕልተ/ ደብረ ታቦር አስተርአየ መንግስተ እግዚአብሔር
- ወሰከ ሳኦል ኃጢያተ በዲበ ኃጢያት
- ተበውሐ/ተሠልጠ ሚካኦል ታህተ/መትሕተ/ እግዚአብሔር

አገባብ ሳይወድቅበት

- ኢይደልወከ ከመአንተ ትባእ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ
- ለእመ ሀሎ ጠቢብ ኢይትነሳእ ላዕለ ብእሲ ዘገብረ ሀካየ እስመ እግዚአብሔር ለሊሁ ይገሥጾ ለብእሲ ሀካይ

አገባብ ሲወድቅበት

- አሐዱ አሐዱ ይሣለቅ በላዕለ ቢጹ
- ወልደ እግዚአብሄር በሎ ለናትናኤል ብእሴ ሳሌም ርኢኩከ በታህተ ዕፀ በለስ
- ወእስከ አጽናፈ ዓለም በፅሐ ነቢቦሙ

**የደቂቅ አገባብ ሙያ**

1. መነሻ፤_ መኑ ይትዔረዮ ለእግዚአብሔር በደመናት
2. መገስገሻ፡-መንገለ አድባር ወጽዐ ነአዊ ልዑል ከመይቅትል ቀትለ
3. ማንጸሪያ፡-ኩኑ ጻድቃነ ከመ አነሂ ጻድቅ
4. አፈ.ቃቃሪ፡-አበስነ ምስለ አሕዛብ ዐላውያን

ደቂቅ አገባባት የሚዘረዘሩ እና የማዘረዘሩ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ምሳሌ፡- የማይዘረዘሩ------እስከ፡ እንበይነ፡ እም ወዘተ

የሚይዘረዘሩ------ከመ፡ ዲበ ፡ላዕለ ፡ ወዘተ

ደቂቅ አገባባት ቃልን ከቃል የሚያዛምዱ እንደመሆናቸው መጠን ሰፋ ያለ ትርጓሜ ይዘው ይገኛሉ፡፡ በጽሑፍም ሆነ በንግግር በብዛት የምንጠቀምባቸው ደቂቅ አገባባት የሚከተሉት ናቸው፡፡

**፩, ዲበ፤ላዕለ፤መልዕልተ**

በ----ላይ ፤ ስለ ተብለው ይፈታሉ፡፡በግብር ፤ በስም ፤ በቦታ ፤ በጥሬ ይገባሉ፡፡

ምሳሌ፡-ዲበ/ላዕለ/መልዕልተ <u>ሐዋርያት</u> ኀደረ መንፈስ ቅዱስ፡፡ ----------በግብር ሲገባ(ሐዋርያት የግብር ስም ነው፡፡)

ዲበ/ላዕለ/መልዕልተ <u>ማርያም</u> ኀደረ መንፈስ ቅዱስ፡፡ ----------በስም ሲገባ(ማርያም ስም ነው፡፡)

ዲበ/ላዕለ/መልዕልተ <u>ደብረ ታቦር</u> አስተርአየ መንግስተ እግዚአብሔር፡፡------በቦታ ሲገባ(ደብረ ታቦር የቦታ ስም ነው፡፡)

ወሰከ ሳኦል ኃጢያተ በዲበ/ላዕለ/መልዕልተ <u>ኃጢያቱ</u>፡፡------በጥሬ ሲገባ(ኃጢያት ጥሬ ነው፡፡)

ጸልዩ ላዕሌነ---------ስለእኛ ጸልዩ፡፡ ላዕለ ----ስለ ተብሎ ሲፈታ

ላዕለ፤ መልዕልተ፤ ዲበ ተብለው ተነስተው የተነበቡ እንደሆነ በላይ፤ ወደላይ ተብለው ይፈታሉ፡፡

ምሳሌ፡-ዐርገ ላዕለ-----ወደላይ ወጣ

ነበረ ላዕለ -----በላይ ተቀመጠ

**ማስታወሻ፡-**

- ደቂቅ አገባባት ብቻቸውን አይነበቡም፤ ከፊታቸው ካለው ስም ጋር አብረው በአንድ ትንፋሽ እንደአንድ ቃል ይነበባሉ እንጅ፡፡ ከላይ እንዳየነው ‹በላይ፤ ወደላይ› ተብለው የተፈቱ እንደሆነ ግን ተነስተው ይነበባሉ፡፡

**፪, ታሕተ፤ታሕቲቱ፤መትሕተ**

በ----ታች ተብለው ይፈታሉ፡፡በግብር ፤ በስም ፤ በቦታ ፤ በአካል ይገባሉ፡፡ ታሕተ፤መትሕተ፤ታሕቱተ ተብለው ተነስተው ከተነበቡ በታች ወደተች ተችን ተብለው ይፈታሉ፡፡

ምሳሌ፡-ተሠልጠ ሚካኤል ታሕተ/መትሕተ/ታሕቲተ እግዚአብሔር፡፡

ተበውሐ ገብርኤል ታሕተ/መትሕተ/ታሕቲተ ሥላሴ፡፡

ወረደ ታሕተ--------ወደታች ወረደ፡፡

**፫, ውስተ፤ውሳጤ**

በ---ውስጥ ማለት ነው፤በቦታ ይገባል፡፡ውስተ፤ውሳጤ፤ውሳጢተ ተብለው ተነስተው ሲነበቡ ወደውስጥ ውስጥን ተብለው ይፈታሉ፡፡

ምሳሌ፡- ኀደረ ዳንኤል ውስተ ግበ አንበሳ

ነበረ ገሪማ ውሳቴ ገዳም

ውስተ ኄተ መቅደስ ነበርኪ

ቦአ ውስተ/ውሳጤ------ወደውስጥ ገባ

ነበረ ውስተ/ውሳጤ------በውስጥ ተቀመጠ

ነጸረ ውስተ/ውሳጤ------ወደውስጥ ተመለከተ

**፬, ቅድመ**

በ---ፊት ማለት ነው፡፡ በስም በግብር ይገባል፡፡ ቅድመ ተብሎ ተነስቶ ከተነበበ ወደፊት፤ ፊትን ተብሎ ይፈታል፡፡

ምሳሌ፡- ቅድመ ዳዊት ቆመ አቢሳ

ሖረ ቅድመ/ፍጽመ -------ወደፊት ሔደ

ነጸረ ቅድመ/ፍጽመ ------ወደፊት ተመለከተ/ፊትን አየ

ቆመ ቅድመ/ፍጽመ-------በፊት ቆመ

**፭, ድኅረ**

በ---ኋላ ማለት ነው፡፡ለሚስጥር ጊዜ ነው፡፡በስም በግብር ይገባል፡፡ ተነስቶ ከተነበበ ወደኋላ፤ በኋላ ተብሎ ይፈታል፡፡

ምሳሌ፡- ድኅረ ነግሠ ዳዊት ነግሠ ሰሎሞን፡፡

እምድኅረ ፀደይ ይመጽዕ ክረምት፡፡

ቆመ ድኅረ-----ወደኋላ፤ በኋላ ቆመ ገብአ ድኅረ--------ወደኋላ ተመለሰ ነጸረ ድኅረ------ወደኋላ ተመለከተ

**፯, ማዕከለ**

በ---መሀል፤ መካከል ማለት ነው፡፡በስም ፤ በግብር ፤ በቦታ ገባል፡፡ ተነስቶ ከተነበበ በመሀል፤ መሀልን ተብሎ ይፈታል፡፡

ምሳሌ:- ማዕከለ ዳዊት ወሳኦል ነበረ ናታን፡፡

ማዕከለ ክልዔቱ ፈያት ተሰቅለ ችግዚእነ፡፡

**፰, ኀበ፤መንገለ፤ውስተ፤እንተ**

እነዚህ ደቂቅ አገባባት ወደ ተብለው ይፈታሉ፡፡

ምሳሌ:- ቦአ ኀበ/መንገለ/ውስተ/እንተ ቤት፡፡

ዐደወ እምዘመነ አሪት ኀበ/መንገለ/ውስተ/እንተ ዘመነ ወንጌል፡፡

**፱, ለ**

‹ለ› ደቂቅ አገባብ ሲሆን ትርጉሞቹም ብዙ ናቸው፡፡ በአብዛኛው የሚኖሩት ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አዳማቂ (ትርጉም አልባ) ይሆናል፡፡

   ምሳሌ፡-ዘጸምዐ ለይምጻዕ ኀቤየ-------ተጠማ ወደእኔ ይምጣ፡፡

   ለትባእ ጸሎትየ ቅድሜከ-----ጸሎቴ በፊትህ ትድረስ፡፡

2. በቁም ቀሪ (ትርጉሙ ‹ለ›) ይሆናል፡፡

   ምሳሌ፡-ለሢመት ተኀረየ-------ለሹመት ተመረጠ፡፡

   ለአምላክ ተቀነየ-------ለአምላክ ተገዛ፡፡

3. ዘርፍ አያያዥ (ትርጉሙ ‹የ›) ይሆናል፡፡

   ምሳሌ፡-አይቴ ብሔራ ለጥበብ-------የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው፡፡

   ሐዲስ ውእቱ ልብሱ ለሳሙኤል-----የሳሙኤል ልብሱ አዲስ ነው፡፡

4. መገስገሻ (ትርጉሙ ‹ወደ›) ይሆናል፡፡

   ምሳሌ፡-ቦአ ለቤት----------ወደ ቤት ገባ፡፡

   ዐደወ እምዘመነ አሪት ለዘመነ ወንጌል----ከኦሪት ዘመን ወደወንጌል ዘመን ተሻገረ፡፡

5. ተጠቃሽ ተሳቢ (ትርጉሙ ‹ን›) ይሆናል፡፡

   ምሳሌ፡-ሰቀልዎ አይሁድ ለኢሱስ----------አይሁድ ኢየሱስን ሰቀሉት፡፡

   አዳም አእመራ ለሔዋን----አዳም ሔዋንን አወቃት፡፡

**፲, በ**

‹በ›ም እንደ ‹ለ› ሁሉ ደቂቅ አገባብ ሲሆን ትርጉሞቹም ብዙ ናቸው፡፡ በዋናነት የሚኖሩት ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) አዳማቂ (ትርጉም አልባ) ይሆናል፡፡

   ምሳሌ:- በከመ ጸሐፈ ወንጌለ ጸሐፈ መልእከክተ፡፡

2) በቁም ቀሪ (ትርጉሙ ‹በ›) ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ በብትን ሰዋስው ይገባል፡፡

   ምሳሌ:- ወመሐለ ሙሴ በይእቲ ዕለት፡፡

   በገዳም ነበረ፡፡

   በፀዊረ መስቀል ደክመ፡፡

3) ትርጉሙ ‹ለ› ይሆናል፡፡ ‹በ› ‹ለ› ሲሆን በአካል ይገባል፡፡ በመደራረግ ፤ በማደራረግ ያሳስራል፡፡

   ምሳሌ:- ያስተናጽር እግዚእ አመ ምጽአቱ ኩሉ ገጽ በገጽ፡፡

4) ትርጉሙ ‹በ---ጊዜ› ተብሎ ይፈታል፡፡ ማንጸሪያ ሆኖም ይገባል(ትርጉሙ ‹እንደ› ይሆናል)፡፡

   ምሳሌ፡-በምንዳቤየ ተዘከርኩከ፡፡--------አቤቱ በችግሬ ጊዜ አሰብሁህ፡፡

   ጽድቅ በወልታ የዐውደከ፡፡-------ጽድቅ እንደ ጋሻ ይከብሃል፡፡

**ማስታወሻ፡-**

- ‹በ› በማይስማማው ግስ ሲነገር ለሚስማማው ግስ ቸልታ ሆኖ ይፈታል፡፡

**ምሳሌ፡-**

*መሀረ እግዚእ ወንጌለ በሥጋ----በሥጋ ተገልጦ(ታይቶ) አስተማረ፡፡*

*ሰበከ እግዚእ በነቢያት ሥጋዊሁ-----በነቢያት አድሮ አስተማረ፡፡*

**፲, አመ፤እንተ**

እነዚህ ደቂቅ አገባባት ‹ለ› ተብለው ይፈታሉ፡፡አመ ‹በ› ሲሆን በአኀዝ በጊዜ ይፈታል፡፡እንተ ‹በ› ሲሆን በቦታ በአካ ይፈታል፡፡

ምሳሌ፡- *አመዕለተ ፍዳ ኩንኒ ቃውመ ወቤዛ፡፡*

*ፈነወ እዴሁ እንተ ስቁረት፡፡*

*አስተማሰልኩኪ እንተ ኀቤየ፡፡*

**፲፩, በበ**

‹በየ› ተብሎ ይፈታል፡፡ የተጸውዖ ስም ሲቀር በቀር በብትን ሁሉ ይገባል፡፡

ምሳሌ፡- በበደወሉ ፤ በበብሔሩ ፤ በበዕለቱ ፤ በበሰዐቱ

**፲፪, እንበለ፤ኢ**

‹ያለ› ‹በቀር› ተብለው ይፈታሉ፡፡

ምሳሌ፡- እንበለ ዘርዕ ተፀንሰ፡፡ እንበለ ኃጢያት ተሰቅለ፡፡

ግብር ዘይትገበር በኢምክር ወኢሐተታ/በኢያእምሮ እበድ ውእቱ፡፡

‹ኢ› ከእንበለ ተለይቶ አላ----ም ፤ አል----ም ተብሎ ይፈታል፡፡

ምሳሌ፡- ኢያእመረ---አላወቀም ኢበላዕኩ----አልበላሁም

**፲፫, ወ**

ትርጉሙ ‹ም› ነው፡፡ ከአንቀጽ፤ ከስም፤ ከግብር፤ ከነገር ሁሉ በፊት ይገባል፡፡

ምሳሌ፡-*ሐመ ወሞተ ------ታመመ ሞተም፡፡*

ብእሲ ርኁብ አመበልዐ ኀብስተ ወሰትየ ጽዋዐ ባረከ ፈጣሪሁ---የተራብ ሰው ዳቦን በበላ ጽዋንም በጠጣ ጊዜ ፈጣሪውን አመሠገነ፡፡

ተሰደ ዮሴፍ ለግብጽ ማርያም ምስሌሁ፡፡----ዮሴፍ ወደግብጽ ተሰደደ ማርያምም ከእርሱ ጋር፡፡

**፲፬, ባህቱ፤ሰ**

ግን ተብለው ይፈታሉ፡፡ ያንዱን ለብዙ፤ የብዙውን ለአንድ፤ የወንዱን ለሴት፤ የሴቲቱን ለወንድ ፤ የቅርቡን ለሩቅ፤ የሩቁን ለቅርብ፤ የባዕዱን ለዘመድ፤ የዘመዱን ለባዕድ፤ የከፉውን ለመልካም፤ የጽድቁን ላሉታ፤ የአሉታውን ለጽድቅ ያበድራሉ፡፡

ምሳሌ፡-

- ይሁዳ ሤጠ ለክርስቶስ ቶማስሰ ተሠይጠ ሎቱ፡፡
- ሐና ቀሰፎ ለክርስቶስ ጴጥሮስ ባህቱ ተቀስፈ ሎቱ፡፡
- እሥራኤትል ጸልዕዎ ለሙሴ ሙሴሰ ተዐገሦሙ ለእሥራኤል፡፡

‹ሰ› ተለይቶ ለአገባብ ተራስ እየሆነ ባህቱ ግን ይሆናል፡፡

- ተክለ ሃይማኖት ለከበ ክብረ ኀበ ጸለየ ጸሎተ ኀበሰ ኢጸለየ ጸሎተ መርቅያን ኢረከበ ክብረ፡፡
- ንረክብ ክብረ እመናፈቅር ፆመ እመሰ ናፈቅር መብልዐ ንረክብ ኀሣረ፡፡

‹ባህቱ› ተለይቶ ነገር ግን ይሆናል፡፡ ከነገር በፊት ይውላል፡፡

- ሰሎሞን አእመረ ጥበበ ባህቱ ኢድኀነ እሞት፡፡
- ክህደ ጴጥሮስ ከመኢየአምሮ ለክርስቶስ ባህቱ ነስሐ ድኀረ፡፡

**፲፭, ሂ፤ኒ፤ዓዲ**

‹ሂ› እና ‹ኒ› በአንቀጽ ትራስ እሆኑ ‹ም› ተብለው ይፈታሉ፡፡ ለቅርብ፤ ለሩቅ፤ ለአንድ፤ ለብዙ፤ ለሴት፤ ለወንድ ድምበር ይሆንሉ፡፡

ምሳሌ፡- በልዐ ሰትየሂ/ሰትየኒ -------በላ ጠጣም፡፡

አመ ተሰቅለ ክርስቶስ አመሂ ተረግዘ አመኒ ተቀነወ አድኀነ ኲሎ ዓለመ፡፡----ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ በተወጋ ጊዜም በተቸነከረ ጊዜም ዓለምን ሁሉ አድኗል፡፡

‹ዓዲ› ‹ም› ተብሎ ሲፈታ ከነገር በፊት በኋላም ይገባል፡፡

ተሰቅለ ዓዲ ተቀነወ ------------ተሰቅሎም ተቸነከረ፡፡

‹ዓዲ› ከላይ ካየነው ሌላ ‹ገና፤ አሁን፤ እነሆ፤ ዳግመኛ› ተብሎ ይፈታል፡፡

ምሳሌዎች፡-ኢሞተ ኤሊያስ እስመ ዓዲ እድሜሁ፡፡------ኤሊያስ እድሜው ገና አልደረሰምና አልሞተም፡፡

ዓዲ መጽዐ፡፡------------አሁን/እነሆ መጣ፡፡

ይነግስ ሰሎሞን በመንበረ ዳዊት ወልደ እሴይ ወይፈትሕ ዓዲ ፍትሐ ለግፉዓን፡፡

**፲፮, ሌሎች ደቂቅ አገባቦች**

| | |
|---|---|
| ዝየ ---ከዚህ፤በዚህ | ለፌ----ወዲህ |
| ህየ----ከዚያ፤በዚያ | ከሀ/ከሀከ---ወዲያ |
| ከሀት---ወዲያኞች | ጥቃ፤ጎር፤ሕጽን፤ገቦ፤ ጉንድ---አጠገብ |
| ጸጉ---ጥግ | ዓውድ/ዘውር---ዙሪያ |
| ግድም----አግድም | ኩለሄ----ከሁሉ ዘንድ |
| ቅድም/ቀዲሙ/ቀዳሚ/አቅዲሙ---ቀድሞ፤አስቀድሞ፤ ፊት | ድኅረ፤ደኅሪ-----ከዋላ፤ በኋላ፤ ተከትሎ፤ አስከትሎ |
| ጥንት---መሠረት ፤መዠመሪያ | ፍፃሜ/ተፍፃሜት/ተፍፃም ----መጨረሻ |
| ትማልም/ትካት-----ድሮ | ጌሠም/ሳኒታ-----ከርሞ፤ማግስት |
| ዓዲ/ናሁ/ዮም/ይእዜ----ዛሬ፤አሁን | ዮም/ይእዜ----ዛሬ |
| የማን/ይምን----ቀኝ | ጺጋም/ጽግም -------ግራ |
| ድኅሪት/ግንጽሊት/ግፊተቲት----የኋሊት | አድያም/ደወል/ብሔር---አውራጃ |
| ጽፍሕ፤ጽንፍ፤ጽንፈፍ፤ጽላፍ፤ከንፍ፤ከንፈፍ፤ከነፊ፤ከንፈር፤ሐይቅ፤ድንጋግ------------ወሰን፤ዳር | |
| ማዕከል-----መሀከል | ትርጋጽ---ግርጌ |
| አፍአ----እዳሪ | ኩለንታ---ሁለንተና |
| ወትረ/ዘልፈ/ለዝሉፉ----ዘወትር | |

ምሳሌ፡-ሮፀ ሕፃን እምዝየ እስከ ከሀ

ሰበከ ጴጥሮስ እስከ ሮሜ ወእምህየ(ወእምከሀ) ተመይጠ ኀበ ማኅደሩ

ይነብሩ ሙታን ውስተ መቃብር እስከ ይትነሡኡ ድኅረ

ተአሥረ ክርስቶስ ድኅሪተ/ግንጽሊተ

በጽሐ ማዕከለ ባሕር

**ምልማድ ፬**

ሀ, ቀጥሎ የተሰጡትን ዐ.ነገሮች ተርጉሙ፡፡ ደቂቅ አገባቦችንም ለዩ፡፡

1) አኃውየ ግበሩ ጽድቀ በቅድመ እግዚአብሔር፡፡
2) ሰገደ በገጹ ውስተ ምድር አመ ቆመ ቅድመ እግዚእ፡፡
3) እለመኑ ይነብሩ ታሕተ እግረ ደብር፡፡
4) ርኢኩ ብእሴ እግዚአብሔር ውስተ በዐቱ፡፡
5) ማዕከለ ፈጣሪ ወፍጡራን ዘኮንኪ ጽላተ ኪዳን፡፡
6) እንቋእ መጻእክሙ ኀበ ቤተ ግእዝ በሰላም፡፡
7) ዉሉዱ ለያዕቆብ ወረዱ ውስተ ብሔረ ግብጽ፡፡

8) መኑ አምላክ እንበለ እግዚአብሔር፡፡
9) እግዚአብሔር ሣረራ ለምድር፡፡

ለ, የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ተርጉሙ የ‹ለ›ን እና የ‹በ›ን አገልግሎትም ግለጹ፡፡

1. ወራዙት እሙንቱ ዉሉዱ ለአዳም፡፡
2. ለይምጽው ኅቤየ እለየኀሥሡኒ፡፡
3. ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ፡፡
4. ለመኑ እነግር ኀዘነ ልብየ፡፡
5. እሉ እሙንቱ ሕጻናቲሃ ለማርታ፡፡
6. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ይብሉ መላእክት እንዘ ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር፡፡
7. ሤሞ ለጴጥሮስ ዘአንገሦ ለአዳም፡፡
8. ይትናጸር ግፉዕ ምስለ ገፋዒሁ ገጽ በገጽ በዕለተ ፍዳ፡፡
9. አአትብ ገጽየ ወኩለንታየ በትእምርተ መስቀል፡፡
10. ሃሌ ሉያ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ ገነዝዎ ለኢየሱስ በሰንዱናት ለዘተንሥአ እሙታን በመንክር ኪን፡፡

## ፫.፪ ንባበ ልሣነ ግእዝ

**፫.፪.፩ የስልክ ንግግር / ንባብ በምህላፈ ቃል**

አንድ ሰው ስልክ ሲደውል፣ ጥሪ ሲቀበል፣ ሰውን ሲያገናኝ፣ የተሳሳተ ቁጥር ሲያገኝ በግእዝ ቋንቋ የሚገልፅባቸው መንገዶች አሉ። በአጠቃላይ አንድ ሰው ስልክ ሲደውል ሊጠቀምባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ቃላቶች እና ሀረጎች የሚከተሉት ናቸው።

| ፩ ስልክ የሚያነሳው ሰው | ፪ ስልክ የደወለው የሚመልሰው መልስ |
|---|---|
| ▪ ነየ/ወይም ሄሎ/ ማኅበረ ቅዱሳን፣ ጅማ መካነ አእምሮ | ሄሎ እረክቦ ለጸሐፊሁ |
| ▪ መነ እብል/ መኑ አንተ/መኑ አንቲ | ሄሎ ሳሙኤል አነ እምብሔረ አሜሪካ |
| ▪ እፎ ወዐልከ ዳነኤል | ሄሎ እኁየ እስኩ ምስለ ልድያ አስተራክበኒ |
| ▪ መነ ተኀሥሥ ኢያእመርኩከ | ዳዊት አነ አኀሥሥ ለእኁየ ወልደ ሰንበት |

ስልኩን ያነሳው ሰው ሶስተኛ ሰው ከሆነ እና የሚፈለገው ሰው ካለ

- ዕቀበኒ ነስቲተ ሰዐተ አስተራክበከ
- ኦሆ ሀሎ እጼውእ ለከ
- ሀሎ ዳዕሙ ንስቲት ይርኀቅ

ስልኩን ያነሳው ሰው ሶስተኛ ሰው ከሆነ እና የሚፈለገው ሰው ከሌለ ደዋዩ መልእክት ሲያስተላልፍ

| | |
|---|---|
| ▪ ተሣሃለኒ ሳሙኤል ኢሀሎ | ትክህልኑ ዜንዎ መልእክት |
| ▪ ናሁ ወጽዐ ድኅረ ይመጽዕ | እኁየ እስኩ ንግር ሊተ መልእክተ |
| ▪ ብከኑ መልእክት | ንግሮ ከመ ኀሥሥክዎ |
| ▪ እንዘ ይትሜየጥ ከመ እዜኑ ለከ ምንተ ብከ ዘእነግር ለከ | አመ ይመጽእ ንግሮ ዘንተ |
| ▪ እክህልኑ ተወኪፎተ መልእክት | ድኅረ አስተራክበኒ ምስለ ሃና |

ስልክ የደወለው ሰው ቁጥር ከተሳሳተ

| | |
|---|---|
| ▪ ተሣሃለኒ እኁየ ኍልቈ ምእላፈ ቃል ስሒተከ ሀሎ | ተሣሃልኒ እኅትየ በእንተ ስሒትየ |
| ▪ ተሣሃለኒ እኁየ በዝ ስም ዘይትጼውእ ሰብእ ኢሀሎ | ተሣሃልኒ እኅትየ በእንተ ዘገበርኩ ስሒት |

ከላይ ያየነውን ይበልጥ ለመረዳት የሚከተሉትን ምሣሌዎች እንመልከት

፩ ሲሳይ ለዶክተር ዋስይሁን ሆቴል ውስጥ እያለ ይደውልለታል። ዋስይሁን ዶ/ር ነው ሲሳይ ደግሞ ነጋዴ ነው።

| | |
|---|---|
| ተቀባይዋ፡- ሄሎ ሂልተን ሆቴል | ሲሳይ፡- ለዶ/ር ዋስይሁን እክህልኑ እርከቦ |
| ተቀባይዋ፡-ኢሀሎ ዶ/ር ዋስይሁን እክልኑ ተወኪፎተ መልእክት | ሲሳይ፡- በእስፍንቱ ሰዐት ይትሜየጥ |
| ተቀባይዋ፡-ድኅረ አሐዱ ሰዐት ይትሜየጥ ሀሎ | ሲሳይ፡- ኦሆ ድኅረ አሐዱ ሰዐት ካዕበ እጼውዐኪ |
| ተቀባይዋ፡-ሠናይ ዳኅና ኩን | ሲሳይ፡- ኦሆ ዳኅና ኩኒ |

፪ ሄለን ለዲያቆን ዮናስ እየደወለች ነው።ዲ/ን ዮናስ በደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ን አገልጋይ ነው።

| | |
|---|---|
| ጸሐፊዋ፡- ሄሎ | ሄለን፡- ሄሎ እክህልኑ ረኪቦ ለዲ/ን ዮናስ |

ጸሐፊዋ፡- መኑ አንቲ ሄለን፡- አንሰ ሄለን አነ

ጸሐፊዋ፡- ተሣሃልኒ ዕቀቢ ንስቲተ ሄለን፡- ኦሆ

፫ ቤዛዊት እና ቤተ ልሔም የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሲሆኑ ጓደኛሞች ናቸው።

ቤዛዊት፡- ሄሎ ቤቲ ለምንት ጠፋሕኪ ቤተ ልሔም፡- አንሰ ኢጠፋሕኩ ለሊኪ እንዘ ትጠፍሒ ሊተ ጠፋሕኪ ትብልኒ

ቤዛዊት፡- ለምንት ኢረከብኩኪ በጽባሕ ቤተ ልሔም፡- ኀበ ደብረ መዊዕ ሐዊርየ ቦ

ቤዛዊት፡- በእንተ ዝንቱ ውእቱ ዘጠፋሕክኒ ቤተ ልሔም፡- አንቲ ኢሖርኪኑ ይእዜ መድኃኔዓለም ውእቱ

ቤዛዊት፡- ኢሖርኩ ዳእሙ በምሴት አሐውር ቤተ ልሔም፡-ለምንት ኀቢረነ ኢነሐውር

ቤዛዊት፡- አንሰ እትፌሣሕ ለእመ ፈቃድኪ ኮነ ቤተ ልሔም፡- ኦሆ ኀቢረነ ነሐውር

ቤዛዊት፡- በሰዐተ ሠርክ እጼውዐኪ ቤተ ልሔም፡- ኦሆ እኅትየ

ቤዛዊት፡- ሰላም ኩኒ ቤተ ልሔም፡- ለኩልነ

## ተፈጸመ ልሳነ ግእዝ ለዝንቱ ክፍል!!!